በእውነት፣ በእውቀት፣ በእምነት እና በፍቅር ለህዝባችን የግንዛቤ እድገት ሳናሳልስ እንሰራለን!

# የቀለም ቀንድ

ዘወትር ማክሰኞ

ማክሰኞ ሰኔ 17 ቀን 2006 ዓ.ም ቅፅ 01 ቁጥር 02 ብር 10.00

ግብረሰዶማዊነትን እንኩዋን ካልተቀበላችሁ በርሃብ የሚያልቀዉን ህዝባችሁን አንረዳም እስከማለት...



ሽንቁጥ አየለ

## ሰላማዊ አመፅ



መስከረም አበራ

በዘር ሳንከፋፈል አደባባዩ ላይ የምንሰነብተውስ ለስንት ቀን ይሆናል?

## አንዳንዴ አገሬን ሳስባት ከመጠቃት የደረሰች . . .



ሙሉቀን ተስፋው

. . .ሰው እንደወጣ መቅረት እንደቀላል የተቆጠረበት ዘመን

# እንደነት ማንንም አልዋጠም!

ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው



## ምዕራብ ወለጋ ከጊምቢ እና ቄለም /እንፍሌ ወረዳ/ አሽ ቀበሌ በሽህ የሚቆጠሩ የአማራ ተወላጆች ተፈናቀሉ ተባለ

2

## ኢትዮጵያ አሁንም ከዓለማችን ደሀ ሀገራት ከመጨረሻው ሁለተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች ተባለ::

2

## የCOC ብቃት ምዘናው በህግ ዓይን

5

## ዜና

# ምዕራብ ወለጋ ከጊምቢ እና ቄለም / እንፍሌ ወረዳ አሽ ቀበሌ በሽህ የሚቆጠሩ የአማራ ተጠላጀች ተፈናቀሉ::



የአሜሪካ ድምፅ ሬድዮ የአማርኛው ስርጭት ሰኔ 12 ቀን 2006 ዓ.ም እንደዘገበው በሺ የሚቆጠሩ የአማራ ተወላጆች በኃይል አካባቢውን እንዲለቁ ከመደረጉ በላይ ድብደባና ግድያ እየተፈፀመባቸው መሆኑን ጨምሮ ዘግቧል።

ዘገባው የተፈናቃዮችን ምስክርነት እንዳስደመጠው ድብደባና ግድያው በከተማው ህዝብና ፖሊስ የታገዘ መሆን እና ህይወታቸውን ያተረፉት በኮርኒስ እና ጫካ በመደበቅ መሆኑን ሲገልጹ አንድ ምስክርነታቸውን ለቪኦኤ የሰጡ ተፈናቃይ አክለው እንደገለፁት ከጊምቢ ከተማ ብቻ ከ3 ሺህ በላይ የአማርኛ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን መፈናቀላቸውን ተናግረዋል። ሌላው ምስክርነት ሰጭ ደግሞ ቁጥሩን ከ8 ሺህ ህዝብ በላይ አድርሰውታል። አምስት ልጆች የነበሯቸው መሆናቸውን የተናገሩት ሌላው ተፈናቃይ የነበራቸው መደብር መዘረፉንና ካለምንም ሀብት መቅረታቸውን ጉዳዩን አቤት ለማለት ወደ ባለስልጣናት ቢሄዱም ሰሚ ማጣታቸውን አስታውቀዋል። የቪኦኤ ጋዜጠኛ ያናገራቸው አቶ አወቀ የተባሉ ባለስልጣን በክልሉ ምንም አይነት ሰው የተባረረ እንደሌለ ገልፀዋል። የኦሮሚያ ክልል መንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች ኃላፊ ወ/ሮ ራሂያ ኢሳ #ሰዎቹ የሄዱት ፈርተው ነው; ካሉ በኋላ #ቁጥራቸው ከመቶ አያልፍም; ብለዋል።

የአማራ ተወላጆች በ2004 ከጉራ ፋርዳ፣ ከቤንሻንጉል፣ ከኢሊባቡርና ከወለጋ ኢ-ሰብአዊ ግፍ እየተፈፀመባቸው ለዘመናት ያፈሩት ንብረት እየተነጠቁ መባረራቸውን ያመለከቱ ዘገባዎች ሲወጡ የነበረ መሆኑ ይታወሳል።

# የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ከቤንሻንጉል ጉምዝ የተፈናቀሉ ዜጎች ለክስ የሚያበቃ በደል አልደረሰባቸውም አለ::



ከቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል የተፈናቀሉ ዜጎች በተወካዮቻቸው አማካኝነት የመሰረቱት ክስ በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት 8ኛ ፍትሀ ብሄር ምድብ በዋለው ችሎት የታየ ሲሆን በቀረበው ክስ ላይ የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴርና የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል መንግስት መልስ ሰጥተዋል።

ከሳሾች ለበርካታ አመታት ከኖሩበት ቀየ በህገ-ወጥ መንገድ በመፈናቀላቸው ሀብትና ንብረት ማጣታቸውን በጠበቃቸው አማካኝነት ተናግረዋል።

የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በበኩሉ# ከሳሾቹ ቤት ንብረት ምንም ለክስ የሚያበቃ ነገር ሳይኖራቸው ጉዳያቸው ለፖለቲካ ፍጆታነት እየዋለ ነው; በማለት መልስ ሰጥተዋል።

በጉዳዩ ዙሪያ ላይ ያነጋገርናቸው ጠበቃው ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማሪያም የፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ጉዳይ የሚመለከተው የክልሉን መንግስት እንጅ የፌደራሉን አይደለም በማለት የሰጠው መልስ ትክክል አለመሆኑን ተናግረዋል። የህገ-መንግስቱ አንቀፅ 52 ማንኛውም የሰብአዊ መብት ጥሰት ሲፈፀም የፌደራል መንግስቱን እንደሚያገባው፣ በዚህም የተነሳ የፌደራል መንግስቱን አይመለከትም ማለት እንደማይችል ገልፀዋል።

ዶ/ር ያዕቆብ ጠ/ሚ ኃ/ማሪያም ደሳለኝ #ከቤንሻንጉል ጉምዝ ሰዎች እንዲፈናቀሉ ያደረጉትን ለፍርድ እናቀርባለን; በማለት ተናግረው እንደነበር አስታውሰው አሁን እየታየ ያለው ግን የዚህ ተቃራኒ ነው ሲሉ አክለዋል።

# ኢትዮጵያ አሁንም ከዓለማችን ደሀ ሀገራት ከመጨረሻው ሁለተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች ተባለ::





የኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ዘርፈ ብዙ የድህነት መለኪያ ነጥቦች በተሰኘው ጥናቱ / Multidimensional Poverty Index (MPI) የ የአለማችንን 108 በማደግ ላይ ያሉ ሀገራትን የድህነት ደረጃ የፈተሸው ዩኒቨርሲቲው ጥናት ኢትዮጵያን ከ108ቱ ሀገራት ኒጀርን ብቻ በልጣ ከመጨረሻው ሁለተኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች ብሏል።

ደረጃው ጤና እና የትምህርት ሁኔታ ላይ የሚያጠነጥኑ 10 መስፈርቶች ሲኖሩት ከ10ሩ መስፈርቶች አንድ ሶስተኛውን እንኳ ያላገኘን ደረጃው ዘርፈ ብዙ ደሃ ሲለው ከመስፈርቱ ዝርዝር ውስጥ አንድ ሶስተኛው ያህል የተሟላለትን ደግሞ ለኑሮ መሰረታዊ ነገር ያልተሟሉለት ይለዋል።

በዚህ መሰረት ከኢትዮጵያ አጠቃላይ ህዝብ 87.3% ያህሉ ዘርፈ ብዙ ደሀ በሚለው ክልል ውስጥ ሲገኝ 58.1% ደግሞ መሰረታዊው ነገር ያልተሟሉለት በሚለው ክልል ውስጥ እንደሚገኝ የጥናት ውጤቱ ያስረዳል።

ኢትዮጵያ ባለፉት አመታት ውስጥ መሰረታዊ ነገር ያልተሟሉላቸው ዜጎቿን ቁጥር በመቀነስ ረገድ ጥሩ ውጤት ብታስመዘግብም ኢትዮጵያ አሁንም 76 ሚሊዮን ዘርፈ ብዙ ደሃ ህዝብ ያለባት ሀገር መሆኗን የጥናቱ ውጤት አረጋግጧል።

ይህም ቁጥር በአለማችን ካሉ መሰል በርካታ እጅግ ደሀ ህዝብ ከያዙ ሀገራት ማለትም ከህንድ፣ቻይና፣ ባንግላዴሽ እና ፓኪስታን በመቀጠል ኢትዮጵያ በ5ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች። የደረጃው ዝርዝር የገጠሪቱን ኢትዮጵያ አስመልክቶ 96.3% ህዝብ በድህነት ውስጥ እንደሚገኝ ሲገልፅ በአንፃሩ የከተማ ነዋሪው 46.4% በድህነት ውስጥ እንዳለ ያስረዳል።

በኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች የሚስተዋለውን የድህነት ደረጃ አስመልክቶ በሶማልያ 93% በኦሮሚያ 91.2% በአፋር 90.9% በአማራ 90.1% በትግራይ 85.4% ህዝብ በድህነት ውስጥ እንዳለ ገልጿል። ከተሞችንም በተመለከተ አዲስ አበባ ከሌሎች ከተሞች ይልቅ አነስተኛ ደሀ (20%) ያለባት ስትሆን ድሬዳዋና ሀረር ደግሞ አነስተኛ ደሀ በመያዝ በ54.9% እና 57.9% ይከተላሉ ሲል ድሬ-ቲዩብ ዘግቧል።

# የሰብአዊ መብት ጉባኤ ማጣራት ሊያደርግ መሆኑን አስታወቀ::

የሰብአዊ መብት ጉባኤ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቤታቸው የፈረሰባቸው ነዋሪዎች ያቀረቡትን አቤቱታ ሊያጣራ መሆኑን አስታወቀ።

የኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ነዋሪዎች #የመኖሪያ ቤታቸን ያለምንም ማስጠንቀቂያ በመንግስት አካላት በሌሊት የሰላም እንቅልፍ በተኛንበት ሰዓት ቤታችንን አፈረሱት; በማለት አቤቱታ ማቅረባቸውን ድርጅቱ ገልጿል።

ዋና ዳይሬክተሩ አቶ ግርማ በይሳ እንደተናገሩት አቤቱታ አቅራቢዎቹ #መጠለያ የለንም፣ ተደብድበን ነው ቤታችን የፈረሰው፣ ፖሊስ ጣቢያ ብናመለክትም ምንም አይነት መልስ አልሰጡንም; በማለት የተቃጠሉ ልጆቻቸውንና ራሳቸውን በፋሻ ጠቅልለው መምጣታቸውን ተናግረዋል። አያይዘውም ድርጅቱ በተዘዋዋሪ መንገድ ማጣራት ሲያደርግ ምንም ማስጠንቀቂያ እንዳልደረሳቸው ለመረዳት መቻሉን ገልጿል።

ድርጅቱ የአቤቱታ አቅራቢያዎችን ቃል መቀበሉንና በቅርብ ጊዜ አጣሪ ቡድን ወደ ስፍራው በመላክ ተገቢውን ማጣራት አድርጎ እውነትና ትክክል መሆኑ ከተረጋገጠ ከክፍለ ከተማው፣ ከማዘጋጃው እንዲሁም ከአዲስ አበባ አስተዳደር ጋር እርምጃ የሚወሰድበትንና መፍትሄ የሚፈለግበትን አግባብ እንደሚነጋገሩ ተናግረዋል፤ ይህ ካልሆነ ግን ጉዳዩን ለፓርላማ እንደሚያቀርብ አስታውቋል።

# ግብጻዊቷ ጋዜጠኛ በቀጥታ ቴሌቪዥን ስርጭት የኢትዮጵያ አምባሳደር ላይ በንዴት ስልክ ዘጋች::



ግብጻዊቷ የቴሌቪዥን ጋዜጠኛ ራኒያ ባዳዊ በግብጽ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሞሀመድ ድሪር ጋር በአረብኛ ስለኢትዮጵያው ታላቁ የህዳሴ ግድብ በቀጥታ በሚተላለፍ ስርጭት እየጠየቀቻቸው በነበረበት ወቅት አምባሳደሩ ‹‹የህዳሴው ግድብ አለም አቀፍ ደረጃ በጠበቀ ዲዛይን እየተሰራ ነው። በታችኛው የአባይ ተፋሰስ ሀገራት ላይ ምንም የሚያስከትለው ተጽዕኖ የለም›› በማለት ሲያብራሩላት ግብጻዊቷ ጋዜጠኛ ‹‹የህዳሴውን ግድብ ግብጽ ማስተዳደር ትችላለችን?›› የሚል ጥያቄ አነሳች።አምባሰደሩም ‹‹የህዳሴውን ግድብ ማስተዳደር የምትችል ኢትዮጵያ ብቻ ናት›› ብለው ሲመልሱ ጋዜጠኛዋ በንዴት ስልኩ እንዲቋረጥ አደረገች። ጋዜጠኛ ራኒያ ባዳዊ አምባሳደር ሞሀመድ ድሪሪን ምንም እንዲናገሩ ሳትፈቅድላቸው አሊያም በጨዋነት ሳታሰናብታቸው በንዴት ስልክ መዝጋቷን የተለያዩ የዜና አውታሮች ዘግበውታል።

# "ያገባኛል ባይነትና ጋዜጠኝነት በአምባገነን ስርዓት ውስጥ" በሚል ርዕስ የውይይት መድረክ ተካሄደ ::



የሰማያዊ ፓርቲ ወጣቶች ጉዳይ ቅዳሜ በ14/10/06 ዓ.ም ከቀኑ 9:30 ጀምሮ ሃሳባቸውን በነፃነት በመግለጻቸው ብቻ ወደ እስር ቤት እየተወረወሩ ስላሉት ኢትዮጵያውያን ፖለቲከኞችና ጋዜጠኞች የውይይት መድረክ በማዘጋጀት ጋዜጠኛ አናኒያ ሶሪ፣ ኤልያስ ገብሩና ዳዊት ሰለሞን "ያገባኛል ባይነት እና ጋዜጠኝነት በአምባገነን ስርዓት ውስጥ" በሚል ርዕስ ያዘጋጁት ውይይት የሰማያዊ ፓርቲ ፕሬዚዳንት ኢ/ር ይልቃል ጌትነትና ጥሪ የተደረገላቸው ተጋባዥ እንግዶች በተገኙበት ተካሂዷል።

በውይይቱም ጋዜጠኛ አናኒያ ሶሪ የሃሳብ ነፃነትን በማራመዳቸው የታሰሩ ጋዜጠኞችና ፖለቲከኞች እንዲሁም ጦማሪያን መታሰራቸው ከፍትህ ውጭ መሆኑን ሰፊ ትንታኔ ሰጥቶበታል። በዘላቂነትም መፍትሔው ሁሉን አቀፍ የህዝብ ትግል ለዲሞክራሲ ግንባታ ወሳኝ መሆኑን አስምሮበታል። ከውይይቱ ተካፋዮችም ሃሳብ ተሰጥቶበት የዕለቱ የውይይት መድረክ ተጠናቋል።

ድርጅትዎንና አገልግሎትዎን
በዚህ ሳምንታዊ ጋዜጣ
ያስተዋውቁ
0934-680524

ርዕሰ አንቀፅ

# ህዝባችንን ከአባቶቹ ሀገር እያፈናቀሉ ማባረሩ ይቁም

ቪኦኤና ልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ሰሞኑን እንደ ዘገቡት ኢትዮጵያዉያን ዜጎች አማሮች በመሆናቸዉ ብቻ ሀብት ካፈሩበትና በህጋዊነት ከኖሩበት ቀያቸዉ ( ከምዕራብ ወለጋ ከጊምቢ እና ቄሌም (እንፍሌ ወረዳ አሽ ቀበሌ) አገራችሁ አይደለም ተብለዉ እየተፈናቀሉ ተባረዋል:: ይህ ድርጊት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ተደጋግሞ መከሰቱ ይታወቃል:: አማሮቹ ለምን ከልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ክፍል እንደሚባረሩ አንዳንድ ባለስልጣናት የሚሰጡት መልስ የዜጎችን ህገ-መንግስታዊ መብት የሚጥስ ከመሆኑም በላይ ለነገይቱ ኢትዮጵያ ህልውና እጅግ አደገኛ ሆኖ ይስተዋላል:: የሰሞኑን መባረርና መፈናቀል በማስመልከት የተጠዬቁ ባለስልጣናት መልስም የሚያረጋግጥልን ይሄንኑ ነዉ:: ሲቀልዱ ይሁን በራሳቸዉ ህዝብ ላይ ሲዘብቱ "ፈርተዉ ነዉ አካባቢዉን ጥለዉ የሸሹት" ወይም "የተባረሩት ሰዎች መቶ አይሆኑም" ሲሉ ይመልሳሉ:: እንዲህ አይነት መልስን በ21ኛው ክፍለ ዘመን ከሚኖር ባለስልጣን መጠበቅ እጅግ ከባድ ነዉ:: ያዉም አንዲት ሀገር ህገ-መንግስት ዘርግታና በህገ መንግስቱ ስር የተዋቀሩ ልዩ ልዩ ህጎችን ለአጠቃላይ ሀገራዊ ስርዓቱ መተዳደሪያነት አስፍና በምትገኝበት ወቅት እንደዚህ አይነት በዘበትና በንቀት የተሞሉ የባለስልጣናት መልሶች ባለስልጣናቱን ከስልጣን መንበራቸዉ ሊያስነሳቸዉ ይገባል እንላለን::

በህገ-መንግሰቱ መሰረት ወላጆቹ ወይም ከወላጆቹ አንዱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ነዉ/አንቀፅ 6/1/ :: ኢትዮጵያዊ ዜጋ ደግሞ በህገ መንግሰቱ የተቀዳጃቸዉ መብቶች አሉት:: እነሱም በህግ ይጠበቁለታል:: እንደ ህገ መንግሰቱ ገለጻ ማለት ነዉ:: ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ከፈቃዱ ዉጭ ዜግነቱ ሊገፈፍ አይችልም (አንቀጽ 33/1 ):: ደግሞም ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የኢትዮጵያ ዜግነት የሚያስገኘዉን መብት፣ ጥበቃ እና ጥቅም የማግኘት መብት አለዉ (አንቀጽ 33/2).:: እንግዲህ የምናወራዉ ህገ-መንግስቱ በዜግነታቸዉ መብት ስላቀዳጃቸዉ ኢትዮጵያዉያን ዜጎችና መብታቸዉም በህገ መንግስቱ ስለሚጠበቅላቸዉ ዜጎች ነዉ::

ህገ መንግስቱ ለማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የመዘዋወር ነፃነት በአንቀፅ 32 አጎናፅፎአል:: አማራ ፣ ኦሮሞ : ትግሬ ወይም ያኛዉ ብሄር ሳይል ስለመዘዋወር ነፃነት እንዲህ ይላል: -ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ወይም በህጋዊ መንገድ ሀገሪቱ ዉስጥ የሚገኝ የዉጭ ዜጋ በመረጠዉ የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖርያ ቦታ የመመስረት እንዲሁም በፈለገዉ ጊዜ ከሀገር የመዉጣት ነፃነት አለዉ :: እንኳዋን ኢትዮጵያዊ ይቅርና የሌላም አገር ዜጋ የመዘዋወር ነፃነቱ ተጠብቆለታል:: እንደያዉም የኢትዮጵያዊዉን ዜጎች መብት የኢኮኖሚ የማህበራዊና የባህል መብቶች በሚልና በአንቀፅ 43 ስር እንዲህ አስፋፍቶ ያስቀምጥለታል:-

- ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ዉስጥ በማንኛዉም ኢኮኖሚዊ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪየዉ የመረጠዉን ስራ የመስራት መብት አለዉ (43/1)
- ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያዉን ስራዉንና ሙያዉን የመምረጥ መብት አለዉ -43/2
- መንግሰት ለስራ አጦችና ለችግረኞች ስራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል -43/6
- መንግስት ዜጎች ጠቃሚ ስራ የማግኘት ዕድላቸዉ እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል- 43/7
- ገበሬዎችና አርብቶ አደር ኢትዮጵያዉያን በየጊዜዉ እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸዉና ለምርት ካደረጉት አስተዋፅኦ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተገቢ ዋጋ ለምርት ዉጤቶቻቸዉ የማግኘት መብት አላቸዉ:: መንግስት የኢኮኖሚና የማህበራዊ የልማት ፖሊሲዎችን በሚተልምበት ጊዜ በዚህ መርህ መመራት አለበት-43/8

ታዲ በጥረታቸዉ ሀብት ያፈሩ ሰዎችን ፣ የዜግነት መብታቸዉን ተጠቅመዉ በሀገሪቱ ተዘዋዉረዉ በልዩ ልዩ ስራ ላይ የተሰማሩ ዜጎችን ከሀገራቸዉ ማባረር ምን ይባላል? ህገመንግስቱ እንደሚያትተዉ በኢኮኖሚ እንዲጎለብቱ እንዲሁም በባህል እንዲጠናከሩ በልዩልዩ ፖሊሲዎች መደገፍ ተገቢዉ ነዉ:: እየሆነ ያለዉ ግን ተቃራኒ ነዉ::

የዚህ ሁሉ ጣጣ መነሻዉ አንዱ ማህበረሰብ ለአንዱ አካባቢ ወራሪና መጤ ተደርጎ መፈረጁና ደርዝ ባለዉ መልክ ይሄዉ ሙት አስተሳሰብ በማህበረሰባችን ዉስጥ መነዛቱ ነዉ:: ሆኖም ኢትዮጵያ የሁሉም ኢትዮጵያዉያን ማህበርሰቦች ያባቶቻቸዉ ሀገር ነች:: ማንም ወራሪ : ማንም ተወራሪ : ማንም መጤ ወይም ደግሞ ለዬትኛዉም አካባቢ ማንም ብቸኛ ባለሀገር የለም:: ይህ ታላቅ ሀገር: ይህ ታላቅ ህዝብ በታላቅ አክብሮት ሊጠበቅና ሊመራ ይገባዋል እንላለን:: የኢትዮጵያ ህዝብ በኢኮኖሚ መመንመኑ ብቻ ተሰፍሮ በንቀት አይን ሊታይ የሚገባዉ ህዝብ አይደለም:: የኢትዮጵያ ህዝብ ባለ ታላቅ ባህል: ባለ ታላቅ ታሪክ : ከፍ ያል ስነልቦናዊ ጭብጥ ያለዉ: እጅግ በፍቅርና በመተሳሰብ ታላቅ የህዝብ ዉህደትን በማከናወን መሰረት የረገጠ ዉህድ ኢትዮጵያዊ የጋራ እሴትን ያፈራ ህዝብ ነዉ:: ከሰሜን እስከ ደቡብ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ታላቅ የህዝብ ዉህደት : መደባለቅ ብሎም የጋራ ታላቅ እሴትን መገንባት የቻለ ህዝብ ነዉ:: ሀገሪቱ ኢትዮጵያም የሁሉም የጋራ ሀገር ነች:: ኢትዮጵያም ተጠብቃና ታፍራ ለዘመናት የኖረችዉ በሁሉም ኢትዮጵያዉያን ታላቅ ያጋራ ተጋድሎ ነዉ::

በመሆኑም አንዱን ወገን ከአባቶቹ ሀገር አባሮ አንዱን ወገን ባለ ሙሉ መብት ለማድረግ የሚደረግ ሙከራ ሁሉ እዳና መዘዙ በቀላሉ ተመዞም ተሰፍሮም አያልቅም:: እናም ለአጠቃላይ ኢትዮጵያዉያን የወደፊት የጋራ ደህንነት ሲባል ህዝባችንን ካባቶቹ ሀገር እያፈናቀሉ ማባረር ይቁም እንላለን:: የአንድ ማህበርሰብ አይደለም የእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ሰበአዊ መብቱ ብሎም ህገመንግስታዊ መብቱ ሙሉ ለሙሉ መከበር አለበት ብለን እናምናለን:: እናም ህዝባችንን ከአባቶቹ ሀገር እያፈናቀሉ ማባረሩ በፍጥነት ይቆም ዘንድ እናሳስባለን::


**ዲኦንሄር ፐብሊሽንግ ሚዲያ እና ኮሚንኬሽን ኃ/የተ/የግ/ማህበር**

መጋቢት 2006 ዓ.ም ተመሰረተ

ሥራ አስኪያጅ
ዮናስ ሙሉጌታ

ማኔጂንግ ኤዲተር
ሙሉቀን ተስፋው

ም/ማኔጂንግ ኤዲተር
መስከረም አበራ

ዋና አዘጋጅ
በለጠ ካሳ መኮንን
+251-911-58-90-88
beletekassa@gmail.com

ከፍተኛ አዘጋጅ
መለሰ እንግዳ
+251-9-11-89-83-65

ሪፖርተር
ደረጀ ወንዲይፍራው

## አምደኞች

ዶ/ር ደስታው አንዳርጌ
መልካምሰው አባተ
ሽንቁጥ አየለ
ደምስ ሰይፉ
ኪያ ዓሊ
ቃልኪዳን ኃይሉ
ውብሽት ሙላት
ይባቤ አዳነ

የኮምፒውተር ፅሁፍ
ምናለሽዋ ሞገሴ

ሌይ ዓውት እና ዲዛይን
አህመድ ናስር ባለኬር
0913 70 09 22

አድራሻ:-
ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 08
የቤት ቁጥር 471

Email: yekelemkend@yahoo.com
Facebook: www.facebook.com/yekelemkend
Website:www.iwooket.com/yekelmkend
Mobile: +251934680524


# ማስተካከያ

- እኔን የሚያበሽቁኝ በሚለው መጣጥፍ ስር በከተማችን ከሚገኙ FM ሬድዮ ጣቢያዎች 1 FM ሬድዮ በግል ይዞታነት ይገኛል የሚለው ሁለት FM ሬድዮ ጣቢያዎች በሚል ከይቅርታ ጋር የተስተካከለ መሆኑን ለአንባቢዎቻችን እንገልፃለን::
- የቤት ቁጥሩ ደግሞ 470 ሳይሆን 471 ተብሎ እንዲስተካከልልን እንጠይቃለን::

ትኩረት

# ለተቃዉሞ ትግሉ ስኬት ዉህደት ወይስ የፓርቲዎች ህበረት



በአስፋዉ ጌታቸዉ

የመድበለ ፓርቲ ስርዓት አንዱ መገለጫ በሀገሪቱ ዉስጥ ሁለትና ከዚያም በላይ የሆኑ የተለያየ የፖለቲካ የኢኮነሚ የማህበራዊና ርዕዮተ ዓለማዊ ፍልስፍና የሚራምዱ ፓርቲዎች አማራጮቻቸዉን በሰለጠነና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ለህዝብ በማቅረብ ለመንግስትነት የሚወዳደሩበት ስርዓት ነዉ:: በሰለጠነዉ ዓለም ህዝቡ ራሱ አማረጭ ሀይልን ለሚዛን ማስጠበቂያ (check and balance ) ስለሚፈልገዉ አማራጭ ፓርቲዎች እንዲጠናከሩ አባል ባይሆንም እንçን ድጋፍ ያደርጋል:: እንዲሁም እንዱ ፓርቲ ብቻ ወንበሩን 99.6 % እንደ ኢህአዴግ ጠቅልሎ አንዳይወስድና ፓርላማዉም ጥሩ ስብጥርና ሚዛኑን የተበቀኛ ሀሳቦች የሚነሸራሸሩበት እንዲሆን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ወንበር እንዲያገኑ ይመርጣቸዋል:: እንዲሁም የምርጫ አስፈፃሚዉ ነፃና ገለልተኛ በመሆኑ ህዘቡ ፓርቲዎች በስልጣን ቆይታ መባለግ እንዳያመጡ መንግስትን የመቀየር ባለዉ ስልጣን ተጠቅሞ ፓርቲዎችን በገዥነት ይቀያይራቸዋል::

በሰለጠነዉ ዓለም ይህ ሁሉ ሊሆን የቻለዉ የፓርቲዎቹ በቁጥር ቢያንስ 3 ቢበዛ 5 የማይሞሉ ፓርቲዎች ብቻ እንዲኖሩ ህግ ገድቦ ሳይሆን ህዝቡ ራሱ ፓርቲ የሚያሥፈልገዉ ለህዝብ አመራረጥ ምቹ የሆኑ ዉስን ፓርቲ ብቻ እንደሚያሥፈልገዉ ያመነና ከዚህ ዉጭ ግለሰቦች ድንገት ብድግ ብለዉ ፓርቲ እንደ አሸን በማፍላት የግለሰቦች የአደባባይ መዉጫ የማድረግ የግለኝነት (supper ego ) የወደቀ የሞራል ስብእና ያልተላበሱ ህዝቦች በመሆናቸዉ ነዉ ዉስን የፓርቲዎች ቁጥር ሊኖራቸዉ የቻለዉ::

ይህን ወደ ኢትዮጵያ ስንመልሰዉ ፓርቲዎች እንደ አሸን በየእለቱ የሚፈለፈሉበትን 4 መሰረታዊ ገፊ ምክኒያቶችን እናገኛለን፡፧

1ኛ ገዥዉ ፓርቲና በህገ መንገስቱ በፖለቲካ ፓርቲ መደራጀት መብት በዓይነትና ይዘቱ ያልተገደበ በመሆኑ ግለሰቦች ሲሻቸዉ በብሄራቸዉ ወይም ጎሳቸዉ ስም ያለዚያም በg'ንgቸዉ ስም በባህላዊ እሴታቸዉ ወይም በህብረብሄራዊ እንድነት ስም የመደራጀት መብት የሰጠ በመሆኑ በሀገሪቱ 23 ሀገር አቀፍና 65 በላይ የጎሳና የብሄር በድምሩ 94 የሚደርሱ ፓርቲዎች እንዲፈጠሩ አድር¹ል፡፧

2ኛ ፓርቲዎች በተለይ የተቃዋሚ ፓርቲዎች አመራሮች እርስ በርሳቸዉ በሚፈጥሩት አለመግባባት ችግሮችን የማስወገጃ ስልቶችን (conflict management strategies ) ከመጠቀም ይልቅ ኃላፊነት በጎደለዉ መልኩ በፍጥነት አዲስ ፓርቲ ማggምን አgራጭ መንገድ አድርገዉ በመዉሰዳቸዉ የመተዳደሪያ ደንብና ፕሮግራሙን እያባዙ ስም ብቻ በመቀየር አዲስ ፓርቲና አዲስ ሊቀመንበር ሆነዉ ይመጣሉ :: ይህም አስፈላጊ ያልሆኑ ፓርቲዎች ቁጥር እንዲበራከት ምክንያት ሆ[illegible]ል:: በዚህ መልክ አንዱ ሌላዉን ፓርቲ እየወለደ የመጣበትን መንገድ እናያለን::ለማሳያ ያህል መዐህድ አና የመኢአድ የልጅ ልጅ የሆኑትን ፓርቲዎች እንመልከት መጀመሪያ መዐህድ ነበር ከመዐህድ መኢአድ ኢዴፓ

መኢብን መኢዴፓ ወ.ዘ.ተ ከአንድነት ሰማያዊ እንዲሁም ከኢራፓ አትፓ ዕያሉ በዙ ተባዙ ሌሎች ፓርቲዎችም የብሄር ሆኑ ህብረ ብሄር በዚሁ መልኩ የተፈጠሩትን መቁጠር ቀላል አይሆንም::

3ኛ ፓርቲ ለማggም የሚያስፈልገዉ መስፈርት ለሀገር አቀፍ 1500 ለክልል ፓርቲዎች 750 የመስራቾች ፊርማ ከየክልሉ ማሰባሰብና የቢሮና የህጋዊ ኦዲትር መኖር ዋና ዋና ቀላል መስፈርቶች በመሆናቸዉ እንድ ጡረታ የወጣና ቀሪ ህይወቱን በፖለቲካ ፓርቲ ፕሬዝደንትነት ላሳልፍ ብሎ ያሰበ ጎበዝ 3 ወር ባልሞላ ጊዜ ዉስጥ ፓርቲ አgቁሞ አደባባይ ለመዉጣት የሚያስችለዉን እድል ቀላል በመሆኑ በዚሁ መልክ ለአደባባይ መዉጫ ያህል ብቻ በሊቀመንበር ደረጃ ብቻ የሚቆጠሩ ሽማግሌ ፓርቲዎች ቤቱ ይቁጠራቸዉ::

4ኛ የመድበለ ፓርቲ ስርዓት ዓለ ለማስባል ሲባል ብቻ ገዥዉ ፓርቲ እንዲበራከቱና የህዝብ ድምፅ እንዲከፋፈል በማድረግ ተቃዋሚዎች በምርጫ የማሸነፍ እድላችን አችንዲቀጭጭና ገዥዉ ፓርቲ ራሱን አዉራ ፓርቲ አድርጎ ለመቀጠል የሚጠቀምባቸዉ ስልቶች አላስፈላጊ ፓርቲዎች እንዲበራከቱ ከፍተኛ ሚና አበርክቶል::

እንግዲህ እነዚህ ሁሉ ፓርቲዎች የሚታገሉት ለህዝብ ነዉ ወይ ብለህ ስትጠይቅ ምላሽህ አይደለም የሚሆነዉንበት ምክንያት የፓርቲ አመራሮች አለመግባባታቸዉን የሚፈቱበት መንገድ አዲስ ፓርቲ ማggም ሆኖ በመገኘቱ ነዉ:: ለህዝብ የሚታገሉ ቢሆኑ ኖሮ እማ በአንድ አይነት ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ብዙ ፓርቲ ባልመሰረቱ ነበር::

አሁን ዋናዉ የኢትዮጵያ የተቃዉሞ ፖለቲካ ችግር ፓርቲ ማብዛት ሳይሆን የፓርቲዎችን ቁጥር በዉህደት ወይም በግንባርና ቅንጅት ቁጥሩን በማሳነስ ለመራጩ ህዝብ ዉስንና ጠንካራ አማራጭና ተፎካከሪ የሚሆኑ ፓርቲዊችን መመስረት ላይነዉ::የህዝቡም ጥያቄ እንደቅንጅት እንድ ሆናችሁ ተባበሩ ያለዚያም ተሰባበሩ››የሚል ወቅታዊ ጥሪ በአራቱም መዓዘን እያሰማ ነዉ::

ለኔ ዋንኛ ጥያቄ ግን ለመተባበር የትኛዉ ይቅደም የፓርቲዎች ዉህደት ወይስ ህብረት ይሁን የሚለዉ በአግባቡና በተጠና ሁኔታ መልስ ሊያገኝ የሚገባ ወሰኝ ጥያቄ ነዉ:: አንድነትና መኢአድ ይህን የህዝብ ጥያቄ ለመመለስና በምርጫም ዉጤት ለማስመዝገብ ዉህደት የተሻለና ቀዳሚ እርምጃ ነዉ ብለዉ ለዉህደት በሂደት ላይ ይገኛሉ:: በሌላ በኩል ደግሞ መደረክ ከመለስተኛ የጋራ ፕሮግራም በመዉጣጥ ወደ አንድ የግንባር ፕሮግራም በመለወጥ የፓርቲዎችን ህብረት ይዞ የተሻለዉ መንገድ ይህ ነዉ ብሎ በዉስጡ 4 ያህል የየራሳቸዉን ህልዉና ያላቸዉን ፓርቲዎች ይዞ በመታገል ላይ ይገኛል::

ዋናዉ ነገር ዉህደትም ሆነ ግንባር የትኛዉ ይበልጥ ዘላቂነትና ተፅእኖ ፈጣሪ በሆነ መልኩ የኢትዮጵያን የተቃዉሞ ትግል ወደ ስኬት ያደርሳል የሚለዉ ጥያቄ ሚዛን የሚደፋ ይሆናል::ለኔ ሁለቱም መንገዶች በጥልቅ ጥናት ላይ የተመሰረቱ የዉህደትን ሆነ ለግንባርነት የሚሳስፈልጉ መርሆችን ጠንቅቀዉ ያወቁና ካለፉት ዉህደት ሆነ የቅንጅት/ግንባር የዉድቀት ታሪካች የቀሰምናቸዉ ትምህርቶች ተለይተዉ ተይዘዉ ያንኑ ስህተት ላለመድገም የተደረገ ጠንካራ ስራ ካለ ሁሉትም መንገዶች ዉጤት ሊያመጡ የሚችሉበት እድል ሰፊ ነዉ ባይ ነኝ::

ነገር ግን ከኢትዮጵያ ፖለቲከኞችና ፓርቲዎች ግላዊ ስሜትና ፍላጎት አçያ የትኛዉን አደረጃጀት ይቅደም ? የፓርቲዎች ዉህደት ወይስ የፓርቲዎች ህብረት/ግንባር የሚለዉን ጥያቄ በጥንቃቄ ማየትና መፈተሽ ተገቢ ነዉ ብዬ አምናለሁ::

ማናኛዉም የፓርቲዎች የዉህደት ሆነ የህብረት ስራ ለመስራት በቅድሚ በጋራ ለመስራት ያሰቡት አካሎች የመጠናኛ ሰፊ ግዜ ያስፈልጋቸዋል:: ሌላዉ በጋራ ሊያታግላቸዉ የሚያስችል ቁልፍ የጋራ ዓላማ እና ይህኑ ዓላማ ለማስፈፀም የሚያስችል ተመጣጣኝ ሰዉ ኃልና የገንዘብና የቁሳዊ ሀብት ግኝት ሊኖራቸዉ ግድ ይላቸዋል:: በዚሁ መሰረት ለዉህደት ሆነ ለህብረት መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸዉ የምላቸዉን ሀሳቦች በማቅረብ የእንድነትና የመኢአድ የዉህደት ሂደትንና የመድረክን የግንባር ትግልን በቀጣዩ ለመቃኘት እሞክራለሁ::

ለፓርቲዎች ዉህደት ወሳኝ መስፈርቶች

1.ሊታገሉለት የተነሱበት ግልፅና ዋና የጋራ ዓላማን ለይቶ ማዉጣት

2.የራስን ና የፓርቲን ዉስጣዊና ግላዊ ፍላጎትን ለመግደል መወሰንና ለዉህዱ ፓርቲ ማሰብ

3.ዉህደቱ ስçር በዉሃ ወይም ጨዉ በዉሃ ዉስጥ ሲዋሃድ የሚያሳዉን ወጥነት መፈጠሩን ማረጋገጥ

4.ከዉህደት በኃላ ከዉህደት በፊት ወደነበሩበት ቅርፅና ይዘት መመለስ አለመቻሉን ማረጋገጥ

5.ከትግሉ ድል ሊገኙ የሚችሉ ህዝባዊ ማህበረሰባዊ እና ግለሰባዊ ጥቅሞችን አስቀድሞ መተንበይንና ማሳወቅ::

6. ፓርቲዎች ሲዋሀዱ አንዱ ሌላኛዉን አለመዋጡን ማረጋገጥና በሚፈጠረዉ አደስ ዉህድ ዉስጥ ሚዛናዊ ባለድርሻነት እንዲኖር ማደገረግን ይጠይቃል::

7.የቀድሞ የፓርቲዎች የዉህደት ስኬትና ወድቀት ትንታኔ በድንብ ተቀምሮ መቀመጥ አለበት

8.ሌሎች ለጊዜዉ ለኔ ያልታዩ ቁልፍ ጉዳዮችን ማካተትም ያስፈልጋል ::

እነዚህን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ የአንድነት እና የመኢአድ የዉህደት ሂደት እነዚህን መሰፈርቶች የትኞቹን በምን ያህል ጥልቀት የዳሰሰ እነደሆነ መፈተሽ ተገቢ ይሆናል ብዬ አምናለሁ::ከዚህ አçያ ሁለቱ ፓርቲዎች በግልፅ በጋራ የሚታገሉለትን ትልቁን ዓላማ ለይቶ የማዉጣት ችግር ይገጥማቸዋል የሚል ግምት የለኝም:: ነገር ግን በተራ ቁጥር ሁለት የተቀመጠዉን መስፈርት 60% እንçን ያሏሉ የሚል እምነት የለኝም::የኢትዮጵያ ፖለቲከኞችና ፓርቲዎች ዋንኛ መገለጫ የራስን ግለሰባዊና የፓርቲን ፍላጎት ገድሎ ለህዝብ ፍላጎትና ጥያቄ ምለሻሽ ለመስጠት የሚጠይቀዉን ዋጋ ለመክፈል፧ ያለን ዝግጁነት ጥያቄ ዉስጥ የሚገባ ነዉና::

ይህን በተጨባጭ ያየነዉ ጉዳይ በመሆኑ የአንድነትና መኢአድ ዉህደት ቀጣይ ፈተና ይህ መስፈርት ያለመሏላት አንድ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት አለኝ:: ለዘህ ስጋቴ ዋንኛ ምክንያት አንድ ፓርቲ ኬላ ፓርቲ ጋር ሲዋሀድ ቀደም ሲል ፓርቲዉ በግሉ የገነባዉ ስብእና ታሪክ (Reputation and constituency ) እይታዉን በአዲሱ ዉህድ ፓርቲ አዲስ ቅርፅና ይዘቱን (Brand ) የሚቀይር ወይም የሚያጣ በመሆኑ ይህን (Brand ) በቀላሉ አሳልፎ መስጠት ለፓርቲዎችም ሆነ ለፖለቲካ አመራሮች ቀላል ዉሳኔ ሆኖ አይገኝም. ምክነረያቱም ፓርቲ በቡዙ ዋጋ እንጂ እንዲሁ በመንገድ የሚገኝ ተgም አይደለም:: የቅንጅት ዉህደት አለመሳካት አንዱ ይህ ምክንያትን በዋናነት ሊቀመጥ የሚችል ጉዳይ ነዉ:: ዉሳኔዉ ቀላል የማይሆነዉ ፓርቲዎች መኢአድም ሆነ አንድነት የተመሰረቱበት ሂደት በየራሱ ብዙ ዉጣ ዉረድ ያለበትና የተከፈለ ዋጋም ያለዉ በመሆኑ ፓርቲዉን ህልዉና አጥፍቶ በሌላ አዲስ ቅርፅ ባለዉ ፓርቲ ዉስጥ ለመቀጠል መወሰን ብዙ ጊዜ አስቦ አንዴ መወሰንን የሚጠይቅ ከባድ ዉሳኔ በመሆኑ ነዉ::

ዉሳኔዉን የሚያፀናዉ ደግሞ አዲስ የሚፈጠረዉ ዉህድ ፓርቲ በተጨባጭ የሚያሥመዘግበዉ አዲስ ድልና የትግል ጥንካሬና የዉስጣዊ ሰላምና ዲሞክራሲያዊ ማእከላዊነት የመጠበቅ አቅሙ አሳማኝና ተስፋ የሚሰጥ ሆኖ ከተገኘ ብቻ ነዉ:: የአንድነትና የመኢአድ የዉህደት ጉዞ ከጅምሩ አስከ ቅድመ ስምምነት ያለዉን ሂደት ስንመለከት በብዙ መሰናክሎችና አስከ ድብድብ ያደረሰ ክስተቶች ተሞላ መሆኑ ወደፊት በዉህዱ ፓርቲ ዉስጥ ሊኖር ሚችለዉን ሰላም አንድነት የትግል ጥንካሬና ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ከወዲሁ ስጋትና ጥያቄ ዉስጥ የሚከት ይመስላል:: ይሁንና ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም እንዲሉ አንድነትና መኢአድ የቅርብ እይታቸዉን ሳይሆን ከተራራዉ ጀርባ እየፈነጠቀች ያለችዉን የፅሀይ ብርሃን ተሳፋ ባደረገ መልኩ ሁሉንም ጉልበታቸዉን ተራራዉን በመዉጣት ላይ ማስተባበር ይጠበቅባቸዋል ባይ ነኝ:: ይህን የምጠቅስዉ ቀድመዉ ያወቁት ችግር የመፍትሄዉ ግማሽ አካል ነዉ የሚለዉ መርህ በመነሳት ነዉ:: ሌላዉ ስጋት በኢትዮጵያ 94 ፓርቲዎች ባሉበት ሀገር የሁለት ፓርቲ ዉህደት የኢትዮጵያ ህዝብ ጥያቄን የመመለስ አቅም አለዉ ወይ ነዉ ጥያቄዉ:: የሁለቱ ብቻ ዉህደት የፓርቲዎች ብዛትን ሳይቀንስ አንድ ጠንካራ ስብስብ ፓርቲ የሚጫወተዉን ተፅእኖ የመፈጠር ሀይል ያመጣል ወይ የሚለዉ ሌላዉ ጥያቄ ሲሆን በሌላ አንግል መድረክ በፓርቲዎች የስብስብ ግንባር ሆኖ መቀጠሉ ሌሎች ፓርቲዎች ደግሞ በተናጠል ጉዞ ተፅእኖ ፈጥረን ነጥረን እንወጣለን ብለዉ የሚያስቡ መኖራቸዉ የአንድነትና የመኢአድን ዉህደት ተፅእኖ ፈጣሪነት ሚናዉን አያደበዝዝም ወይ የሚል ጥያቄ አለኝ ?

በሌላ መልኩ መኢአድ በዉስጡ ያልተፈቱ ብዙ የመከፋፈል አንጃዎች የእነ ማሙሸት አማረ ቡድን የእነ አቶ አሰፋ ሀብተወልድ ግሩፕ የእነ ያቆብ ልኬ ተከታዮች እና ዋናዉ የእነ አቶ አበባዉ መሀሪ ስራ አስፈፃሚ በመኢአድ ጉዳይ ላይ አንድ የደረሱበት የጠራ የጋራ መደምደሚያ ባለመኖሩ መኢአድ ከአንድነት ጋር ተዋህዶ ህልዉናዉን ሲያጠፋ አንጃዎቹ መኢአድ አልጠፋም ብለዉ ሊነሱና (Brand ) ን ይዘዉ የሚነቀሳቀሱ ቡድኖች ሊፈጠሩ እንደሚችል አልጠራጠረም ምክንያቱ መኢአድ በአgራጭ ሊሸጥ ነዉ የሚሉ አካሎች ብቅ ብቅ እያሉ ነዉና ::ይህ ከሆነ ደግሞ የሚፈጠረዉ አዲሱ የአንደንነትና የመኢአድ ዉህድ ፓርቲ ከመኢአድ ጥቂት አመራሮችን የወሰደ ልክ አንድነትና ብርህን ሲዋሃዱ ብርህን ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ በአንድነት ዉስጥ ተዉጦ አንድነት የነበረዉን ብራንድ (ስሙን ) እንçን የመቁየር ተፅእኖ ሳይደርስበት ዉህደት እንደፈፀመና ሁለቱ ፓርቲ መዋሀድ ቢያነስ በኢትዮጵያ ፖለቲካ አሰላለፍ ላይ ያመጣዉ አዲስ ተፅእኖ አለመኖሩን እንረዳለን:: ያዉ አንድ ጠንካራ ፓርቲ ሌላዉን ደካማ ፓርቲን መዋጥና ፓርቲዎችን ቁጥር ከ94 ወደ 93 ማዉረድ ከልሆነ በቀር ዉህደቱ ያስፈለገበት ቁጥር አንድ ዓላማ ተሳክቶል ወይ ብሎ መጠየቅ የቀጣዩን አንድነትና የመኢአድ የዉህደት ፋይዳ እስከምን ሊደርስ እንደሚችል መገመት ከባድ አይሆንም::

መኢአድና አንድነት ዉህደት ዉስጥ አዲስ ስምና ፕርግራም ቢለዉጡም የመኢአድ ሌሎች ያገባኛል ባዮች የመኢአድን (Brand ) ኀትተዉ ስለሚያስቀሩት አዲሱ ዉህድ ፓርቲ የአንድነትና የተወሰኑ የመኢአድ አመራሮች የሚስተዋሉበት ከመሆን ዉጭ የሁለት ነገሮች አዲስ ዉህድ ዉጤትና መልክ ልክ እንደ ሻይና ቡና (አስፕሪስ ) ብናና ወተት( መኪያቶ ) የመሆንና የማየት ችግሮች ከፊቱ ይደቀናሉ የሚል ስጋት አለኝ:: የአንድነትና የመኢአድ ዉህድት ወይ ነጭ መኪያቶ ወይም ጥቁር መኪያቶ በመሆን የአንዱ ጫና የበረታበት ሊሆን እንደሚችል እገምታለሁ:: ይህ አንዳይሆን ከተፈለገ እነ አቶ አበባዉ በመኢአድ ላይ ያገባናል የሚሉዋቸዉን እነ ማሙሸት አማረን ደ/ር ታዲዮስ እነ አቶ አስፋ ሀብተወልድ እነ አቶ ያቆብ ሌኬን እነ አቶ ማህተመ እና እነ ዶክተር በዛብህን ወዘተ በማሳተፍና በማወያየት ለአዲሱ ዉህድ ፓርቲ አዎንታዊ ሚናና ድርሻ እንዲኖራቸዉ ካልተደረገ በስተቀር የአንድነትና የመኢአድ የዉህደት ሂደት ብዙ ፈተናና ዉጣ ዉረድ የበዛበት እንደሚሆን ስጋት አለኝ::

ሌላኛዉ ስጋት በቁጥር 3 የተቀመጠዉ መስፈርት ሲሆን ዉህዱ ፓርቲ ከዉህደት በኃላ የሚያሣየዉ ቅርፅ ስçር ወይም ጨዉ ዉሃ ዉስጥ ሲJJ የሚኖረዉን ወጥ የሆነ ቅርፅ በአንድነትና በመኢአድ የዉህደት ቅርፅ ዉስጥ ይታያል ወይ የሚል ግምቴ የመነመነ ነዉ::ምክንያቱም ሁለቱ ፓርቲዎች ወደታች ያላቸዉ መዋቅር ይዘት በጣም የሚለያይ ከመሆኑ የተነሳ በመኢአድ ሰፊ መዋቅሮች መኢአድ ጎልቶ የሚወጣበትና የዉህዱን ቅርፅ ሳይሆን የነባሩን ቅርፅና ይዘት ሣይለቅ ሚያንፀባርቅበት እድል ሰፊ ሲሆን በተመሳሳይ አንድነትም እንዲሁ በሌሎች ቦታዎች የራሱን ቅርፅ ጠብቆ የሚቀይበትን ሂደት የመፈጠሩ ሁኔታ ሰፊ ነዉ የሚል ግምት አለኝ :: ይህ አይነት ክስተት ደግሞ ዉህዱን ፓርቲ ረጅም ርቀት እንዳይ¹ዝ መሰናክል እንዳይፈጥርበት ስጋት አለኝ::

በተራ ቁጥር 4 የተቀመጠዉ መስፈረት በተመለከተ የሚዋሃዱ ፓርቲዎች በዉህደት ስምምነታቸዉ ዉሥጥ ከተዋሃዱ በኃላ በአመራሮች መካከል በሚፈጠር አለመግባባት ምክንያት ወደ ቀድሞ የፓርቲዉ ይዘትና ቅርፅ መመላስ በማያስችል አንቀፅ መደንገግ አለባቸዉ :: እንደ ህገመንግስታችን አንቀፅ 39 በአንድነትና በእኩልነት መኖር ካልተመቸኝ የራሴን እድል በራሴ እዉስናለሁ የሚልና ይህን አይነት እድል የሚሰጥ የዉህደት ስምምነት መቀመጥ የለበትም ፡፧ ሁለቱም ፓርቲዎች ከዉህደቱ በኃላ የቀድሞ ህጋዊ ስዉነት የፓርቲ ምዝገባ ሰርተፊኬታቸዉን ለምርጫ ቦርድ በሚመልሱበት አስራር ላይ መስማማት ይጠበቅባቸዋል:: ይህ ከሆነ በአመራሮች መካከል በሚፈጠር አለመግባባት ፓርቲ ይገፔ እኤዳለሁ የሚል አካል እንዳይፈጠር የማድረግ ሚና አለዉ::

ሌላኛዉ መስፈርት ቁጥር 5 ላይ የገለፅኩት ከዉህዱ ፓርቲ ቀጣይ ትግል የሚገኙ ድሎችና የሚገኙ ህዝባዊና ግለሰባዊ ጥቅሞች ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ብቻ ሳይሆን የሆኑና ተሳኩ ያህል የሚሰማ ስነልቦና መገንባት ያስፈልጋል:: የሚወሀዱ ፓርቲዎች በዉህዱ ፓርቲ የሚያገኙትን ድል እንደሚያገኙት ወይም እንደአገኙት እርግጠኝነት ካልተሰማቸዉና ይህን ስነ ልቦና ሳያደብሩ ቀድሞ የነበራቸዉ ፓርቲ ዉስጥ ያጡትን ነገር የሚያሰላስሉ ከሆነ አዉህደቱ አደጋ አለዉ:: ለምሳሌ ሁለት ፓርቲዎች ከዉህደት በፊት ሁለት ፕሬዝደንት/ሊቀመንበር አሉ በዉህዱ ደግሞ አንድ ሊቀመንበር ብቻ መኖሩ ግድ ይላል ስለዚህ አንዱ ቀድሞ የነበረዉን ስልጣን በዉህደቱ ምክንያት ማጣቱን የሚያብሰለስል ከሆነ የዉህዱ ፓርቲ ስኬታማነት ጥያቄ ዉስጥ ይገባል:: ይህ እነዳይሆን በተበታተነ ትግል የፓርቲ ልቀመንበርነት እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብን የነፀነትና የድል ባለቤት ማድረግ አለመቻሉን መረዳትና በዉህዱ ፓርቲ በሚጎናፀፈዉ ህዝባዊ ስልጣን ዉስጥ ሊኖር የሚችለዉን የተትረፈረፈ የስልጣንና አመራር ቦታዎች መኖራቸዉን አርቆ ማሰብ እንዲችሉ የማድረግ ስነልቦና ግንባታ ስራ ማስረፅ ለሚዋሀዱ ፓርቲዎች ጥንካሬ ቁልፍ መሳሪያ ነዉ::

ሌላዉ በቁጥር 7 መስፍርት ላይ ተቀመጠዉ የቀድሞ ዉህደትና ህብረት ቅንጅት ዉድቀትና ስኬት ጀርባ ያሉ መረጃዎችና ሁኔታዎች በሚገባ ተንትኖ ያስቀመጠ ዶክመንት መዘጋጀት አለበት:: በእዉን የአንድነትና መኢአድ ዉህደት ሂደት ይህን መስፈርት በግልፅ የተተነተነ ተጨባጭ ጥናትና ዶክመንት ይዘዉ ይሆን ወደ ዉህደቱ ሂደት የገቡት? የትንተና ዶክመንቱ ካለ መልካም ይህ ዶክመንት ከሌለ ግን አሁንም ከዉድቀታችንና ስኬታችን ምንም ተመክሮ ያልወሰደ ዉህደት ስለሚሆን ስህተትን ለመድገም ሰፊ እድል ያለዉ ሆኖ እናገኘዋለን፡፧ ህብረት ከመፍጠር አçያ ቅንጅትን ዉድቀጥና ስኬት በመተንተን የፓርቲዎች ዉህደት ወይስ ቅንጅት ይቀደም የሚለዉን ለመተንተን ሰፊ አድል ይሰጠዋል:: አንድነትና መኢአድ ዉሕደት ወይስ ህብረት ብለዉ ሲወስኑ የቅንጀት ታሪክ ወይም መድረክን ታሪክ ተንትነዉ መሆን አለበት ፡ያለበለዚያ ዉህደት ከህብረት መሻሉን እንዲሁ ህዝብ ተባበሩ አንድ ሁኑ ከሚለዉ ጥቅል እሳቤ ተነስተዉ ከሆነ የዉህደት ሂደቱ የአፋፍ ላይ ጨዋታ ከመሆን አይልፍም::

ዉህደት ጥቅምን ከህብረት ይልቅ ቀዳሚ ነዉ ብለዉ ሲወስኑ ደግሞ አሁንም የአንድነትና ብርህን ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ዉህደትን ታሪክ ስኬትና ዉድቀት ተንትነዉ ከዚያ በተገኘ ተጨባጭ መረጃና ትምህርትን መሰረት ያደረገ መሆን ይገባዋል ባይ ነኝ፡፧ አንድነት ከብርሃን ጋር መዋሃዱ ምን አተረፈ ምን አጣ ብርሃን ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ፓርቲ ከአንድነት ጋር በመዋሃዱ አመራሩና ፓርቲ ምን አተረፉ ለኢትዮጵያ ህዝብስ ምን አዲስ ክስተት ፈጠሩ የሚለዉ የተተነተነ መሆን አለበት ፡፧ የብርሀን ፓርቲ አመራሮች ትናንትና ዛሬ ለፖለቲካዉ ትግል ያበረከቱት አዎነታዊ ሚና (synergy ) ምንድን ነዉ? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፧ ለምሳሌ ብርሃን ከአንድነት ጋር ሲዋሃድ የሆነዉ ነገር አቶ ሙላት ጣሰዉ የብርሃን ፓርቲ ሊቀመንበር ኢንጂነር ዘለቀ ረዲ የብርሃን ፓርቲ ም/ሊቀመንበርን በአዲሱ ዉህድ ፓርቲ ዉስጥ ቁልፍ ሚና በስራ አስፈፃሚና ልአላይ ምክር ቤት አባል ዉስጥ እንዲኖር ማድረጉ ይታወሳል :: ይሁንና ኢንጅነር ዘለቀ ረዲ ከዶክተር ነጋሶና ስራ አስፈፃሚዉ ጋር በፈጠሩት አለመግባበት በሰንደቅ ጋዜጣ ላይ ‹‹በቃኝ!›› በማለት የሰጡትን ኢነተርቪዉ ያነበበ ሰዉ በእርግጠኝነት የብርሃን ፓርቲ ዉህደት አመራሮችን በአዲሱ ዉህድ ፓርቲ ዉስጥ ለስልጣን የማብቃት ካልሆነ በስተቀር ለተሳካ ትግሉ ትልቁን ዓለማ መሰረት ያደረገ ነበር ለማለት ይከብዳል፡፧ ኢንጂነር ዘለቀ በደፈናዉ ፖለቲካ በቃኝ ቢሉ ደስ ባለኝ ነበር ነገር ግን የተዋሀዱትን አንድነትን ፓርቲ አመራርን የአምባነን ስብስብ ነዉ :: ‹‹ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣም ሌላዉ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ነዉ›› ብለዉ በአደባባይ ሲተቹ ዉህደቱ ፋይዳዉ ይሄ ነዉ ብዬ በወቅቱ አዝኜ ነበር:: ምክንያቱም ሁለቱ ሲዋሃዱ በክብር እንግድነት ተገኝቼ ነበርኩኝና ኢንጂነር ዘለቀ በደ/ር ነጋሶ ተሸንፈዉ ሽንፈታቸዉን በፅጋ መቀበላቸዉን ለማረጋገጥ ያቀረቡትን ንግግርና የሙገሳ ፁሁፍ የሰማ ሰዉ እና በኃላ ኢንጂነሩ ዶክተሩን በሰንደቅ ጋዜጣ የገለፅበት g'ንgን ያየ ሰዉ እንዲሁም ዶ/ር ነጋሶ የኢንጂነሩን ፖለቲካ ብቃት የገለፅበትና እከሰዋሉ ማለታቸዉን የሰማ ሰዉ የፓርቲዎች ዉህደት መዳረሻዉ እስከምን ሊሆን እንደሚችል መገመት ቀላል ነዉ::

አሁን ደግሞ ዶ/ር ነጋሶ ስልጣናቸዉን ሲያጠናቅቁ ልክ እንደ ኢንጂነር ዘለቀ ረዲ ሁሉ በተራቸዉ ‹ፖለቲካ በቃኝ! › አሉን ኢንጂነሩም በቃኝ ያሉት ተመልሰዉ ወደ ፖለቲካዉ ገቡና አሁን አንድነት ዉጭ ግንኙነት ኃላፊ ሆነዉ እየሰሩ ነዉ፡፧ እንግዲህ ይህ የሚያሳየን ሲንዋሀድም ሆነ ህብረት ሲንፈጠር በቁጥር አንድ የተቀመጠዉ ትልቁ ዓላማ ምንድን ነዉ የሚለዉ ላይ የጠራ ምልከታ አለመኖር ወይም ተለጣፊ ዓላማ መሸከም ለዚህ መሰል ምስቅልቅል ጉዳይ መደራጉ አይቀርም ስለዚህ የአንድነትና የመኢአድም ዉህደት በዚህ መልኩ ከቀድሞ ዉህደትና ህብረት ስኬትና ዉድቀት ትንታኔ የተማረና ያንን መነሻ ያደረገ መሆን አለበት የሚል መልእክት ማስተላለፍ እፈልጋለሁ፡ ፧በቀጣዩ ፅሁፌ ፓርቲዎች ህብረት/ቅንጅት ወይም ግንባር ለመፍጠር ምን መስፈረርቶች ማዉጣት እንዳለብን ከዉህደት በፊት ህብረት .ግንባር የሚያስገኛቸዉን ጥቅሞች የምዳስስበት ፅሁፍ ለማቅረብ እሞክራለሁ ፡፧ እስከዚያዉ ቸር እንሰንብት ::

ህግና ማኅበረሰብ

በሽንቁጥ አየለ (shenkutayele@yahoo.com)

# በትምህርት ተቋማት የሚሰጡት የትምህርት ማስረጃዎች በልህቀት ማዕከሉ (OCACC) ዋጋ ማጣታቸዉ ምን ያህል ህጋዊ ነዉ ? የብቃት ምዘናው COC በህግ ዓይን

በአንዲት ሀገር ዉስጥ ትምህርት ለዕድገት: ለሥልጣኔ : ለምርምር : የዜጎችን ሕይወት ለማሻሻል : ተወዳዳሪ ለመሆን እንዲሁም የበለጸገና ገቢዉ ከፍ ያለ ማህበረሰብ ለመፍጠር ያስችላል:: ሆኖም የትምህርትን ሙሉዕ እምቅ አቅም በአግባቡ አሟጦ ለመጠቀም የትምህርት ስርዓቱ በሕግ መመራት አለበት:: እንደሚታወቀዉ የህግ ጽንሰ ሀሳብ መፍሰሻና መድረሻ ዘርፋቸዉ ብዙ ሲሆን ከነዚህም ዋና ዋና የሚባሉት መንፈሳዊ የህግ ጽንሰ ሀሳብ አቀንቃኝ ዘርፍ: አባታዊ የህግ ጽንሰ ሀሳብ አቀንቃኝ ዘርፍ: ስምምነት ተኮር የህግ ጽንሰ ሀሳብ አቀንቃኝ ዘርፍ እንዲሁም የስነልቦና የህግ ጽንሰ ሀሳብ አቀንቃኝ ዘርፍ ተብለዉ ሊከፈሉ ይችላሉ:: ሆኖም በዚህኛዉም ሆነ በዚህያኛዉ ጠርዝ ያለ የህግ ጽንሰ ሀሳብ አቀንቃኝ ዘርፍ ዋና ግቡና አንደምታ አድርጎ የሚያጠነጥነዉ ለማህበረሰባዊ ሁል አቀፍ ተጠቃሚነት ነዉ::

በአጠቃላይ ለሕግ መፈጠር ዋና ዋና ምክንያቶቹ እንደሆኑ የሚጠቀሱት ጉልህ ጉዳዮች የኑሮ ደረጃ ማደግ፣ የጥንቱ የጋርዮሽ ሥርዓት መፈራረስ፣ የግል ንብረት መፈጠር፣ እዲሁም የንብረተሰብ የማህበረሰባዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታዎች መዛባት ብሎም አጠቃላይ የማህበረሰብ ብልጽግና ታሳቢዎች እየጎለመሱ መምጣት ናቸዉ:: የህግን አጀማመር በኢትዮጵያ ስንመለከትም አንዳንዶች እንደሚሉት መነሻዉ ፍትሃ ነገስት ነዉ ይላሉ:: ይሄም ማለት ፍትሐ ነገሥት በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ተቀነባብሮ የተፃፈ ሕግ ሲሆን ከ1426-1460 በአፄ ዘርዓያ ዕቆብ ዘመነ መንግሥት ይሆንንና ከ500 ዓመታት በላይ አገልግሎት አበርክቷል ማለት ነዉ::

ሆኖም በኢትዮጵያ ጥንታዊነት ስልጣኔ ላይ የማያወላዳ አቋም የያዙ ምሁራን እንደሚተነትኑት የተራቀቁ ህጎች በኢትዮጵያ ከሙሴ ዘመን በፊት እንኳን ይሰራባቸዉ ነበር ይላሉ:: ለዚህ ማጣቀሻም ኢትዮጵያዊዉ ዮቶር የሴት ልጁን ባል ሙሴን ስለ ፍርድ ህግ እንዲሁም ስለ ህዝብ አመራር ህግ ያስተማረበትን ጥንታዊ የመጽሀፍ ቅዱስ ክፍል በማጣቀስ ያቀርባሉ:: ይሄም ማለት ኢትዮጵያዉያን በዚያን ዘመን የራሳቸዉ የህዝብ አስተዳደር ህግና የፍርድ ህግ እንደነበራቸዉ ያሳያል ሲሉ አበክረዉ ይገልጻሉ:: ያም ተባለ ይህ ህግ በኢትዮጵያ ያለዉ ታሪካዊ ሂደቱን በመጠበቅ አሁን አለበት ደረጃ ላይ ደርሷል:: ይሄንኑ ታሪካዊ ሂደት ተከትሎም በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በተፃፈ ሕግ የሚመራ ሥርዓትን መመስረቱ ይታወቃል::

ኢትዮጵያ በተፃፈ ሕግ (Civil Law Legal System) በመባል የሚታወቀውን የሕግ ሥርዓት የምትከተል ሲሆን በተጨማሪም በፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት የሚወሰኑ ውሳኔዎችም እንደ ሕግ እየተቆጠሩ በሥራ ላይ እየዋሉ ናቸው:: ሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ሀገርን ለመምራትና ለማስተዳደር የሕግ መኖር ወሳኝ እንደመሆኑ መጠን በሁሉም የስራ መስኮች ዘርፍም ዝርዝር እና ግልጽ ህግ መኖሩ እጅግ ወሳኝና ቁልፍ የብልጽግና ሂደት አካል ነዉ:: ህግ በሌለበት ማኅበረሰቡን መምራት ካለመቻሉም በላይ ማህበራዊ ቀዉስ መፈጠሩ የታመነም የታወቀም ነዉ:: ጆን ሎክ እንደሚለዉ ማህበረሰብም ሆነ ግለሰብ አለ ህግ የሚኖር ከሆነ ህገ አራዊትነትን ይከተላልና::

ስለሆነም ሰላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ሀገርን ለመምራት ሕግ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ የሕግ አውጭው የሚያወጣቸው ሕጎች ተፈፃሚ እንዲሆኑ የወጡበትን አላማ እንዲያስፈጽሙ ሆነው መውጣታቸው ጠቃሚ ነው:: እንደሚታወቀዉ ሶስቱ የመንግሥት ዘርፎች ( የሕግ አውጭዉ : ሕግ አስፈፃሚዉና ሕግ ተርጓሚዉ) ተናበዉ : ተቀናጅተዉና የየስራ ድርሻቸዉን በአግባቡ መወጣት የሚችሉበት ስርዓት በአንዲት ሀገር ዉስጥ ካልተዘረጋ የሀገር ብልጽግና የማህበረሰብ እርካታ ከቶም የሚታሰብ አይሆንም::

በአንዲት ሀገር ዉስጥ እንደሚታወቀዉ የሕግ አወጣጥ ሥርዓቱ የሚከተለዉን ፍሰት ይከተላል:: የበላይ ሕግ የሆነዉ ሕገ መንግሥት : በሕግ አውጪ የሚወጡ አዋጆች: በሕግ አውጭ በተሰጠው የሥልጣን ገደብ ውስጥ የሕግ አስፈፃሚው የሚያወጣው ደንብ እንዲሁም የሕግ አስፈፃሚው በሚሰጠው ውክልና መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚረዱ መመሪያዎችን የሚያወጡ ተቋማት የሚያወጧቸዉ ህጎች በየደረጃቸዉ ቅደም ተከተላዊ ገዥነት አላቸዉ:: ይህም ማለት አንድ ህግ ሲወጣ ከሕገ መንግሥት ጋር የማይቃረን : ከፌዴራል መንግሥትና ከአዋጆች ጋር የተሰናሰነ (የተጣጣሙ: የሚናበቡ : የማይጋጩ: ወጥነት ያላቸዉ) : ቀጣይነት ያለው : የተፈፃሚነት ወሰኑ ግልጽ የሆነ እንዲሁም ግልፅነት ያለዉ መሆን አለበት::

ለመንደርደሪያ ያህል ከላይ የተነሱትን ሀሳቦች ከጠቃቀስኩ ዘንዳ ለዛሬ ወደ ማተኩርበት ጭብጥ ልለፍ:: ዋናዉ የዛሬ ርዕሰ ጉዳይ የሚያጠነጥነዉ በአዋጅ የተቋቋሙና ሕጋዊ እውቅና ያላቸው የትምህርት ተቋማት የሚሰጡት የትምህርት ማስረጃ በልሕቀት ማዕከሉ ሕግ የተነሳ ዋጋ ማጣታቸዉ ምን ያህል ህጋዊ ነዉ ? የሚለዉን ጥያቄ ለመዳሰስ ይሞክራል:: ከዚሁ ጋር በተያያዥነትም የአዲስ አበባ መስተዳድር ያቋቋመዉ የልህቀት ማዕከል ደንብ እራሱ ህጋዊ መሰረቱ እስከምን ድረስ ነዉ የሚለዉን ጥያቄ ለመመለስ እሞክራለሁ:: እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስም አዋጆችን: ደንቦችን: መመሪያዎችን ለመዳሰስ ተሞክሯል:: ለዚህ ጽሁፍ ግብዓትነት ያገለገሉ ህጎችን ዘርዘር አድርጎ ለማቅረብ ያህል:-

1.በፌዴራሉ ፓርላማ የወጣው የከፍተኛ ትምህርት አዋጅ

2.በፌዴራሉ ፓርላማ የወጣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና አዋጅ

3.የሲቪል ሰርቪስ አዋጅ፣

4.የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የልህቀት ማዕከል ደንብ፣

5.የፓርላማ የሕግ አወጣጥ ሥርዓት አዋጅ 14/1988

6.የፌዴራሉ ፓርላማ ያወጣው የአዲስ አበባ መስተዳድር ቻርተር

7.የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነው ሕገ-መንግሥት ናቸው::

እንደሚታወቀዉ የአንዲት ሀገር ህጎች የሚጣጣሙ የሚናበቡ የማይጋጩ የማኅበረሰቡን ዕድገት ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ብሎም ችግር ፈቺ መሆን አለባቸዉ:: በግልጽ እንደሚታወቀዉ ሕግ የማውጣት ሥልጣን በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 55 የተሰጠው አካል ሕግ አውጭ ማለትም የፌዴራሉ ፓርላማ የሕግ አወጣጥ ሥርዓት ደረጃ በምን መልኩ መከናወን እንዳለበት ተደንግጓል:: በአዋጅ ቁጥር 14/1988 የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ አወጣጥም በስራ ላይ ውሏል:: ተመራጭ የሆነ የምክር ቤት አባል ጥያቄ በ20 የምክር ቤት አባላት ፊርማ መደገፍ፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የሕግ ረቂቅ ለምክር ቤት በማቅረብ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 51 ከተሰጡት ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም በአንቀጽ 50(9) ለክልሎች ውክልና ሲሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል:: የሕግ አስፈፃሚው ሕግ አውጪው ሳያውቅ ባልተሰጠው ሥልጣን ሕግ የማውጣት ምንም ሥልጣን የለውም ቢወጣም ፈራሽ ነው የሚል ግልጽ ህግም ተደንግጓል:: እንዲሁም በሕግ አውጭውም ሆነ በሕግ አስፈፃሚው የወጡ ሕጎችን የመተርጎም ሥልጣን የሕግ ተርጓሚው ሥልጣን እንደሆነ ተደንግጓል:: የሕግ ተርጓሚው የሚቃረኑ ሕጎችን የመተርጎም ሥልጣን እንዳለውም ሳያወላዳ ተደንግጓል::ከዚህም በተጨማሪ ሕገመንግሥትን የመተርጎም ሥልጣን የፌዴሬሽን ምክር ቤት እንደሆነ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 62(1) ተደንግጓል::

በዚህ መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ ልህቀት ማዕከል የተቋቋመበት የሕግ መሠረት ምን ይመስላል? የሚለዉ ጥያቄ የሚከተሉትን ህጎች መሰረት በማድረግ ሊመለስ ይገባዋል:: የከፍተኛ ትምህርት አዋጅን እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አዋጅን እንዲሁም አዋጅ ቁጥር 391/1996 በተቋቋመው ጽሕፈት ቤት ጋር ያለውን ግንኙነትና ልዩነት ሲፈተሽ ነገሩ ግልጽ ይሆናል:: ከሁሉ በፊት መመለስ ያለበት የልሕቀት ማዕከሉ በማን ተቋቋመ የሚለዉ ጥያቄ ነዉ:: እንደሚታወቀዉ የልህቀት ማዕከሉን ያቋቋመው አዲስ አበባ መስተዳድር ሲሆን ይህን ማዕከል የማቋቋም ሥልጣንስ አለው ወይ የሚለዉ ጥያቄ ይከተላል? ማዕከሉ በአዲስ አበባ መስተዳድር የተቋቋመው በደንብ ቁጥር 1/2000 ሲሆን ይህ አሰራር ከሌሎች የፌዴራሉ ፓርላማ አዋጆች ጋር ሲታይ ምን ያህል ህጋዊነት አለዉ ብሎ መጠዬቅ ተገቢ ነዉ::

እነዚህን ጥያቄዎች ለመመለስ ሰፋ ያሉ ጉዳዮችን መዳሰስ ተገቢ ነዉ:: የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የተቋቋመበት አዋጅ በተሻሻለው ቻርተር

361/1995 ሲሆን የከተማው የበላይ ሕግ አውጪም በአንቀጽ 14 መሠረት ምክር ቤቱ እንደሆነ ተደንግጓል:: ይሄም በምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ስር ተዘርዝሮአል:: ሆኖም በዚህ በተዘረዘረው አዋጅ/ህግ የማውጣት ሥልጣኑ ሥር የልህቀት ማዕከልን ስለ ማቋቋም የተሰጠ ሥልጣን አንድም ቦታ የለም:: ምክር ቤቱ አዋጆችን/ ህጎችን እንዲያወጣ የተሰጠው ሥልጣን በዝርዝር የተቀመጠለት በመሆኑ የሚያጠራጥር አንቀጽም የለም:: ይሄም ማለት ፓርላማው በሰጠው ሥልጣን ሥር የልህቀት ማዕከልን ስለ ማቋቋም የተሰጠ ሥልጣን ከቶም አልተጠቀሰም:: ይሄን ለማጣራት የሚፈልግ ማንም አካል በቻርተር 361/1995 በአንቀጽ 14 ስር የተደነገጉትን ሕጎች ማየት ይችላል::

ያም ሆኖ ደንብ ቁጥር 1/2000 ን ያወጣው የከተማው ካቢኔ በአዋጅ 361/1995 አንቀጽ 23/1/ረ ን በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት እንደሆነ በመጥቀስ ቢገልጽም ይህ አንቀጽ ግን በከተማው ምክር ቤት በሚወጡ አዋጆች ላይ በሚሰጠው ሥልጣን መሠረት ደንቦች እንደሚያወጣ ይደነግጋል እንጅ ፈጽሞ የልህቀት ማዕከልን ስለ ማቋቋም የሚጠቅሰዉ ጉዳይ የለም:: ከዚሁ ጋር ሲጎተት የሚመጣዉ ጉዳይ ደግሞ ደንብ ቁጥር 1/2000 ከወጣ ብኋላ አዋጅ ቁጥር 4/2000 ደንቡን ለማሻሻል ወጥቶአል:: ይህም ደንብን ለማሻሻል አዋጅ መውጣቱ ተገቢነት የለውም:: የከተማው ካቢኔ አዋጅ የማውጣት ሥልጣንም አልተሰጠውም::

አንዳንድ ባለስልጣናት ይኸንን አይነት አሰራር የሚፈቅድ ሕግ እንደሌለ ሲጠዬቁ በሥራ ሂደት ወቅት የሚገጥሙትን ችግሮች ለመፍታት አዋጅ ከመጠበቅ ይልቅ ደንብና መመሪያዎች አውጥቶ ወደ ሥራ መግባት ይቀላል በማለት ምላሽ ከመስጠት ሌላ የሕግ መሠረቱን አያስረዱም:: የልህቀት ማዕከሉ የሚሰጠው አገር አቀፍ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ከትምህርት ሚኒስቴር ዉክልና ስላለዉ መሆኑን በደንብ ቁጥር 1/2000 በአንቀጽ 6(3) ይጠቅሳል:: ሆኖም ትምህርት ሚኒስቴር ለማዕከሉ የዉክልና ስልጣን የሰጠበት ህግ አንድም ቦታ የለም:: ትምህርት ሚኒስቴር ውክልና ለልህቀት ማዕከሉ ሰጥቷል ከተባለም የልህቀት ማዕከሉ ደንብ ሲቋቋም የቻርተሩን 231/2/ረ ሳይሆን መጥቀስ የነበረበት የሚኒስቴሩን ውክልና ጠቅሶ መውጣት ነበረበት:: ይሄም ማለት ማዕከሉ ባልተሰጠው ሥልጣን የሚሰጠው የትምህርት ማስረጃ የሕግ መሠረት የለውም ወደ ሚል ድምዳሜ ያደርሰናል::

የፌዴራሉ ፓርላማ በአዋጅ 650/2001 አንቀጽ 8 የትምህርት ማስጃዎችን የመስጠት ኃላፊነት ለትምህርት ተቋሚት ሰጥቷል:: ሆኖም ይህን ለትምህርት ተቋማት የተሰጠውን ስልጣን የልህቀት ማዕከሉ ቀምቷቸዋል:: ምንም እንኳን የትምህርት ተቋማት "ከነሙሉ ክብሩ፣ ጥቅሙና ግዴታዎቹ ይህ የትምህርት ማስረጃ ሰጠን" ብለዉ ቢያዉጁም አሁን ባለዉ ሁኔታ አንድ ከትምህርት ተቋማት ይሄን የትምህርት ማስረጃ ያገኘ ተማሪ የልህቀት ማዕከሉ ያወጣዉን ፈተና አላለፍክም ተብሎ የስራም ሆነ ቀጣይ ትምህርት የማግኘት ጥቅሙ ዉድቅ ሲሆንበት ይስተዋላል:: እና የትምህርት ተቋማት ዲፕሎም አስጨርሻለሁ ወይም ዲግሪ አሲዣለሁ በማለት "ከነሙሉ ክብሩ፣ ጥቅሙና ግዴታዎቹ ይህ የትምህርት ማስረጃ ተሰጠ" ብለዉ በህጋዊነት የሚሰጡት የትምህርት ማስረጃ ዉድቅ ተደርጎ አንድ ተማሪ ባገኘዉ የትምህርት ማስረጃ ሊያገኘዉ የነበረዉ ቀጥተኛ ጥቅም ተገድቦበታል::

የፌዴራሉ ፓርላማ ሙሉ ስልጣን በሰጠዉ በትምህርት ሚኒስቴር ስር ያሉ ሙሉ የትምህርት ማስረጃ የመስጠት ስልጣን ያላቸዉ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አዋጅ 650/2001 አንቀጽ 8 የሰጣቸዉ ስልጣን በልህቀት ማዕከሉ ተነጥቋል:: ከዚህ በተጨማሪም የተማሪዎች የምዘና ሥርዓትም በዚሁ አዋጅ 650/2001 አንቀጽ 41(ረ) በተማሩበት ተቋም መሆኑን ያሳያል:: ለምሳሌ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ሥርዓትን ለማደራጀት የወጣዉ አዋጅ ቁጥር 391/1996 አንቀጽ 45/1/ የሥልጠና ማጠናቀቂያ ማስረጃ አይነቶች አሰጣጥ ላይ የሚከተልዉን ይላል:- ሥልጠናውን የሰጡ ተቋማት በሚሰጧቸው ምዘና መስፈረት ሲረጋገጥ የትምህርት ማስረጃ ይሰጣል ይላል:: ሆኖም ይህ በአዋጅ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ተቋማት የተሰጠ ስልጣን በልህቀት ማዕከሉ ተነጥቋል:: ለዚህ ማረጋገጫዉም በአሁኑ ሰዓት አንድ ተማሪ ከቴክኒክና ሞያ ተቋማት የትምህርት ማስረጃ ቢያገኝም የትምህርት ጥራት ማዕከሉ የሚያወጣዉን ፈተና እስካላለፈ ድረስ በቀጣይ ትምህርት መማር አይችልም እንዲሁም የስራ እድሉም መንምኗል::

በዙሁ አዋጅ 650/2001 አንቀጽ 45(1) የመካከለኛ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ኘሮግራሞች ማጠናቀቂያ ማስርጃዎች በአገር አቀፍ ደረጃ እኩል ተቀባይነት ይኖራቸዋል የሚለውን የአዋጁን ሕግ በመጣስ ሌላ አገር አቀፍ ማስረጃ ከትምህርት ልህቀት ማዕከሉ አስፈላጊ እንደ ሆነ ሁሉ ሲሰራበት ይስተዋላል:: በአዋጁ አንቀጽ 47(5) የሙያ ብቃት ምዘና ለሚያልፉ ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ የሚሰጠው ከሚኒስቴሩ ወይም ከሚወክለው አካል ይሆናል ይላል:: ሆኖም የትምህርት ልህቀት ማዕከሉ ከትምህርት ሚስኒስቴር ዉክልና የወሰድበት ህግ የለም:: በአንቀጽ 47 እንደተደነገገውም ትምህርት ሚኒስቴር አገር አቀፍ የብቃት ምዘና ሥርዓት መመሪያ የሚያወጡና ምዘና የሚሰጡ ተቋማትን እንደሚያደራጅ በአዋጅ ስልጣን ተሰጥቶ እያለ የልህቀት ማዕከሉ ግን በትምህርት ሚኒስቴር ሳይቋቋም ወይም ዉክልና ሳይኖረዉ የትምህርት ጥራት ላይ ይሰራል::

ብሎም በትምህርት ሚኒስቴር እዉቅና የተቋቋሙ ተቋማት የሚሰጧቸዉን የትምህርት ማስረጃዎች የኔን ፈተና ተማሪ ካላለፈ በማለት የትምህርት ማስረጃዉን ከጥቅም ዉጭ ያደርገዋል:: ይሄም የትምህርት ሚኒስቴርን ስልጣን መጋፋት ከመሆኑም በላይ በሌለዉ ስልጣን የህጋዊ ተቋማትን ስልጣን መንጠቅ ነዉ:: በአጠቃላይም ከተፈጻሚነት ወሰኑ ጭምር በመዉጣት የልህቀት ማዕከሉ የበላይ ሕጉን ለመሻር ሲንጠራራ ይስተዋላል:: ከዚህ በተጨማሪም ከፌዴራል ትምህርት ሚኒስቴር ሙያ ትምህርት ሥልጠና ዘርፍ ጽ/ቤት ጋር የመጣረስ ሁኔታ ይታይበታል:: በአዋጅ ቁጥር 391/1996 አንቀጽ 54 ጽሕፈት ቤት እየተባለ የሚጠራው የትምህርትና ሥልጠና ዘርፍ የሙያ ብቃት ማረጋገጫና ሥርዓት የመቆጣጠር ሥልጣን በአንቀጽ 56(5) ተሰጥቶታል:: ሆኖም የትምህርት ልህቀት ማዕከሉ የዚህን ጽ/ቤት ስልጣንም ይነጥቃል:: በአንቀጽ 56(6) መሰርተ ሀገር አቀፍ ሥልጠና ማጠናቀቂያ ማስረጃ አሰጣጥ ሊከናወን የሚገባዉ በአዋጅ 391/1996 በተቋቋመው ጽሕፈት ቤት ሥር ሆኖ እያለ የልህቀት ማዕከሉ ማስረጃዎችን ውድቅ የሚያደረግ ምዘና መስጠቱ የህግ አግባብ የለዉም:: እንዲሁም በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 57 የተቋቋመውን ካውንስል በአንቀጽ 58(ለ) የሙያ ክህሎት፣ ሥልጠና እና የሙያ ብቃት ምዘና ምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥልጣንን ቀምቷል::

የልህቀት ማዕከሉ ከሌሎች ህጎች ጋር ለምሳሌ በአንቀጽ 5 ከቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ተቋማት ወይም ከኮሌጆች ለሚወጡ ሠልጣኞች የሙያ ብቃት ምዘና ማካሄድና የሙያ ብቃትና ጥራትን ለማሳደግ እንዲሁም በቴክኒክና ሙያ ጉዳዮች ጥናትና ምርምር ለማድረግ የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና አዋጅ አንቀፍ 55 የጽ/ቤት ተግባር ጋር ተደራራቢነት ብቻ ሳይሆን መናበብ ሲሳነዉ ይስተዋላል:: የአዋጁና የደንቡ ተፈጻሚነት ወሰን ከአዋጁ አንቀጽ 3 እና የደንቡ ተፈፃሚት ወሰን በአንቀጽ 17 የማይጣጣሙ መሆናቸውና ተናባቢ አለመሆናቸውን ያሳያል::

የልህቀት ማዕከሉ ሕግ ውጤት (ተፅዕኖ) ቀላል አይደለም:: ዋና ዋናዎቹ ተጽዕኖዎችም :-የልህቀት ማዕከሉ የሚያወጣዉን ፈተና ማለፍ እንደ መስፈርት በመቆጠሩ ተማሪዎች ቀጣይ ትምህርት ለመማር ከትምህርት ተቋማት ያገኙትን ማስረጃ በማቅረብ ቀጣይ ትምህርት መማር አለመቻላቸው ከፍተኛ የስነልቦና ጫና ይፈጥራል:: በመንግሥትም ሆነ በግል ተቋማት የልህቀት የማዕከሉን ማስረጃ ምክንያት በማድረግ ሥራ የማግኘት ዕድል አሉታዊ ተጽዕኖ መከሰቱ በዜጎች ዘንድ አላስፈላጊ ምሬት መፍጠሩ አይቀሬ ነዉ::

ከሀገር ኢኮኖሚ ብክነት አንጻር ሲገመገምም ተማሪዎች ጊዜአቸውን፣

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ሰላማዊ ህዝባዊ አመፅ እንደ ለውጥ መንገድ?

(ከባለፈው የቀጠለ)



በመስከረም አበራ

በሰሜናዊ አፍሪካ ሃገሮች የታየው በተለምዶ "የፀደይ አብዮት"በመባል የሚታወቀው ህዝባዊ አመፅ ወደሌሎች የአፍሪካ ሃገራት እንደሚዛመት ተገምቶ ነበር:: እንቅስቃሴው የታየባቸው ሃገራት አስጨንቀው የሚገዟቸውን አምባገነኖች ማስወገዱ ቢሳካላቸውም የሃገራቸውን ፖለቲካ መልክ ማስያዙ ከጀማሪዋ ቱኒሲያ በስተቀር ለሌሎቹ አልተሳካም:: በተለይ ግብፅ ዞሮ ዞሮ በወታደራዊ መንግስት መዳፍ ውስጥ ተመልሶ መግባቱ አልቀረላትም:: በትግሉ ሂደት ውስጥ የብዙዎች ህይወት መጥፋቱ፣ ንብረት መውደሙ እና የተፈለገው ውጤት እምብዛም የሚያረካ አለመሆኑ ከአምባገነን መንግስታት ጋር መታገል ብዙ ሊታሰብበት የሚገባ ነገር እንደሆነ ያመላክታል:: በተለይ የተጠላው መንግስት ከወደቀ በኋላ ስለሚኖረው ፖለቲካዊ ከባቢ በቅጡ ሊታሰብበት ይገባል:: ይህ ሳይሆን ቀርቶ በ 'ውጡ እንውጣ ብቻ' አብዮት ለማስነሳት መሞከሩ ከጥቅሙ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል:: ከጉዳቶቹ ግልፅ የሆኑትን ለመግለፅ አምባገነን መንግስታቱን የመጣሉ ሂደት የሚጠይቀው ዋጋ፣አብዮቱን የሚመሩ አካላት የእርስበርስ መከፋፈል እና መተላለቅ፣ከመንግስታቱ መውደቅ በኋላምመንበሩን ተቀብሎ መልክ የማስያዙ ነገር ካልታሰበበት የእርስበርስ ፍጅት፣ ዘረፋ፣ የውጭ ጣልቃገብነት ማስከተሉ ወ.ዘ.ተ ናቸው::

እነዚህ ችግሮች ህዝባዊ አመፁ የተፈለገውን ለውጥ እንዳያመጣ ስለሚያደርጉት ህዝቡ ወደተስፋ መቁረጥ ያመራል:: የቀደመ የለውጥ ፍላጎቱንም ያሳጣዋል::ይሄኔ ከአምባገነኑ መውደቅ በኋላ በተነሳው ግርግር ስልጣን ላይ የወጣው አካል(በአብዛኛው ወታደሩ ክፍል ይሆናል) ከበፊቱ የበለጠ አምባገነን ቢሆን እንኳን ሃይ የሚለው የህዝብ ቁጣ ያጣልና የአምባገነንነቱ አዙሪት ከመቀጠሉም በላይ ህዝቡ ለውጥን የሚፈራ ድንጉጥ ይሆናል::የትግሉ አርአያነትም መልካም አይደለም እና የሌሎች ሃገሮችን የለውጥ ፍላጎት ለመግታት ጎረቤት አምባገነኖች እንደ መቀጣጫ የሚያነሱት ሁነት ይሆንላቸውል::

የቱኒሲያ አብዮት ስኬት ሊቢያን እና ግብፅን የማነቃቃቱን ያህል፤የግብፅ እና የሊቢያው ግን ወደ ሌሎች ሃገሮች መዛመት የተሳነው የሃገራቱ ህዝባዊ እንቅስቃሴዎች ከተስፋ ሰጭነታቸው ይልቅ አስፈሪነታቸው ስላመዘነ ነው:: በእርግጥ የቱኒሲያው አብዮት የሰመረው የወታደሩ ወገንተኝነት ወደ ህዝቡ መሆኑ እና 'በህዝቡ ላይ አልተኩስም' በማለቱ ነበር:: የአምባገነኖች መተማመኛ ደግሞ ጠብመንጃ ነውና የወታደሩ እርምጃ ፕሬዚዳንት ቤን አሊ እግሬ አውጭኝ እንዲሉ አስገድዷል:: ዋናው ጥያቄ ግን 'የቱኒሲያው ምቹ ሁኔታ ሁሌ ይከሰታል ወይ?' የሚለው ነው::

በቅርቡ የሃገራችን መንግስት በኢቲቪ ሲያስተላልፈው የነበረው ዳክመንተሪ ፊልም የሶሪያን፣የግብፅን፣የዩክሬንን..... ያልተሳኩ ህዝባዊ የለውጥ እንቅስቃሴዎችን እያነሳ፣ "ተንታኞች" እያፈራረቀ ሲያሳይ የነበረው ሁሉ 'ብትሞክሩት ይህ ይሆንባችኋል' እንደማለት ያለ ማስፈራሪያ መሆኑ ነው:: በዶክመንተሪ ፊልሙ ከላይ የተጠቀሱትን ህዝባዊ አመፁ ያልተሳካላቸውን ሃገራት ሲዘረዝር በሰላማዊ ህዝባዊ አመፅ መንግስት መለወጡ የተሳካለትን የቱኒዚያውን ህዝባዊ አመፅ መጥቀስ አለመፈለጉ የፊልሙ አላማ ማስፈራራት እንደነበር ተጨማሪ ማስረጃ ነው::ሆኖም አሁንም በሃገራችን በህዝባዊ ሰላማዊ አመፅ የመንግስት ለውጥ ማምጣቱ ይሳካል ብለው የሚያስቡ አልጠፉም:: በግሌ ይህ እንደ መፃፍ መናገሩ የሚቀል አይመስለኝም:: ምክንያቶቼን በአዲስ መስመር ላስረዳ::

ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘበት ዘመን ጀምሮ በሃገሪቱ ያረበበው የዘር ፖለቲካ ህዝቡን በጎሳ ከመከፋፈሉም በላይ የአብዛኛውን ህዝብ ስሜት እና ቀልብ የመሳብ ከፍተኛ ሃይል ያለው የዘር ጉዳይ ብቻ ሆኖ ህዝቡ በሃሳብ ተመሳሳይነት ዙሪያ እንዳይሰባሰብ ከልክሎታል::እናም አብዛኛው ፖለቲካዊ ንቃት አለኝ ባይ ዜጋ ቀልቡን ሰብስቦ የሚያዳምጠው የመጣበትን ብሄር ውሎ አዳር ሆኗል:: በአንፃሩ በሃገር ደረጃ የህዝቡ የኑሮ ደረጃ እያደር ማሽቆልቆል፣የዲሞክራሲ እጦት፣የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ የመልካም አስተዳደር መጥፋት ወ.ዘ.ተ የሚያስተባብሩ ጉዳዮች አልሆኑም:: በምትኩ መፈራራት፣መጠራጠር፣'መንግስት ቢቀየር እንኳን የእንትን ብሄር ተመልሶ ሺህ አመት ሊገዛ የሚችልበት በለስ ሊቀናው ይችላል' በሚል የእርስበርስ መጠባበቁ አይሏል::ከብሄር እና ከሃይማኖት በቀር የሚያስተባብር ነገር በዚች ሃገር ጠፍቷል:: ዋኖቻችን ለነፃነታችን ከሃገሪቱ ዳርቻ ተጠራርተው በሞቱበት የአድዋ ድል አንድምታ ላይ እንኳ መስማማት አቅቶን ለአንድ ብሄር አንዳንዴም ለአንድ ሰው ሽልመን ባይትዋርነትን እንመርጣለን:: በዚህ መንፈስ ያለ ህዝብ በምን ሁኔታ ተደማምጦ ፣በአንድነት ታግሎ የመንግስት ለውጥ ሊያመጣ ይችላል ተብሎ እንደሚታሰብ ግራ ነው:: ከለውጡ በኋላ በሚሆነው ነገር ላይ ሳይታሰብበት ተጠራርቶ አደባባይ የመውጣቱ ነገር ቢሳካ እንኳን ውጤቱ ትሻልን ሰዶ ትብስን እንደማያመጣ እርግጠኛ መሆን አይቻልም:: በበኩሌ አደባባዩ ላይ እንገናኝ የሚለው ነገርም የሚሳካ አይመስለኝም:: እንደው በሆነ ተአምር ቢሳካ ብለን ብናስብ እንኳን አደባባይ ያስወጣን ችግር ሳይፈታ አንገባም ብለን እዛው የምንቆየው ጊዜ ምን ያህል ይረዝማል? በዘር ሳንከፋፈል አደባባዩ ላይ የምንሰነብተውስ ለስንት ቀን ይሆናል?አመጹን የሚመራው የእኛ ጎሳ ሰው ካልሆነ ሁሉ ነገር ይቅር የማንለውስ ስንቶቻችን ነን? የመንግስት የጥይት አረር፣ የቦምብ ድምፅ አስበርገጎ ቤታችን የማያስገባንስ ምን ያህል ነን?

አምባገነን መንግስታት በስልጣናቸው ለመጣ በምድር የሚሽከረከረውንም በአየር የሚበረውንም ወታደራዊ መሳሪ ተጠቅመው ፀጥ ለማድረግ እንደሚሞክሩ የታየ ሃቅ ነው:: ይህን ተቋቁሞ በሰላማዊ የህዝብ ተቃውሞ የተፈለገውን የመንግስት ለውጥ ለማምጣት ደግሞ መጀመሪያ እርስበርስ መተማመን፣ በተወሰኑ ወሳኝ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ ግድ ይላል::መግባባቱ ከሌለ ለሰላማዊ ተቃውሞ መነሳሳት ሆነ በገቢር እንቅስቃሴ ማድረጉ የሚታሰብ አይሆንም:: አሁን በሃገራችን ያለው የቋንቋ መደበላለቅ እና ጥላን ያለማመን ጥርጣሬ ደግሞ በተራው ህዝብ ቀርቶ የተቃውሞ ፖለቲካውን ልጓም በጨበጡ ልሂቃን ላይም የሚታይ ነው:: ልሂቃኑ በጋራ መስራት የሚችሉባቸውን ጉዳዮች ነቅሰው አውጥተው በጋራ ለመስራት ሆደ ሰፊነቱም ተነሳሽነቱም የላቸውም::በመሆኑም በአንድ ሳምንት ልዩነት ሁለት ሰልፍ እየጠሩ ህዝቡን ግራ ያጋባሉ:: ጭራሽ የኢህአፓን እና የመኢሶንን ዘመን በሚያስታውስ ሁኔታ(የኢህአፓውን የጠረባ ቡድን ያስታውሷል) 'በእኛ ፓርቲ ሰልፍ የእንትን ፓርቲ አባላት ምን ሊያደርጉ መጡ' በሚል ለድብድብ የሚጋበዙ አባላትን ያቀፉ ተቃዋሚ ፓርቲዎችም እየታዩ ነው::የሚጠራው ሰልፍ አላማን ሳይሆን የፓርቲንስም ያስቀደመ ማድረጉም የተቃውሞ ፖለቲካውን ስንዝር የማያራምድ ግን እንደ መልካም ነገር በመቀጠል ላይ ያለ ፈሊጥ ሆኗል::

በመንግስት በኩል ለሩብ ምዕተ-ዓመት የሰው ማንነት ድርና ማግ የሚናገረው ቋንቋ ብቻ ይመስል በዚሁ ሲከፋፈል የኖረ ህዝብ በተቃውሞው ጎራ ቢያንስ በዋነኛ ሃገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ አስተባብሮ ለበጎ ለውጥ የሚመራው ፓርቲ ያስፈልገው ነበር::ይህ ሲሆን ግን አይታይም::የተከፋፈለ ህዝብ ደግሞ እንደ ኢህአዴግ እስከ አፍንጫ የታጠቀ፣በኢኮኖሚም ራሱን ያደነደነን መንግስት ትርጉም ባለው ሁኔታ መገዳደሩ ቀላል አይሆንለትም:: ለዚህ ነው በተለያየ ጊዜ በተለይ በግሉ ፕሬስ ሰላማዊ ህዝባዊ አመፁ 'የማይቀር ነው' ሲባልለት ብዙ ጊዜ ቢያልፍም እውን ሳይሆን አመታት የነጎዱት:: ህዝባዊ ዝምታው የመጣው ኢህአዴግ እንደሚለው አስተዳደሩ ያመጣው እድገት የህዝቡን የልብ ስላደረሰ አይደለም:: ይልቅስ ህዝቡ ከገዥውም ከተቃዋሚውም ጎራ የሚያምነው አጥቶ በዛ ላይ ተከፋፍሎ ስላለ ነው::

ሌላው ሰላማዊ ህዝባዊ አመፁን ከመከሰት የሚከለክለው ጉዳይ በሃገርቤት የከተሙ፣በቋሚነት ላመኑበት ጉዳይ የሚሰሩ፣ህዝቡን የሚያነቃቁ ጠንካራ አክቲቪስቶች ያለመኖር፤ መንግስትም እንዲኖሩ ያለመፈለጉ ጉዳይ ነው:: በአሁኑ ዘመን ለፖለቲካዊ ለውጥ ስኬት የአክቲቪስቶች ሚና ከፍ ያለ ነው:: በተለይ እንደእኛ ሃገር በየምክንያቱ ለሚከፋፈል ህዝብ መከፋፈሉ የመተባበሩን ያህል ጥቅም እንደሌለው የሚያስረዱ አክቲቪስቶች ያስፈልጉታል:: አቀንቃኞች/ አክቲቪስቶች እንደየዝንባሌያቸው የተለያዩ ማህበረ-ፖለቲካዊ ችግሮችን ነቅሰው አውጥተው ስለመፍትሄያቸው እንዲሰራ የሚጎተጉቱ ግለሰቦች ናቸው:: የአንድን ሃገር ጎላ ያሉ ማህበረ-ፖለቲካዊ ህማማቶች በመንቀስ ወደ በጎው መንገድ ለመምራት አክቲቪስቶች ዋና ናቸው:: በሃገራችን ልምዱ ስላልነበረም፤ አምባገነን መንግስታትም የግለሰቦቹን መኖር ስለማይፈልጉ ጠንካራ አክቲቪስቶችን ማየት አልተቻለም:: ይህ በሚሆንበት ጊዜ ጋዜጠኞች እና ፀሃፍት የአክቲቪስትነቱንም ሚና መወጣት አለባቸው የሚል አዲስ እይታ አለ::እውቁ ጋዜጠኛ እና ተንታኝ እስክንድር ነጋ ይህን ሃሳብ በማራመዱ በሃገራችን ቀዳሚ ነው፤ለተግባራዊነቱም እስር ሳይቀድመው በፊት ብዙ ሰርቷል::ሃገራቸው ተለውጣ ማየት የሚፈልጉ ጋዜጠኞች እና አምደኞችም ፈለጉን በመከተል በቅርቡ የአክቲቪስትነቱን ስራም ለመስራት እየሞከሩ ነው::ሆኖም ጋዜጠኞቹ በሚፈልጉት ፍጥነት እና ድምቀት ህዝባዊ እንቅስቃሴው እየታየ አይደለም:: ምክንያቱም ለህዝባዊ እንቅስቃሴ በብዙሃኑ በኩል ፖለቲካዊ ንቃት ይሰርፅ ዘንድ ያስፈልጋል፤ለዚህ ደግሞ ህዝቡ እንደዜጋ ሊያገኘው ሲገባ ስለጎደለበት ነገር ሳያሰልሱ የሚወተውቱ በርከት ያሉ አክቲቪስቶች ያስፈልጋሉ:: ይህ ባለመሆኑ ህዝቡ መንግስትን በእውቀት ላይ በተመሰረተ መልኩ እንዳይገዳደር፣እንዳይተች፣ነገሩ ሲበዛም እንዳይቆጣ ከልክሏል::በውጤቱም በሰላማዊ ህዝባዊ አመፅ መንግስት የመቀየሩ ነገር በነፃው ፕሬስ ሚዲያዎች ገፅ እንጅ በሃገራችን ምድር ላይ የማይወርድ ህልም አስመስሎታል::

ሌላው ተመሳሳይ ችግር በፖለቲካዊ ጉዳዮች፣በሰብአዊ መብቶች ዙሪያ ወጣቱ በሚያዘወትራቸው የማህበራዊ ድህረገፆች ላይ በቋሚነት እና ሳቢ በሆነ መልኩ የሚፅፉ ብሎገሮች አለመኖራቸው ነው:: ሰላማዊ ህዝባዊ አመፅ እንደጦር ሜዳ ትግል አዝማች ጄኔራል ስለማይኖረው እነዚህ ብሎገሮች የትግሉን አቅጣጫ የመምራቱን ነገርም አብረው ይሰራሉና እንደመሪም ሊቆጠሩ ይችላሉ:: በግብፅ እና ሊቢያ አብዮት በሚገርም ፅናት ትግሉን ሲመሩ የነበሩት ወጣት ብሎገሮቹ ነበሩ::ትግሉ ከተፋፋመ በኋላም በህዝቡ ላይ ይደርስ የነበረውን ሰቆቃ ለአለማቀፍ መገናኛ ብዙሃን በድምፅም በፅሁፍም እያደረሱ ትግሉ በአለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት እንዲስብ ያደርጉ ነበር:: በዚህ ሁሉ ውስጥ መሞት፣መታሰር፣ መንገላታት ነበር::

ወደእኛ ሃገር ተጨባጭ ሁኔታ ስንመለስ የሃገራችን ወጣቶች ማህበራዊ ድህረ-ገፆች በአመዛኙ የሚጠቀሙት ለማህበራዊ ጉዳዮች እንጅ ፖለቲካው አጀንዳ ያላቸውን ፅሁፎች የሚጎበኘው ሰው ቁጥር ጥቂት ነው:: በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርገው የሚፅፉ በሃገር ውስጥ ያሉ ብሎገሮችም ቁጥራቸውም ሆነ ተፅእኖ ፈጣሪነታቸው ብዙ አይደለም:: በርግጥ ጅምሩ በዞን ዘጠኝ ጦማሪያን ተጀምሮ ነበርና ጅምር መኖሩ መልካም ቢሆንም ተፅዕኖ ፈጣሪ የመሆኑ ነገር ግን ገና ነው::

ሃገራችን ከትጥቅ እስከ ሰላማዊ ትግል የተሞከረባት፣ብዙዎች ስለለውጥ ሲሉ ህይወታቸውን ያጡባት ነች::ነገር ግን ይህ ነው የሚባል ለውጥ ሳይታይ አሁንም ከድህነት እና ከመልካም አስተዳደር እጦት ጋር አለች::ይህን ሁሉ ያሳለፈችው ሃገራችን አሁን የሚያስፈልጋት ተጨባጭ ውጤት የሚያመጣ እርምጃ እንጅ እንዳለፉት ትግሎች መስዕዋትነትን ብቻ የሚያመጣ ሆኖ የሚቀር መሆን የለበትም::ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል ለሚለው ወሳኝ ጥያቄ በግሌ አዋጭ የሚመስሉኝን የቢሆን መንገዶች ሳላይ::

**መንገድ አንድ:-** ይህ መንገድ ሙሉ በሙሉ በኢህአዴግ እጅ ያለ እና ተመራጭነት ያለው መንገድ ይመስለኛል::እንደሚታወቀው ኢህአዴግ ለረዥም ዘመን አሸናፊነትን ብቻ ሰንቆ በሚነሳው የአቶ መለስ ፖለቲካዊ ስነ-ልቦና ሲሾር የኖረ ፓርቲ ነው::ምርጫውም ምርጫ፣ ድርድሩም ድርድር የሚሆነው ኢህአዴግን አሸናፊ እስካደረገ ድረስ ብቻ ነበር:: ይህ ይሳካ ዘንድ ደግሞ ምርጫ ቦርድን አይነት የዲሞክራሲ ተቋማት ቀርቶ ሽምግልናን የመሰሉ በሃገራችን ትልቅ ስፍራ የሚሰጣቸው ማህበራዊ ልማዶች ሳይቀሩ ኢህአዴግ በአሸናፊነት ማማ እንዲቀመጥ በሚሰሩ ግለሰቦች እንዲዘወሩ ተደርጎ ኖሯል::ይህ በርግጥ ፓርቲው እስከዛሬ ስልጣን ላይ እንዲቆይ ማድረጉ እርግጥ ነው::ስልጣን ላይ ደግሞ እንደምንም ብሎ መሰንበት ይቻል ይሆናል እንጅ እንደ መለኮት ዘላለም ስልጣን ላይ መቀመጥን አያስችልም:: ተወደደም ተጠላ አንድ ቀን ወንበር መክዳቱ አይቀሬ ነው::ኢህአዴግ አሁን በሚያደርገው መንገድ ስልጣን ላይ መሰንበት ደግሞ የማይቀረውን አወዳደቅ የሚያከፋ እንጅ የሚያሳምር አይሆንም::

ኢህአዴግ ስልጣን ከማፍቀሩ የተነሳ ስልጣን ላይ የቆየበት ዘመን ርዝመት ለራሱ የታወቀው ባይመስልም የቆየበት ዘመን እጅግ ረዥም ነው:: ከዚህ በላይ ስልጣን ላይ ለመቆየት የሚያስችል መስህብም የለውም:: በፖለቲካው ሆነ በኢኮኖሚው ረገድ አመጣሁ የሚለው ለውጥ ረዥም የስልጣን እድሜውን የሚመጥን አይደለም:: ስለዚህ ፓርቲው ወደደም ጠላም ህዝቡ ለውጥ ይፈልጋል:: ለውጡን ሰላማዊ በማድረጉ በኩል ደግሞ ከኢህአዴግ ብዙ ይጠበቃልና ሁሌ ላሸንፍ ባይ ፖለቲካዊ ስነ-ልቦናውን ከአቶ መለስ ጋር መቅበር ይጠበቅበታል:: ድርድር ማለት ሽንፈት ማለት እንዳልሆነ ተገንዝቦ ስለሃገር ያገባኛል ከሚሉ ሃይሎች ጋር ሁሉ የእውነት የሆነ ድርድር ያደርግ ዘንድ ግድ ነው:: ይህን ማድረግ ለራሱም የሚጠቅመው መንገድ ነው:: ድርድሩ የዲሞክራሲ ተቋማትን እና የመገናኛ ብዙሃንን ገለልተኝነት የሚያረጋግጥ፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በነፃነት ይንቀሳቀሱ ዘንድ የሚፈቅድ ፖለቲካዊ ከባቢ የሚያመጣ መሆን አለበት:: ይህን ካደረገ በኋላ ያለ እኔ አይሆንለትም የሚለው ህዝብ ይመርጠው እንደሆን የሚያይበት፣ ከዚህ የተለየ ውጤት ሊመጣ ከቻለም የሚቀበልበትን ስነ-ልቦ አዳብሮ ነፃ ምርጫ ማካሄድ ይጠበቅበታል::

**መንገድ ሁለት:-**ለዚህኛውም መንገድ ስምረት የኢህአዴግ ለለውጥ መዘጋጀት ያለመዘጋጀት ዝንባሌ ወሳኝ ነው::ኢህአዴግ ብዙ አመት ፀረ-ልማት፣ፀረ-ሰላም እያለ ሲያብጠለጥላቸው ከነበሩት ተገዳዳሪዎቹ ጋር ቁጭ ብሎ መደራደሩን(መንገድ አንድን) እንደ ሽንፈት ከቆጠረው ሃገሪቱን ለተወሰነ አመት ተረክቦ፣ማህበረ-ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮቿን መልክ አስይዞ ለዲሞክራሲያዊ ምርጫ የሚያዘጋጅ የባለሙያዎች መንግስት(Technocratic Government) እንዲቋቋም ማድረግ ቢችል በለውጥ ስም የሚመጣውን ደምመፋሰስ እና የንብረት ውድመት ማስቀረት ይቻላል::የቴክኖክራቶች መንግስት ጥልቅ እውቀት እና ልምድ ያላቸውን ምሁራን በየተማሩበት መስክ ሃገራቸውን እንዲያስተዳድሩ በየሚኒስተር መስሪያቤቱ እና በየሴክተሩ

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

አደባባይ ያስወጣን ችግር ሳይፈታ አንገባም ብለን እዛው የምንቆየው ጊዜ ምን ያህል ይረዝማል? በዘር ሳንከፋፈል አደባባዩ ላይ የምንሰነብተውስ ለስንት ቀን ይሆናል?አመጹን የሚመራው የእኛ ጎሳ ሰው ካልሆነ ሁሉ ነገር ይቅር የማንለውስ ስንቶቻችን ነን? የመንግስት የጥይት አረር፣ የቦምብ ድምፅ አስበርገጎ ቤታችን የማያስገባንስ ምን ያህል ነን?



ደምስ ሠይፉ
sebaradildiy@gmail.com

# ገብሬ . . . . የጥበብ ገበሬ

## ድልድይ

አንዳንድ የጥበብ ትሩፋቶች ከዘመን አውድ ተሻግረው፣ ከውልደት ታዛቸው አልፈው የመሄዳቸውን ያህል አንዳንዴ የጠቢቡን ጥቅል ውስጠ - ምስል በማንጸባረቅ ለዘመናት ሲያስደምሙን ማየት የተለመደ ነው። ከጠቢባን ስራዎች የምንመርጠውም ባይሆን የምናበላልጠው መኖሩ፣ ለመንፈሳችን ቀርቦ አልያም ለአተያያችን ስቦ የምናጎላው ስራ መታዘቡ እንግዳ ነገር አይደለም። እዚህ ላይ የበዓሉ ግርማ ‘ኦሮማይ’፣ የክ/ዶ/ር ሐዲስ ዓለማየሁ ‘ፍቅር እስከ መቃብር’ እንዲሁም የስብሐት ገ/እግዚአብሔር ‘አምስት፣ ስድስት፣ ሰባት …’ ከስራዎቻቸው ሁሉ በተለይ ተጠቃሽ የሆኑበት አብይ ምስጢር ደራሲዎቹ የነፍስ ጩኸታቸውንና የመንፈስ ሽራፊያቸውን አጥንትና ደም ከስራዎቻቸው ጋር በመቀላቀላቸው ሳይሆን አይቀርም። በዓሉ ኦሮማይን ከመፃፉ በፊት የመጽሐፉ ጭብጥ ሊያስከትል ያለውን ዳፋ በገለጸባት #የመጨረሻው መጀመሪያ; የተሰኘች አጭር ልብወለድ ላይ ውስጠ ስብዕናውን እንድናይ ማድረጉን ስናስታውስና በትርክቶቹ የኦሮማይ ውልደት ዋዜማዎችን አስጨናቂነት በገሃድ ማየታችን ከመጽሐፉ ጋር በአንዳች ስውር መንፈስ እንድንተሳሰር አስተዋጽዎ ማድረጉ አልቀረም፣ ከቁጭትና ሕመም ጋር። ክቡር ሐዲስም የሕይወት ሽራፊያቸውን በፍቅር እስከ መቃብሩ በዛብህ በኩል ግዘፍ ነስቶ እንድናይ ማድረጋቸው ልቦለዱን የአንድ ዘመን እውነተኛ ክስተት እንጂ የፈጠራ ውጤት ብቻ አድርገን እንዳንወስድ በሚያስገድድ የደም ትስስር ከስራቸው ጋር ቋጥረውናል። ደራሲው ራሳቸው ‘በጣም የምወደው ስራዬ ወንጀለኛው ዳኛን ነው’ ቢሉም እኛ ግን ከፍቅር እስከ መቃብር አስከትለን እንጂ አስቀድመን ላንጠራው ምለናል። ‘ስራዎቼ የእውነተኛው ዓለም ቅጂ እንጂ ፈጠራ አይደሉም’ የሚለን ስብሐትም ‘አምስት ስድስት ሰባት’ መጽሐፉ ላይ በሳላቸው ገጸባሕሪያት አማካይነት የዘመንተኞቹን ሕመምና ጉስቁልና አጥንታችን ድረስ ዘልቆ እንዲሰማን በሚያደርግ የገለፃ አቅሙ ገጸባሕሪያቱን አትሞብናል፣ የሰው ጉዳይ ለስብሐት ምን ድረስ እንደሚሄድም እንድናይ በማድረግ ጭምር።

የዛሬው ባለታሪካችን ገጣሚና ሰዓሊ ገብረክርስቶ ደስታ ከዚህ አንፃር የሚጠቀሱለት ሁለት ስራዎች አሉ፤ ከገጣሚነቱ ኃይለ ቃል የተቀዳው ‘ሃገሬ’ እና ከሰዓሊነቱ የቀለም ውበት የተወለደው ‘የራስ ምስል’ /Self portrait/፤ ገብረክርስቶስ የስደት ቁርና ብርድ ካንሰፈሰፋት ነፍስያው የሸረፋት ‘ሀገሬ’ ግጥሙም ሆነ መገለል ካስከተለበት የለምጽ ችግር አብራክ የተወለደው ‘የራስ ምስል’ ስዕሉ ዛሬ ላይ ሆነን ስናስበው እጅግ የሚያሳምሙ እውነቶችን እናይበታለን። ለዚህም ይመስላል ስለ ገብሬ ገጣሚነት ሲወሳ ‘ሀገሬ’፣ ስለ ሰዓሊነቱ ሲዘከር ‘የራስ ምስል’ ከፊታችን ድቅን የሚለው። ሃገሬ ይበልጥ የሚረቅብን ደግሞ በግጥሙ ውስጥ የቆየልን የገብሬ ተማጽኖና ዛሬም ድረስ ለተማጽኖው ምላሽ ያልሰጠው ዝምታችንን ስናስተያይ ነው። የባለፈው ሳምንት ትኩረታችን የነበረው ደበበ ሰይፉ ‘ለምን ሞተ ቢሉ’ በተሰኘች ግጥሙ ‘በደህናው’ ዘመን የከተባቸው ቃላት የዕድሜ ዘመኑ ማብቂያ እውነታዎች እንደሆኑ ሁሉ ገብሬም በ‘ሀገሬ’ ግጥሙ የኳላቸው ቃላት ከህልፈቱ በኋላ ለተከተሉት ከ3 አስርት ዓመታት ፊቅ ለሚሉ ጊዜያት ያልተሳኩ ምኞቶቹ የድማሜ ምንጭ ሆነውብናል። የደበበን ኩርፊያ ዛሬ ላይ መካስ አንችል ይሆናል፣ ነፍሱን የሚያስደስታትን በጎ ስራ ሰርተን እፎይ ካላሰኘናት በቀር፤ የገብረክርስቶስን ምኞት ግን እውን ማድረግ እንችላለን ባይ ነኝ። ምኞቱ ምን ነበር?…

ደራሲ፣ ጋዜጠኛና ሃያሲ ዓለማየሁ ገላጋይ በአንድ መጣጥፉ ላይ የከተባትን ትዝብት እንቆንጥር፤ አለማየሁ የገብረክርስቶስ 75ኛ ዓመት መከበሩን ተከትሎ የግጥሞቹን ተሰብስቦ መታተም፣ የስዕሎቹ በአንድ ተሸክፊው መቅረብ እንዲሁም በአ.አ. ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም አማካይነት በገብረክርስቶስና እስክንድር በጎስያን ላይ ያተኮረ ጆርናል መታተሙን አድንቆ ዓይነ-ጥላችን ስለመገፈፉ ያትትና አንድ ትልቅ ተግባር ግን ይቀረናል ይላል፤

#…ገብሬ ሃገሬ ግጥሙ ላይ …
‘ብሞት እሄዳለሁ - ከመሬት ብገባ
እዚያው ነው አፈሩ - የማማ የአባባ’
…

ሲል ምኞቱን አስፍሮ ነበር። የሚያሳዝነው ግን ይህ ሁሉ ምኞት፣ ይህ ሁሉ የወገንና የሃገር ፍቅር ነፋስ ያገኘው ጠል ሆኖ ነው የቀረው። በአብዮቱ ዘመን ሳይወድ ከተሰደደበት ባዕድ ሃገር ራሱን በግጥም ሲያስታምም ለሦስት ዓመት ያህል ቆይቶ በመጋቢት 21/1973 ዓ.ም. ሕይወቱ አለፈች፣ በአሜሪካ ኦክላሃማ



ውስጥ፤ ግና እንዳሰበው ለአገሩ መሬት ሳይበቃ እዚያው ባዕድ ክፍለ ሃገር ውስጥ ተቀብሯል። አንዳንድ ጊዜ ሁኔታዎች እንዲህ ይጨክናሉ። ብዙ አትጠይቅም፣ እሱኑ አታገኝም…; አለማየሁ ይቀጥላል #…ለገብረክርስቶስ ሃገሩ ፍቅሩ ነበረች። ምናልባትም የሕይወቱ ሁሉ ትርጓሜ። በግጥሞቹ ውስጥ ስለፍቅር፣ ስለናፍቆት፣ ስለቸርነት፣ ስለዕድገት … ሲያጫውተን ሃገሩ የነገሮች ሁሉ ማሰናሰያ ሆና ነው የምትቀርበው። ለገብረክርስቶስ ኢትዮጵያ ቁዛሜው ነበረች፣ አዝሎ እሽሩሩ የሚላት። ታዲያ ምን ይሆናል፣ ለአፀደ ሥጋው ቀርቶ ለአስክሬኑ ማረፊያ ተነፈገችው…; ይህ ነው እንግዲህ ከጥበበኞቻችን ስራዎች ውስጥ እጅግ ጎልተው የሚወጡት ፍሬዎች ከደራሲው ጋር በአንዳች ጥብቅ ሰንሰለት የታሰሩ የመሆናቸው ምስጢር ነው በተለየ ዓይን እንድናያቸው የሚያስገድደን ለሚል መደምደሚያ ያበቃኝ።

> …ሥዕል ለደህና ኑሮ መገንቢያነቱ በአገራችን አልታመነበትም፤ ቤተሰቦቼም የእርሻ ትምህርት እንድማር ይፈልጉ ነበር፤ እንደኛ ላለች ሃገር የእርሻ ትምህርት መከታተል አስፈላጊ በመሆኑ እኔም ታላቅ ምርጫ አድርጌው ነበር። ይሁን እንጂ…

## ልጅነት

ጥቅምት 5 ቀን 1924 ዓ.ም. የባለታሪካችን የሕላዌ ደወል የተደወለባት ቀን ናት፤ ታሪካዊዋ የሐረር ከተማ የዚህን ታላቅ ሰው የመኖር ጅማሬ ያጸደቀችው ፋሽስት ሃገራችንን ለመውረር ጥቂት ዓመታት ሲቀረው ነው። ይህ ወቅት ከሐረር የተገኙት ተፈሪ መኮንን ንጉሰ-ነገስት ተብለው የተሾሙበት 1ኛ ዓመትም ነው። የገብረክርስቶስ አባት አለቃ ደስታ በቤተክህነት ትምህርት ጥልቅ እውቀት የነበራቸው ሲሆን አባታቸው ደብተራ ነገዎ በቁም ጸሐፊነትና መጽሐፍ ደጓሽነት የነበራቸውን ዕውቀት ከልጅነታቸው ጀምሮ የገበዩና ብራና በመረምረም፣ ቀለም በመጥበጥና ሐረግ በመጣል ሲያግዙዋቸው ካካበቱት ልምድ ባለፈ ዕድሜያቸው ለትምህርት ሲደርስ ከቤተሰቦቻቸው 15 ዓመት ያህል ተለይተው የአብነት ትምህርቶችንም ቀስመዋል። ግና ወደ ቀያቸው ሲመለሱ አባታቸውን በህይወት አላገኙም ነበር፤ በዚህም ምክንያት ከአንኮበር ወደ ቡልጋ ተጉዘው እናታቸውን ማግኘት ነበረባቸው። በዚህ ወቅት ነበር የርሳቸውንም ሆነ የልጃቸውን የወደፊት መኖሪያና የሕይወት ዘዬ የሚለውጥ አጋጣሚ የተፈጠረው፤ ቡልጋ ሳሉ የአለቃን ሊቅነት የሰሙት ባላምባራስ መኮንን ባለሚላቸው እንዲሆኑ ይጠይቋቸዋል፤ አለቃ በሃሳቡ ተስማምተው በባላምባራስ እልፍኝና ጓዳ ባለሚልና ፀሐፊ ትዕዛዝ ይሆናሉ፤ ባላምባራስ ከአጼ ምኒልክ ጋር ወደ ሐረር በዘመቱ ጊዜም አለቃ አብረዋቸው ተጓዙ። መጋቢት 13/1898 ባላምባራስ መኮንን /በኋላ ራስ/ መሞታቸውን ተከትሎ ደጃች ይልማና ደጃች ባልቻ በተሾሙ ጊዜም አለቃ አብሮነታቸው አልተቋረጠም ነበር። ቆይቶ የራስ መኮንን ልጅ የሆኑት ተፈሪ መኮንን /በኋላ አጼ ኃ/ሥላሴ/ ሐረርጌ ላይ ተሹመው ሲመጡም የሐረር ዙሪያን አስተዳደር ለአለቃ ስለሰጧቸው ተፈሪ አልጋ ወራሽ ሆነው ወደ አዲስ አበባ እስከሄዱበት 1909 ዓ.ም. እና የፋሽስት ወረራ ድረስ በዚሁ ስራቸው ላይ ቆይተዋል። በዚህም ምክንያት አለቃ ደስታ ገብረክርስቶስ ከተወለደበት ጥቅምት ወር መግቢያ ጀምሮ የራሷን ጳጳሳት መሾም የጀመረችበትን አራተኛ ዓመት በዓለ ሲመት በምታከብረው ቤተክህነት መርሐግብር ላይ፣ በእምዬ ምኒሊክ ሐውልት ምርቃት አንደኛ ዓመት ዝግጅት ላይ እንዲሁም በበጅሮንድ ተክለ ሐዋርያት አስተባባሪነት እንደተዘጋጀ በሚነገርለት የመጀመሪያው ሕገ መንግስት ረቂቅ አዋጅ መስሚያ ወቅት በድግሶች ተከባ ሽርብትን ትል በነበረችው አዲስ አበባ መገኘት ግዴታቸው ነበር። ግና ለጉዞ እየተዘጋጁ ባሉበት አንድ ቀን የባለቤታቸው የምጥ ሁኔታ ተፋፍሞ ብቅ አለ፤ በዚያው ዕለት ምሽት ገብሬ ተወለደ። አለቃም ሆነ ቤተሰቡ በጉዞው ዋዜማ በተፈጠረው ልጅ ደስተኞች ነበሩ። ይሁንና የቤተሰቡ ደስታ ከስድስት ወር በላይ አልቆየም፤ እንኳንና በገብሬ ደረጃ ያለ ጨቅላ በማንኛውም የዕድሜ እርከን ለሚገኝ ሰው የመርግ ያህል የሚከብድ ነገር በቤታቸው ውስጥ ሆነ። ገና የመንፈቅ ሕፃን ሳለ ገብረክርስቶስ እናቱን በሞት ተነጠቀ።

የቤተክህነት ሰው ከሆኑት አባቱ አለቃ ደስታ ነገዎ /1849-1947/ እና ወይዘሮ አፀደ ማርያም ወንድምአገኘሁ በስተርጅና የተገኘው የቤቱ 10ኛ ልጅ ገብረክርስቶስ ገና ከጨቅላነቱ ጀምሮ የመከራ ጽዋ መጋት ጀመረ። የገብረክርስቶስን የሕይወት ታሪክ በወጉ ሰንዶ ያቆየልን ብርሃነ መስቀል ደጀኔ በ 1982 ዓ.ም.#የሰዓሊ ገብረክርስቶስ ደስታ የሕይወት ታሪክና አንዳንድ ግጥሞቹ; በሚል ርዕስ ለኢትጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ ባቀረበው ጥናታዊ ጽሑፍ እንዳቀረበው ገብረክርስቶስ የሦስት ዓመት ህፃን ሳለ ነበር ፋሽስት ኢጣሊያ በወልወል ግጭት ሰበብ የመጀመሪያውን ወረራ የፈጸመው፤ በዚህም ምክንያት ሐረር የጦርነት ደመና ያንዣብባት ያዘ፤ በዚህም ምክንያት ገብሬ በልጅነት ዕድሜው ስደት ጀመረ። በ 1927 ዓ.ም. ከሐረር ወደ አዲስ አበባ ተጓዘ፣ ሕፃኑ ገብረክርስቶስ በየካቲት 12/1929 አዲስ አበባና ሕዝቧ በፋሽስቶች ሲፈጁ እዚህ ነበር። ከልጅነቱ መራር ትዝታዎች ውስጥ በጭንቁ ሰዓት ከአባቱ መለያየቱ፣ የአባቱ በጣልያኖች መታሰርና መጋዝ፣ ከዓመት እስራታቸው በኋላ ወደ ሐረር መመለሱ፣ ፊሽስቶችም የሃገሬውን ልጅ ለዓላማቸው መኮትኮቻ እንዲሆን በከፈቱት (ቢላላ) ትምህርት ቤት ከአባቱ ጉያ ተነጥቆ መግባቱ ተጠቃሽ ናቸው።

አስር ዓመት ሲሞላው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን ለመከታተል በ 1933 ዓ.ም. ሐረር በሚገኘው ራስ መኮንን አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተመዘገበ። በዚህ ወቅት አብረውት ከነበሩ የጥበብ ሰዎች ውስጥ ባለቅኔ ሰይፉ መታፈሪያ ተጠቃሽ ነው፣ በክፍል ደረጃ ገብሬ ይበልጥ የነበረ ቢሆንም በትምህርት ቤቱ ውስጥ የነበሩትን አንዳንድ ልማዶቹን ባለቅኔው ያስታውሳል፡ - #… ገብረክርስቶስ ኳስ በጣም የሚወድ ልጅ ነበር፣ በጣም የሚሮጥ፣ ቀልጣፋና ሳይደክም የሚጫወት ነበር፤ ቴኒስም እንጫወት ነበር፤ አቋሙ ሁሉ የስፖርተኛ ነበር … ሌላ ትዝ የሚለኝ፣ ያኔ በባዶ እግር ነበርን፤ የምንለብሰውም ቁምጣ ነበር፤ ታዲያ ጠዋት አልያም በዕረፍት ሰዓት ቁጭ ብለን ፀሐይ ስንሞቅ ቁጭ ብሎ ጉልበቱ ላይ ይስል ነበር፣ በስዕሎቹም እንደነቅ ነበር። ያለምንም ጥርጥር የስን-ክን ሰው ነበር፤ በስን-ክን ስሜት የተነደፈ ልጅ ነበር። …; ገብሬ በ 1938 ዓ.ም. የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን አጠናቀቀ። በ 1939 የ2ኛ ደረጃ ትምህርቱን ለመከታተል ወደ አዲስ አበባ ከተማ አቀና። በዚያም በቀድሞው ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ 2ኛ ደ/ት/ቤት /በኋላ ኮተቤ መምህራን ማሰልጠኛ ኮሌጅ/ በአዳሪ ተማሪነት ተመድቦ ትምህርቱን ቀጠለ። ይህ አጋጣሚ ደግሞ ከሐረሩ አብዬ መንግስቱ ጋር ለመተዋወቅ ዕድል ፈጠረለት። ገብሬ በአዳሪነት የጀመረውን ትምህርት እስከመጨረሻው መቀጠል ስላልቻለ ትምህርቱን አቋረጠ። ምክንያቱ ደግሞ በትምህርት ቤቱ ውስጥ የነበረ የአስተማሪው ውሻ ገብሬን መንከሱና በዚህ እልህ ገብሬ ውሻውን መደብደቡ ነበር። መምህሩ የገብሬን መነከስ ከቁብ ሳይቆጥር ገብሬን መልሶ ይመታዋል፤ ገብሬም በደል የፈጸመበትን ለመምታት ይጋበዛል። በዚህ ምክንያት ተከሶ ርዕሰ መምህሩ ዘንድ የቀረበው ባለታሪካችን ይቅርታ ጠይቅ ሲባል እኔ ምን አጠፋሁ ይልቅ ይቅርታ መጠየቅ ያለብኝ እኔ ነኝ ባይ ሆነ፤ አልፎም ውሻውን በአግባቡ ሳያስሩ ማስተማራቸው አግባብ አለመሆኑን በመግለጽ ሙግት ከፈተ። በዚህ አለመግባባት መነሻነት ገብሬ ከትምህርት ቤት ተባረረ፣ ይባስ ብሎም በወቅቱ 3ኛ ሻለቃ ይባል በነበረ ስፍራ ለአራት ወራት ታሰረ። እስራቱን ሲፈጽም ቀድሞ ከነበረበት ትምህርት ቤት ወጥቶ ወደ ክቡር ዘበኛ ቢዛወርም እዚያም ባጋጠመው የጤና ችግር ምክንያት ትምህርቱን መቀጠል አልቻለም። በየምክንያቱ ከትምህርት ገበታው የሚስተጓጎለው ልጃቸው የደከመበት ትምህርት ከንቱ እንዳይቀር አባቱ ለግርማዊት እቴጌ መነን ተማጽኖዋቸውን እስከማቅረብ ደርሰዋል፡-

## #ግርማዊት እቴጌ…

ገብረክርስቶስ የሚባለው ልጄ እናቱ የመንፈቀ ልጅ ሆኖ ሞተችብኝ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እናትና ሞግዚት ሆኜ አሳድጌ ሐረር የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቱን ጨርሶ፣ ፈተናውን አልፎ ለ2ኛ ደረጃ ት/ቤት አዲስ አበባ ከመጣ አራተኛ ዓመቱ ነው። ባለፈው ግንቦት ወር ከአስተማሪው ጋር ግጭት አድርጎ አራት ወር ያህል ለግሳፄ ከታሰረ በኋላ ወደ ክቡር ዘበኛ ት/ቤት እንዲተላለፍ ታዘዘ። ከዚያ ሳለ ታሞ ከራስ ደስታ ሆስፒታል ገብቶ፣ ታክሞ ወደ ሞቃት ሃገር ንፋስ ይለውጥ ስለተባለ በሃኪሙ ትዕዛዝ ሐረር ወርዶ ስለቆየ ትምህርቱን መከታተል አልቻለም። ለእኔ እመቤቴና አሳቢ እናቴ ግርማዊት መሆንዎን ግርማዊት ያውቁልኛል። ስለዚህ ዋይታዬን ወደ ግርማዊነትዎ ሳሰማ ጩኸቴ ሞገስ አግኝቶ ልጄ እስከዛሬ የደከመበት የትምህርቱ ዋጋ በከንቱ እንዳይቀር አደራን ወደ ግርማዊነትዎ አቀርባለሁ።;

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

የፍጥጫ እንግዳ

# አንድነት ሌሎች ፓርቲዎችን ለመዋጥ አቅጣጫ ይዞ የመጣ ፓርቲ አይደለም



ከኢንጅነር ግዛቸው ሽፈራው የአንድነት ፓርቲ ፕሬዚዳንት ጋር የተደረገ ቃለ-ምልልስ

የቀለም ቀንድ፡- ባለፈው ሰኔ 1 ቀን ከመኢአድ ጋር የቅድመ ውህደት ስምምነት ፊርማ ተፈራርማችኋል የቅድመ ውህደቱ ሂደቱ ምን እንደሚመስል ባጭሩ ቢያብራሩልኝ?

ኢንጅነር ግዛቸው፡- በኢትዮጵያ የፖለቲካ ምህዳር ውስጥ ዲሞክራሲ፣ ፍትህ፣ እኩልነት እንዲኖር የህዝብ ስልጣን ውክልና እንዲያገኝ ፓርቲዎች በአማራጭ ፖሊሲና በህዝብ ድጋፍ ተወዳድረው የህዝብን ውክልና ማግኘት አለባቸው:: አሁን ባለው የተበታተነ የተቃዋሚ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የገንዘብና የህዝብ አቅም ያለውን ፓርቲ ለመደራደርና በምርጫውም ለመሳተፍ ዋናው አላማ መሆን ያለበት ውህደት ነው::

ከዚህ ተነስተን ነው እነዚህ የገዘፉ ፖርቲዎች በመዋቅርም በሰው ሀይልም የተሻሉ ስለሆነ አንድ መሆናቸውን እንደ ትልቅ የፖለቲካ ርምጃ የምናየው:: ይህን ውህደት ከግምት ውስጥ በመክተት በ2002 ዓ.ም የተጀመረውን ውህደት ለማሳካት ድርድር ሲደረግ ቆይቷል:: በሂደቱ ላይ በተለያዩ የቴክኒክ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ጊዜ ወስደን ስንደራደር ከርመናል:: በመሪዎች አካባቢ የቁርጠኝነት ማነስና ፖለቲካዊ እርምጃ የመውሰድ ችግር ነበር:: እንደ መሪ የፖለቲካ እርምጃ መውሰድ ስለነበረብን ይህንን አድርገናል::

በመሰረታዊ የፖለቲካ ፕሮግራም አቅጣጫ ልዩነት አልነበረንም ቴክኒካል በሆኑ ነገሮች ምክንያት ገባ ወጣ የማለት አዝማሚያ ቢታይም ዘግይቶም ቢሆን የቅድመ ውህደቱ ስምምነት ሰኔ አንድ ቀን ተፈፅሟል::

የቀለም ቀንድ፡- በውህደቱ ላይ አንዳንድ ጥያቄዎች ይነሳሉ፤በተለይ በመኢአድ በኩል አሁን ባለው ሁኔታ መኢአድ ወደተለያዩ ቡድኖች መከፋፋሉ ይታወቃል፤ ስለሆነም የተከፋፈሉ ቡድኖችን እንድሰበስብ እና ትክክለኛው የህዝብ ድጋፍ አለኝ ከሚለው ቡድን ጋር ስምምነት እንድያደርግ እና ለውህዱ ፓርቲው እንድጠቅም ለመኢአድ ምን ድጋፍ አድርጋችኋል?

ኢንጅነር ግዛቸው፡- ይሄ የመኢአድ ጉዳይ ነው:: እኛ መኢአድን የምናውቀው ህጋዊ ሆኖ በምርጫ ቦርድ የምስክር ወረቀቱን ይዞ፣ ማህተሙን ይዞ፣ ቢሮውን ይዞ በማዕከል እስከ ታች መዋቅር ያለውን ነው:: ከመዋቅሩ ውጪ በውጪ ያሉ አመራሮች ሊኖሩ ይችላሉ:: እኔ እንደ ችግር አልቆጥረውም:: ዲሞክራሲያዊና ህጋዊ መፍትሔ መስጠት ያለበት ድርጅቱ ነው:: መኢአድ ያለው ህጋዊ መዋቅር መዋሀድ የሚችል ስለሆነ በዚያ መንገድ ነው የምናየው:: ይሄ የመኢአድ የራሱ ችግር ስለሆነ አስተያየት መስጠት ይቸግረኛል:: እንደ እኔ ግን የሚፈጠር ልዩነት መፈታት ያለበት ዲሞክራሲያዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ በህግና በደንቡ መሰረት በውይይት መፈታት አለበት እላለሁ:: ደግሞም ይፈታል የሚል ግምት አለኝ::

የቀለም ቀንድ፡- ትክክለኛውና በህዝብ ዘንድ ተሰሚነት ካለው እና አስኳል ከሆነው መኢአድ ጋር አንድነት የውህደት ስምምነት አላደረገም የሚሉ አስተያየት ሰጭዎች ምን ምላሽ ይሰጣቸው?

ኢንጅነር ግዛቸው፡- እኛ እንደምናውቀው (እንደምናምነው) አሁን ያለው መኢአድ ህጋዊ መዋቅር ከማዕከል እስከ ታች ድረስ በጥሩ ሁኔታ ያለ ነው:: መጋቢት ሰባት ቀን የመኢአድ የም/ቤት አባላትና የአንድነት የም/ቤት አባላት በመኢአድ መሰብሰቢያ አዳራሽ ተሰብስበን ስለ ውህደቱ ተወያይተናል::ያን ጊዜ ያየነው አሁን አንተ ከምትለው የተለየ ነው:: አብዛኞቹ አመራሮች ውህደቱ በተገቢው መንገድ እንድፈጸም ሲጠይቁ ታዝቢያለሁ::

አብዛኛው አባላት የሚደግፉት ከሆነ እንደ ተቋም ውህደቱ ይሳካል ብዬ አምናለሁ:: ዲሞክራሲ ማለት ይሄ ነው:: ውህደቱን የሚያደናቅፍ ነገር ያለ አይመስለኝም::

በዚህ አይነት ሁኔታ አብዛኛው የመኢአድ አባላትና የአንድነት አባላት ደግፈውት ዲሞክራሲያዊ ቅድመ ውህደት ስለተፈጸመ እየጠነከረ የሚሄድ መሆኑ አያጠራጥርም:: መወሰን ያለበት ዲሞክራሲያዊ ባህል ስለሆነ::

የቀለም ቀንድ፡- በአንድ ወቅት መኢአድ ግትርና የዲሞክራሲ እንቅፋት መሆኑን እናንተን ጨምሮ ብዙ ተቃዋሚዎች በትብብር ለመስራት እንደተቸገራችሁ ስተናገሩ ትሰሙ ነበር፤አሁን መኢአድ ህን ችግሩን አስወግዷል ማለት ይቻላል ካልሆነስ ለውህደቱ አስቸጋሪ አይሆነባችሁም?

ኢንጅነር ግዛቸው፡- በዚህ ላይ ግንዛቤው የለኝም ግን ሁሉን ነገር ማየት ያለብን በዲሞክራሲ መነፅርና በህግ አካሄድ ነው ማየት አንዳንድ ነገር በትንሽ ነገር በሚዲያው በጣም ይጮሀሉ:: ስለ መኢአድ እኔ ብናገርም በስብእናም በስነ-ምግባርም አግባብነት የለውም:: ሰነዱ ላይ በትክክል አስቀምጠነዋል፤ ሁሉም መርሆዎች አሉ:: መኢአድም አንድነትም የሚዋሀዱት በእኩልነት መርህ ነው::

የቀለም ቀንድ፡-አንድነት ፓርቲ የሚደርጋቸው ውህደቶች ዋና አላማ ሌሎችን ዉጦ ራሱን ለማግዘፍ ይፈልጋል፤ለዚህም የብርሃንን ፓርቲ የሚያነሱ እና አሁንም የላዕላይ መ/ቤቱ እና የጠቅላላ ጉባኤው እውቅና ከሌለው መኢአድ ጋር ግልጽነት የጎደለው የቅድመ ውህደት እንቅስቃሴ የሚደርገው የሚሉ ወገኞች ቢኖሩ?

ኢንጅነር ግዛቸው፡- ይሄ የገዢው ፓርቲ አባባል ነው:: እኛ ዋናና ትልቁ አላማችን የቻልነውን መስዋዕትነት ከፍለን አንድ ጠንካራ ብሔራዊ አብይ ፓርቲ መፍጠር ነው:: ይሄ ደግሞ ራስን አግዝፎ ሌላውን ውጦ ሳይሆን ሁሉም ፓርቲ የሚዋሀደው በእኩልነት መርህ ነው:: ውህደት የአንድነት ስትራቴጃዊ አቅጣጫ ነው:: አንድነት የሚጓዘው (የሚያምነው) በእኩልነት መርህና በዲሞክራሲ ነው:: ማንም ማንንም የሚወጥበት መንገድ የለም:: በፊት የተዋሀድነው ከብርሃን ፓርቲ ጋር ነው ይሄ የስትራቴጂክ እቅድ አቅጣጫችን ስኬታማነት ነው:: አንድነት ሎሎቹን ፓርቲዎች ለመዋጥ አቅጣጫ ይዞ መጣ ፓርቲ አይደለም ::

የቀለም ቀንድ፡- አንድነት ፓርቲ ከኢህአዴግ በብዙ መንገዶች ያኮረፉ ሰዎች ይበዙበታል:: ከአሁን በፊት በአመራርነት የተለያዩ ቦታዎች ነበሩ አሁን በአባልነትና በተለያዩ የስራ መደቦች ላይ ያሉ አሉ:: ከዚህ አንፃር የፓርቲያችሁን እንቅስቃሴ በጥርጣሬ የሚያዩት ሰዎች አሉ እዚህ ላይ የሚያስተላልፉት ግልፅ መልዕክት?

ኢንጅነር ግዛቸው፡- በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ አንቀበለውም:: ኢህአዴግ የሆነ ሁሉ ሌላ ፖለቲካ ፓርቲ አይገባም ማለት አይደለም:: የኢህአዴግ አካሔድ ትክክል አይደለም ብለው ወጥተው የፈለጉት ፓርቲ መግባት መብታቸው ነው:: አንድነት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ቤት ነው:: ያም ሆነ ይህ ሰዎች የተለያየ የፖለቲካ አቋም ይዘው ስህተታቸውን አርመው ከመጡ መቀበል እንዳለብን እናምናለን::

እኛ የምናየው ድርጅቱ ውስጥ ገብቶ የሚያሳየውን ዲሞክራሲያዊ ተግባር ነው ፤ያለው ታሪኩን አርሞና ቀይሮ የኛን ፕሮግራም የሚቀበል ማንኛውም ኢትዮጵያዊ እንቀበላለን::

የቀለም ቀንድ፡- ሰርገው የሚገቡትን የገዢው ፓርቲና ሌሎች ሰዎችን ለመለየትና ለመከላከል ምን እየሰራችሁ ነው?

ኢንጅነር ግዛቸው፡- ገዢው ፓርቲ የሚልካቸው ሰዎች እኛ ጋር ሊኖሩ ይችላሉ፤ እኔ እንደውም በግልፅ ከሚመጡት ተሰውረው የሚመጡት ናቸው የሚያስቸግሩት:: በፓርቲዎች ውስጥ የመጠፋፋትና ሰርጎ የመግባት ሁኔታ አለ በተለይ በታዳጊ ሀገሮች ይሄ መፍትሔ የሚያገኘው በፓርቲው ውስጣዊ የአሰራር ስልት ነው::

ገዢው ኢህአዴግ በግልፅና በስውር የሚልካቸው ሰዎች ሊገቡ ይችላሉ:: መለየትና ማረጋገጥ ያለብን በአሰራር ነው:: ኢህአዴግ ድርጅቶችን (ፓርቲዎችን) የማዳከም አቅሙ ከፍተኛ ነው:: ይህን መዋጋት ያለብን በጠንካራ የፖለቲካ አቅም ነው::

የቀለም ቀንድ፡- ከመኢአድ ጋር ሊደረግ የነበረው ውህደቱ ከ2002ዓ.ም ጀምሮ እንቅስቃሴ እንደተጀመረ ይታወቃል፤ በተለይም ባለፈው መጋቢት ወር አካባቢ ጉዳዩ ጫፍ ላይ ደረሰ ሲባል ልታዘገዩት የቻላችሁት በሚፈጠረው ውህድ ፓርቲ ላይ በስልጣን ስላልተስማማችሁ ነው ነበር ለሚሉ ሰዎች ምን ይላሉ?

ኢንጅነር ግዛቸው፡- የአንድነትና የመኢአድ ውህደት በስልጣን ሽሚያ ምንም አይነት የተጓተተበት ሁኔታ የለም:: ድርድሩ የዘገየው ቴክኒካል በሆኑ ጉዳዮች ላይ ስንወያይ ነው:: ለምሳሌ ከመድረክ ውጡ አትውጡ የሚለው አንዱ ነው:: ሌላው የመዋቅር ጉዳይ ነው:: መዋቅር ላይ ልዩነት ነበረን ያንን ለማጥበብና ለማቀራረብ ያደረግነው እንጅ በስልጣን አለመሆኑን ሙሉ በሙሉ አረጋግጥልሀለሁ:: ወደፊት በሚፈጠረው ውህድ ፓርቲ ስልጣን የሚገኘው ዲሞክራቲክ በሆነ ምርጫ ነው:: በድልድል አይደለም::

የቀለም ቀንድ፡- ከሌሎቹ ጋር ውህደት ለማድረግ ያላችሁ እንቅስቃሴ ምን ይመስላል?

ኢንጅነር ግዛቸው፡- ዝግጁ ነን፣ ተቀዳሚ አላማችን አንድ ጠንካራ ተፎካካሪ ብሔራዊ ፓርቲ ለመመገንባት ሁሉም ፓርቲዎች ቢሰበሰቡ ተመራጭ መሆኑን እንገልጻለን::

የቀለም ቀንድ፡- በመጨረሻ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?

ኢንጅነር ግዛቸው፡- የማስተላልፈው መልዕክት አንደኛ ውህዱ ፓርቲ ከፍተኛ የፖለቲካ ጠቀሜታ ስለአለው ድጋፉን እንዲሰጥ፣ ሁለተኛ አንዳንድ ውህዱን የሚያደናቅፉ ቃላቶች የኢትዮጵያ ህዝብ አመለካከት ውስጥ እንዳይገቡ፣ ሶስተኛ ማንኛውም ፓርቲ አንድ ጠንካራ ብሔራዊ አብይ ፓርቲ ለመመስረት የሚያደርገው ሂደት የወደፊት የኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ስርዓት መሰረት ስለሆነ ውህደት እንዲያደርግ ጥያቄያችንን እና ጥሪያችንን እናቀርባለን::

የቀለም ቀንድ፡- ጊዜዎትን ሰውተው ለቃለ መጠይቁ ስለተባባሩኝ በጣም አመሰግናለሁ::

## በትምህርት ተቋማት...

ከገጽ 5 የዞረ

ገንዘባቸውን፣ጉልበታቸውን አሟጠው ከትምህርት ተቋማት የተሰጣቸውን ማስረጃ መጠቀም አለመቻል ከፍተኛ ኪሳራ መሆኑ እሙን ነዉ:: ለምሳሌ በአንድ ወቅት በተገኘ መረጃ መሰረት (2004/2005 ዓም መሆኑ ነዉ) በልህቀት ማዕከሉ ከተፈተኑት ተማሪዎች 17% ብቻ ማለፋቸውን ይገለጣል:: 83% ተማሪዎች ወደቀዋል ማለት ነዉ:: ህጋዊነት ከተሰጣቸዉ የትምህርት ተቋማት ትምህርታቸዉን በተገቢዉ መልክ አጠናቀዋል ተብለዉ የትምህርት መረጃ የተሰጣቸዉ ተማሪዎች ይህን ያህል ምን ታምር ቢፈጠር ነዉ የትምህርት ልህቀት ማዕከሉን ፈተና ማለፍ ያቃታቸዉ?

የትምህርት ተቋማትም የሚሰጡት ትምህርት ተማሪዎችን የሚያበቃ መሆኑን እና የሚሰጡት የትምህርት ማስረጃ በራሱ በቂ ነዉ ብለዉ ስለሚያምኑ በለሆሳስ እያጉረመረሙ የልህቀት ማዕከሉን ይቃወማሉ:: አንዳንድ ተቋማት በልህቀት ማዕከሉ የሚሰጠዉ ምዘና ለቀጣይ ትምህርት አቀባበል መስፈረት መሆኑን በሕግ ያልተቀመጠና ግልጽነት የጎደለዉ አሻሚ ሆኖብናል ሲሉ አሁንም በጓዳቸዉና በመስሪያ ቤታቸዉ ያማሉ:: በማስከተልም በህግ የወጣዉን የተማሪዎችን የቅበላ መስፈርትና ሌሎች ሕጎችን ይቃረናል ሲሉ ያልጎመጉማሉ:: በአዲስ አበባ መስተዳድር ሌላ የትምህርት ልህቀት ማዕከል ከማቋቋም ይልቅ ትምህርት ሚኒስቴር በስሩ ባቋቋማቸዉ ጽ/ቤቶች የትምህርት ተቋማትን የትምህርት ጥራት ይቆጣጠርና ይከታተል ዘንድ እንዲሁም የትምህርት ጥራትን በቀጥታ ትምህርት ተቋማት ላይ አጠናክሮ ይሰራ ዘንድ እራሱን ትምህርት ሚኒስቴርን በሁሉም ዘርፍ ማብቃቱ አይሻልም ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች መነሳታቸዉ አይቀርም:: ደግሞም ተገቢ ጥያቄዎች ናቸዉ::


ለትምህርት ተቋማት ተዓማኒነት ማጣት አስተዋጽኦ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ የትምህርት ልህቀት ማዕከሉ ተፅእኖ ከፍተኛ ነዉ የሚሉ ሮሮዎች ይሰማሉ:: ለማጠቃለልም የልህቀት ማዕከሉ የተቋቋመበት ሁኔታ በርካታ አሻሚ ጉዳዮችን ያቀፈ ነዉ:: የሕግ አወጣጥ ሂደትን አልተከተለም:: የስልጣን ፍሰቱ ከለሎች ሕጎች ጋር ይጋጫል፣ በሰዉ ኃይል ልማት ላይም ተጽዕኖ ፈጥሯል፣ በተቋማት ላይ ኢ-ተአማኒነትን ፈጥሯል፣ የትምህርት ተቋማትን ማስረጃ የመስጠት ሥልጣን ነጥቋል፣ የአተገባበር ሂደቱ በርካታ አወዛጋቢ ነጥቦችን የያዘ ነዉ:: እንዲሁም የልህቀት ማዕከሉን ፈተና ማለፍ በቀጣይ ትምህት ለማማር እንደ መስፈርት መቅረቡ አሉታዊ ጎኑ ከፍተኛ ሲሆን ከዚህም ዘሎ አንዳንድ ተቋማት ይሄንን አሰራ ተግባራዊ በማድረግ ትምህርት ለማስቀጠል ከልህቀት ማዕከሉ የሚገኙ መረጃዎችን እንደ ቁልፍ መስፈርት ሲወስዱ አንዳንድ የትምህርት ተቋማት ግን ቸልተኝነት ይታይባቸዋል:: ይሄም በአጠቃላይ በሃገሪቱ የተምህርት ሂደት ላይ አሉታዊ ጥላዉ የገዘፈ እንዳይሆን ያሰጋል:: ከዚሁ የትምህርት ልህቀት ፈተና ማለፍና አለማለፍ ጋር ተያይዞ ሥራ ለመቀጠር እንዲሁም እድገት ለማግኘት በተለያዩ መ/ቤቶች በተለያየ መንገድ የመተግበሩ ሁኔታም ትኩርተ የሚሻ ጉዳይ ነዉ::

ለዚህ አጠቃላይ ችግር መፍትሄ የሚሆነዉ ሕግ አውጭው ይህንን ሕግ ሲፈትሸው ነዉ:: ሕግ አውጪው የህግ ክፍተቱ የተፈጠረበትን ምክንያት አያይዞ ሊመረምረውም ይገባል::ከዚሁ ጋርም ተያይዞ ወደፊት በሕገ አወጣጥ ሂደቱ ወቅት የማኅበረሰቡ፣ የሕግ ባለሙያዎች፣ የተቋማት ተሳትፎ ሊኖር ይገባል:: እንዲሁም ከዚህ ቀደም የደረሰውን ጉዳት የሚያስተካክሉ መንገዶች በሕግ ሊቀየሱ ይገባል::

ከዝግጅት ክፍሉ:-ይሄን በሽንቁጥ አየለ የቀረበ የህግ ትንታኔ በመደገፍም ሆነ በመንቀፍ ከማንኛውም ወገን የሚመጣ የህግ ትንታኔ የምናስተናግድ መሆናችንን እንገልጻለን::

# ውህደቱ መኢአድን የማቀበል እና የማስዋጥ ሴራ ነው

ከአቶ አብርሃም ጌጡ በመኢአድ ከቀድሞ የወጣቶች ሃለፊ ጋር የተደረገ ቃለ-ምልልስ/አቶ አብርሃም ጌጡ በፖለቲካል ሳይንስ የመጀመሪያ ድግሪ ከአ.አ.ዩ እና በህዝብ አስተዳደር ሁለተኛ ድግሪቸውን ከውጭ ሀገር ዩንቨርሰቲ ወስደዋል/



የቀለም ቀንድ፡-በመጀመሪያ ሙሉ ስምና በመኢኣድ ውስጥ ያለዎትን የስራ ድርሻ?

አቶ አብርሃም፡- ስሜ አብርሃም ጌጡ እባላለሁ በመኢኣድ የነበረኝ ድርሻ ከ2003ዓ.ም ጠቅላላ ጉባኤ በፊት ወጣቶች ‹ጉዳይ ሃላፊ ከዚያ በኋላበ ተፈጠረው ችግር ምክንያት ዶ/ር ታዲዮስ በሚመሩት የመኢአድ ክፍል ምክትል ሰብሳቢና የድርጅት ጉዳይ ሃላፊ ነኝ።

የቀለም ቀንድ፡-የመኢአድ ፕሬዘዳንት አቶ አበባው ውህደቱን እንደገፈዋለን የህዝብ መሰረት እና ድጋፍ ያለው እንቅስቃሴ ነው ብለው እየገለጹ ባለበት ሰዓት እናንተ ውህደቱን እንዴት ትቃወማላችሁ?

አቶ አብርሃም፡-በመሰረታዊነት እኛ ውህደቱን አንቃወምም።የምንቃወመው ውህደት ለመዋሃድ ህግና ደንብ መከበር አለበት፣በፓርቲው ውስጥ የተፈጠረው የአመራር ችግር ባልተፈታበት ጠንካራ አመራሮች ውጪ ባሉበት ሁኔታ የሚደረገው ውህደት አፈራሽ እንጂ ውህደት መስሎ ስለማይታየን ሂደቱን እንቃወማለን እውቅናም የለንም።

የቀለም ቀንድ፡-የላዕላይ ምክር-ቤትና ጠቅላላ ጉባኤ እንዳይጠራና ከውሳኔ ውጭ ውህደት እንዲፈጸም አቶ አበባው ለምን የፈለጉ ይመስላችኋል? አላማቸውስ ምን ይሆን ብላችሁ ትገምታላችሁ?

አቶ አብርሃም፡-በብዙ መንገድ መግለጽ ይቻላል፤ በማን አለብኝነት ውህደት ሲሉ ተልእኮን ከማስፈጸም ውጪ ሌላ አላማ አላቸው ብለን አናስብም ።ለውህደቱ፣ለትግል፣ለለውጥ ቀናኢ አመለካከትና ቁርጠኛ አቋም ቢኖራቸው ኖሮ ቀደም ሲል ሊያደረጉት የሚገባ በሰርጎ ገቦች አማካኝነት የተፈጠረውን የፓርቲ የውስጥ ችግር በሰከነና በበሰለ የፖለቲካ ቋንቋ ፈትቶ ውህደቱ ቢፈጸም ነበር ውጤታማ የሚሆነው።በተለይ በአሁኑ ሰዓት ውህደት መፈለጋቸውን በሁለት አቅጣጫ ነው የምናየው፤አንደኛ እኛ ባደረግነው ትግል ራቁታቸውን የቀሩ ይመስለናል እና ብቻቸውን ስለቀሩ ወያኔ የሰጣቸው ማህተም በቆረጣ ሰጥተው ፓርቲውን ለማቀበል እና ለማስዋጥ ይመስለኛል ሌላው ደግሞ ከጀርባ ሆኖ ገዢው ፓርቲ ይጫናቸዋል ብለን እናስባለን። በተጨማሪም አቶ አበባው ገብቷቸውም ይሁን ሳይገባቸው ቀጥታ ወስደው ለእነሱ ለማቀበል ያሰቡ ይመስለኛል።

የቀለም ቀንድ፡- በመሰረታዊነት ውህደቱን ከደገፋችሁ ውህደቱ ምን ምን ነገሮችን ማሟላት ነበረበት ብላችሁ አስባችሁ ነው?

አቶ አብርሃም ፡- በመጀመሪያ ደረጃ የመርህ ጉዳይ አለ፣የአካሄድ ጉዳይ አለ፣የአመለካከት ጉዳይ አለ የሚነድፏቸው ፖሊሲዎች ጉዳይ አለ እነዚህን ጉዳይ ጠቅልለህ ሳታይ ውህደት አይባልም። የውህደቱን ሒደት ብቻ ነው የምንቃወመው።ሂደቱንም የምንቃወመው እንደሚታወቀው መኢአድ ሰፊ ችግር ያለበቱ ፓረቲ ስለሆነ ነው። ገዢው ፓርቲ አስርጎ ያስገባቸው ቡድኖችና ግለሰቦች አማካኝነት የተፈጠረ ክፍተት አለ፤እሱ ክፍተት መጀመሪያ ነባሩ እውነተኛውና ትክክለኛው የላእላይና የጠቅላላው ጉባኤው ተሰብስበው ከማን ጋር መዋሃድ እንዳለበት፡ ከውህደቱ በኋላ ቀጣይ የሚነደፈው ህዝባዊ ትግል ምን መምሰል እንዳለበት ቁጭ ብሎ ባለወሰነበት ሂደት ላይ ውህደቱ ውህደት አይደለደም ። ይሄ ዝም ብሎ የማስመስል ነገር ነው ፤ህዝቡ ውህደት ይፈልጋል ህዝቡ ውህደት ሰለፈለገ ለውጥ ይመጣል ብሎ ማለት አይቻልም።ምክንያቱም ብዙ ውህደቶች፣ግንባሮች ነበሩ ግን በማግስቱ ሲፈርሱ ነው ያየነው፤ ለህዝብ ጠብ ያለ ስራ የሰሩት የለም። ምክንያቱ ግልጽነት የጎደለው ውህደት በመፈጸማቸው ነው።

የቀለም ቀንድ፡- በዚህ የውህደት እንቅስቃሴ ውስጥ የቀድሞው የድርጅቱ ፕሬዘዳንት ኢ/ር ሃይሉ ሻውል ከየትኛው ቡድን ጋር ናቸው ውህደቱን ደግፈዋል ወይስ ደግሞ ውህደቱ የመርህ ችገር አለበት ብለው ነቅፈዋል እናንተስ እርሳቸውን አግኝታችሁ የማነጋገር ዕድሉ ነበራችሁ?

አቶ አብርሃም፡-እሳቸውን በአካል አግኝተን አላነጋገርናአውም ግን በእርገጠኝነት ኢ/ር ሃይሉ ሻውልም ቢሆኑ ፓርቲው ለሌላ ይሸጥ፣ይለወጥ ወይም ይዋጥ ብለው ይፈቅዳሉ አልልም።ጤነኛ አመለካከት ካላቸው ችግሩ ባልተፈታበትና በደበዘዘበት ሁኔታ አንድ ግለሰብና አንድ ማህተም ሄዶ ውህደት ይፈጽም ብልው ይላሉ የሚል እምነት የለኝም፤ይሄ ነው እምነታችን ከሳቸውም ባህሪ እንደምረዳውና እሳቸውም ይዘውት ከነበረው ሃላፊነት አንጻር ስታየው ሊሉ የሚችሉት ምንድነው ትክክለና የፖለቲካ ውሳኔ የሚወስነው የድርጅቱ ባለቤት የሆነው የጠቅላላ ጉባኤው ተጠርቶ በትክክለኛው መስመር ውሳኔ ሳያሳርፍ ውህደት ይፈጸም ብለው ያስባሉ ማለት ያስቸግራል።

የቀለም ቀንድ፡-አሁን መኢአድ ወደ ተለያዩ ትንንሽ ቡድኖች እየተፈረካከሰ መሆኑ ይታወቃል በዚህ ሁኔታ መኢአድን መመለስና ወ ደቀድሞው ጥንካሬው ማምጣት ይቻላል ተብሎ ይታሰባል? ካልሆነስ በዚህ ከቀጠለ የመኢአድ እጣፋንታ ምን ሊሆን ይችላል?

አቶ አብርሃም፡- መኢአድ ባሁኑ ሰዓት በመላው ሃገሪቱ ያሉ አባላትን እየሰበሰበ ወደ አንድ ሃይል እየመጣ ይመስለኛል። ዶ/ር ታዲዎስ ቦጋለ የሚመሩት ሃይል አለ አዲስ አበባ ውስጥ ሙሉ መዋቅር አለው የስራ አስፈጻሚው አመራሩ እንዳለ በተዋረድ የተዋቀረ ነው። በእርሳቸው አማካኝነት ያኮረፈውን አባል እያመጣን ስለሆነ መኢአድ ቀጣይ እራሱን ችሎ ያታለመውን ለውጥ ያመጣል ብለን እናምናለን።

የቀለም ቀንድ፡- ከውህደቱ ጋር ተያይዞ ህጋዊ ነኝ ብሎ ውህደት የፈጸመ ቡድን በአቶ አበባው የሚመራ ቡድን አለ፤ከውጭ እናንተ የምትሉት በነ ዶ/ር ታዲዎስ የሚመራው ቡድን አለ። አሁን ባለው ሁኔታ እነዚህ ቡድኖች ታርቀው መኢአድ እንደመኢአድ ሆኖ መቀጠል ይችላልን?

አቶ አብርሃም፡- መኢአድ ይህ ችግር ሊገጥመው የቻለው በገዢው ፓረቲ እረጉም ክንድ ነው።ነገር ግን በዚህ በኩል የውሸት ማህተም የያዘ ህጋዊ መሰረት የሌለው አንድ እና ሁለት ገለሰቦች ዝም ብለው ያለ ጠቅላላ ጉባኤው እውቅና ማህተም እየመቱ ያሉ ግለሰቦች ቢኖሩም ፤ በዶ/ር ታዲውስ የሚመራው የመኢአድ አካል ግን ህጋዊ መሰረት አለው የምንለው ያለምክንያት አይደለም።አንደኛ 2003 ዓ.ም የነበረው ጠቅላላ ጉባኤ በሙሉ ድምጽ ሃላፊነቱን ሰጥቶት ስለነበር ሁለተኛም ቀደም ሲል በነበረው የአመራር ችግር በተፈጠረው ክፍተት አማካኝነት ተከስን ስለነበር እና የክሱን ጭብጥ ሲያየው የነበረው ፍ/ቤት መሰረታዊ ጭብጥ እንደሌለው የፓረቲው ችግር መፈታት ያለበት በፖለቲካዊ መፍትሄ እንጂ በፍ/ቤት እንዳለሆነ አረጋግጦ ወስኖ ለምርጫ ቦርድ ሰጥቶታል።ምርጫ ቦርድ ዝም ብሎ አንጠጥሎ ይዞታል።አሁን አቶ አበበው ግራ ቀኙን አይተው ከተመለሱ ተመለሱ። ካለተመለሱ ግን ፍ/ቤት ወስኖልናል ህጋዊ ሰውነት አለን ስለዚህ የምናደርገው ምንድን ነው ጠቅላላ ጉባኤ ጠርቶ መኢአድን መኢአድ አድርጎ መቀጠል ብቻ ነው ።

የቀለም ቀንድ፡- ላለፉት 22 ተከታታይ አመታት በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉ ተቃዋሚዎች በጥንካሬውና ቁርጥኛ ታጋዮቹ ገዢውን ፓርቲ እየፈተነ በመሆኑ በውህደት መልክ ከገዢው ፓርቲ ባኮረፉ ሰዎች ከተሞላው ድርጅት ጋር ሄዶ በመቀላቀል በእጅ አዙር በገዢው ፓርቲ እጅ ውስጥ ለማስገባት ነው የሚባል አስተያየት ይሰጣል በዚህ ለይ ምን አስተያየት አለዎ?

አቶ አብርሃም ፡- ይሄንን ሃሳብ እኔ እጋራዋለሁ፤እዚህ ላይ መሰመር አለበት በአምባገነኑ የኢህአዴግ ስርዓት የውስጥ ትግል ተሸንፈው የወጡ፣ በርዕዮ-አስተሳሰብ፤ ባመለካከት ከኢህአዴግ ያልወጡ ልባቸውም ሆነ አጥንታቸው ኢህአዴግ የሆነ፣ በእውነተኛ ትግሉ ውስጥ ያሉ ፓረቲዎችን ለማደናቀፍ ነው እየሰሩ ያሉት፤ይህ ትልቅ ስራ እየተሰራበት ያለው ባለፉት ለ22 ዓመታት ኢህአዴግን ሲፎካከር የነበረው መኢአድ ለማክሰም የተጀመረው ስልት ነው ።ለዚህ ነው መሰረታዊ ችግር አለ የምንለው ይሄ መሰረታዊ ችግር ሳይፈታ ወደ ውህደት መሄዱ በሰላማዊ ትግል በእውነተኛ አጀንዳ የሚታገሉ ሓይሎችን እንደመገታል ይቆጠራል እንላለን።አሁን አንድነትን እየመሩ ያሉ ጥቂት ግለሰቦች አጀንዳቸው ይሄ ብቻ ነው ብለን እናምናለን።

የቀለም ቀንድ፡- ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልዕክት ካለ?

አቶ አብርሃም፡- ሁላችንም በምናደርገው የፖለቲካ ተሳትፎ ህዝቡ ነጻ መውጣት አለበት ።ይሄ ህዝብ ጨለማ ውስጥ ያለ ህዝብ ነው፤ዲሞክራሲ ይፈልጋል፣ፍትህ ይፈልጋል፣የህግ የበላይነትን ይፈልጋል።ስለዚህ ይህን ለማድረግ ትግለ ያስፈለጋል፤ለመታገል ደግሞ የነጠረ አቋም መያዝ ያስፈልጋል።በዚህ መሰረት የሁሉም ንጹህ ልቦናና ንጹህ አእምሮ ያለው ኢትዮጵያዊ ትግልና ተሳትፎ ተጨምሮበት ትግሉ ትግል ሆኖ ውጤታማ ሆኖ በሀገራችን ሰላምና ዲሞክራሲ ሰፍኖ የሀገራችን ሉአላዊነት አስከብረን እና ታላቅ ሆና እንድትቀጥል የሁላችንነም ትግል ይጠይቃል።በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ የመኢአድ ደጋፊዎች በመኢአድ ላይ የተቃጣው የማፍረስና የመዋጥ ዘመቻ እንዲቆም ሁሉም ሰው የድርሻውን እንዲወጣ በዚህ አጋጣሚ መናገር እወዳለሁ።

የቀለም ቀንድ፡- አመሰግናለሁ።

# መኢአድ ውዝፍ እዳ ያለበት ፓርቲ ነው

ከመኢአድ ም/ፕሬዘዳንት ከአቶ ተስፋዬ መላኩ ጋር የተደረገ ቃለ-ምልልስ



የቀለም ቀንድ፡- ስምና በመኢአድ ውስጥ ያለዎት የስራ ድርሻ ምንድን ነው?

አቶ ተስፋዬ፡- ተስፋዬ መላኩ እባላለሁ የመኢአድ ምክትል ፕሬዝዳንት ነኝ።

የቀለም ቀንድ፡- በም/ፕሬዚዳንትነት ለምን ያህል ጊዜ አገለገልዋል?

አቶ ተስፋዬ፡- ባለፈው ሀምሌ 13 እና 14 በተደረገው ምርጫ ነው የተመረጥሁት። ከአሁን በፊት በ2002 እና 2003 የምስራቅ ቀጠና ተጠሪ ሁኜ አገልግያለሁ። የምስራቅ ቀጠና ተጠሪ ማለት ደግሞ በምክትል ፕሬዝዳንትነት ማረግ ማለት ነው። አሁን ባለውና በተሻሻለው ደንብ መሰረት 3ኛው ም/ፕሬዝዳንት እኔ ነኝ።

የቀለም ቀንድ፡- ባለፈው ሰኔ 1 ቀን 2006 ዓ.ም መኢአድ ከአንድነት ጋር የቅድመ ውህደት ስምምነት ፊርማ ተፈራርመዋል። በዚህ ላይ ያለዎት አስተያየት ምንድን ነው?

አቶ ተስፋዬ፡- በውህደቱ ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥቼ ስንቀሳቀስ ነበር። መጋቢት 11 በነበረው የሁለቱም ፓርቲዎች ስብሰባ ውህደቱ መጋቢት 18 እንዲደረግ ስምምነት ነበር። ውህደቱ ሰላማዊና ህጋዊ እንዲሆን በጣም ብዙ ትግልና መስዋዕትነት አድርጊያለሁ።

በመሀል ላይ አለመግባባት በመኖሩ ትንሽ ተቆጥቤ የነበር ቢሆንም። የውህደቱን ጉዳይ ተቀብየ ቀኑ እስኪደርስም በጉጉት ከሚፈልጉት አንዱ በመሆኔ ውህደቱ ጠቃሚ ነው የሚል ፅኑ አመለካከት አለኝ።

የቀለም ቀንድ፡- ከፓርቲው ጋር ያላችሁ መግባባት እየቀነሰ እንደመጣ ነግረውኛል። ያልተግባባችሁበት መሰረታዊ ምክንያት ምን ነበር?

አቶ ተስፋዬ፡- ከጥቅምት አጋማሽ ጀምሮ እስከ መጋቢት 11 ድረስ በድርድሩ ላይ ነበርኩ፤ የቃለ-ጉባኤ ፀሐፊ ነበርኩ ያን እየሰራሁ
ነበር በመሀል አቶ አበባው በደንቡ ላይ በመፈረሜና በማፅደቁ ይሄ ለምን ተደረገ በማለት በከፍተኛ ውንጀላ ከፍተኛ ስቃይ ያደርሱብኝ፤ የአካል ጥቃት ጭምር ደርሶብኛል ። አሁን መጥቀስ በማልፈልጋቸው አካላት በውህደቱ ዙሪያ በምንቀሳቀስበት ሰዓት ከፍተኛ ጫናና ዛቻም ነበረብኝ።

የቀለም ቀንድ፡- ውህደቱ እንዲሳካ ነው ወይስ እንዲስተጓጎል?

አቶ ተስፋዬ፡- ውህደቱ ለምን እንዲሰምር ትፈልጋለህ፣ ውህደት ውህደት ለምን ትላለህ፣ ውህደቱ የራሱ ችግር አለበት ባዮች
አሉ። ውህደቱን የማይፈልጉ ሰዎች እኔን ለማስቆም ጥረት እያደረጉ ነበር። መረጃዎቹን እያሰባሰብኩ ነው፣ እኔ እንቅስቃሴውን ትቻለሁ ፕሬዝዳንቱ በራሱ በፈለገው አካል ውህደቱን እያካሄደ ነው። በውህደቱ ቅድመ ፊርማ ግን ተስማምቻለሁ ።

የቀለም ቀንድ፡-አቶ አበባው ውህደቱ የህዝብ ድጋፍና መሰረት ያለው መሆኑን እየገለፁ ነው እናንተ እና አብዛኛው
አባላት ደግፋችሁታል?

አቶ ተስፋዬ፡- አዎ ደግፈነዋል። አስፈላጊ ነው፣ ከጥቂት አባላት በስተቀር ሙሉ በሙሉ የመኢአድ ደጋፊዎች
ይፈልጉታል።

የቀለም ቀንድ፡- ከውጪ የታገዱት ቡድኖች ሳይካተት ውህደት አይካሄድም ያሉ ናቸው ወይስ ከአንድነት ጋር የሚደረገው
ውህደት ለመኢአድ አይጠቅመውም የሚሉት?

አቶ ተስፋዬ፡- በተለያዩ መስኮች ላይ ያሉትን ነገሮች ዙሪያ ገብ መመልከት ያስፈልጋል። ሁሉንም ነገሮች መፈተሽ አስፈላጊ ነው።
ይህንን መንግስት መጣልና ማንበርከክ የሚቻለው ስትጠናከርና አንድነት ስትፈጥር ነው። አንደኛ በአንድነትም ይሁን በመኢአድም
በኩል የውስጥ ችግር መፈታት አለበት ሁለተኛ መኢአድ በተለያዩ ምክንያቶች በራሱ ህግ ያገለላቸውን አባሎች በጠረጴዛ ዙሪያ ማወያየትና ችግሩን መፈታት አለበት። በውህደቱ ላይ ምንም አይነት ጥላቻ መድረስ የለበትም።

የቀለም ቀንድ፡- መኢአድ በውስጡ የተፈጠረውን ችግር ሳይፈታ ወደ ውህደት ለመምጣት የተጣደፈበት ምክንያት ምንድን ነው?

አቶ ተስፋዬ፡- እነዚህ የታገዱት ሰዎች የፓርቲውን ትክክለኛ ማህተም ለምርጫ ቦርድ ወስደው የሰጡ ናቸው። ይሄ ደግሞ አግባብነት
የለውም። እነዚህን በውጭ ያሉትን ሰዎች እንድመለሱ ግን ከፍተኛ ጥርት እያደረግን ነው። በቅርቡ
የወጡትም አባላት በውይይት በድርድር መመለስ እንዳለባቸው አምናለሁ። በተለያ ምክንያት የወጡትን አባሎች ሰብስቦ ውህደቱን መፈፀም ተገቢ መሆኑን ጭምር አስማማለሁ።

የቀለም ቀንድ፡- የላዕላይ ም/ቤትና ጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ውጪ ነው ውህደቱ የተፈፀመው አቶ አበባው ይህን ለምን ፈለጉ
አላማቸውን ምንድን ነበረ ብላችሁ ትገምታላችሁ?

አቶ ተስፋዬ፡- ወደ ፊት ወደ ዋናው ውህደት ለመሄድ ጠቅላላ ጉባኤ መጠራት አለበት።ላዕላይ ም/ቤቱ ተወያይቶ ለጠቅላላ ጉባኤው ያቀርባል ጠቅላላ ጉባኤው ካሳለፈው በኋላ ውህደቱ ይሄዳል። ካልደገፈው ግን ስምምነቱ ይፈርሳል።

የቀለም ቀንድ፡- የውህደቱ ስምምነት ሲደረግ ነው ተብሎ ጠቅላላ ጉባኤውን መጥራት አይቀድምም ነበር?

አቶ ተስፋዬ፡- ይቀድማል ከጠቅላላ ጉባኤው ላዕላይ ም/ቤቱ ነው የሚቀድመው። ይህን ያስቀመጠው ህግ ነው ወደ ጠቅላላ
ጉባኤው ሲኬድ አጀንዳ ተይዞ መሆን አለበት ያንን የሚያደርገው ደግሞ ላዕላይ ም/ቤቱ ነው።

የቀለም ቀንድ፡- አቶ አበባውና ውህደቱን የደገፉት አመራሮች የላዕላይ ም/ቤቱንና ጠቅላላ ጉባኤውን ለውህደቱ እየጠበቀ ነው
ማለት ነው?

አቶ ተስፋዬ፡- አዎ እየጠበቅን ነው ያለነው። በርግጥ አንዳንድ ሚዲያ ላይ ሀምሌ 5 እና 6 ጠቅላላ ጉባኤ እናደርጋለን የሚል
አይቻለሁ። እስከ አሁን ድረስ በስራ ምክንያት ወደ ቢሮ አልገባሁም። አጀንዳ አልሰራንም። ውስብስብ ችግር ነው ያለው ይህ
ደግሞ ገዢው ፓርቲ አስርጎ ያስገባቸው ሰዎች የሚፈጥሩት ችግር ነው ብዬ እገምታለሁ።

የቀለም ቀንድ፡- ኢንጂነር ሀይሉ ሻውል በነበሩበት ጊዜ እራሳቸው የሚፈልጓቸውን ሰዎች ስለወከሉ ነው ይሄ ሁሉ ትርምስና
ግጭት የተከሰተው የሚባልም አስተያት አለ እርሶዎ ምን ይላሉ?

አቶ ተስፋዬ፡- በወቅቱ እኔ ነበርኩ በ400 የጠቅላላ ጉባኤ አባል ምርጫ ነው ሀላፊነት የተሰጠን፣ ተጠያቂነቱንና ሃላፊነቱን በጋራ
ነው መውሰድ ያለብን ፤አቶ አበባውንም ሆነ እኔን ያስቀመጠን የጠቅላላ ጉባኤ አባሉ ነው።ይሄንን ስራ አስፈጻሚ ለመገምገም የሚችል ጠቅለላላ ጉባኤ ባለመጠራቱ እስከ ውዝፍ እዳው ተቀምጦ ነው ያለው ፤የፖለቲካ እዳ አለበት ለዚህ ነው ቤቱ ተዘግቶ የተቀመጠው።

የቀለም ቀንድ፡-በመጨረሻ የሚያስተላሉፉተ መልእክት ካለ?

አቶ ተስፋዬ፡-ለዚች ሀገር ነጻነት ሁሉም የበኩሉን ጥረት ማድረግ አለበት፤ወደ ነበረበችበት አንድነቷ፣ክብሯ፣ጥንካሬዋ ለመመለስ የሁላችንም ርብርብ ያስፈልጋል።አመለካከታችን አንድ መሆን አለበት።ሁላችንም ወደ ሃገራዊ አጀንዳ ገብተን መንቀሳቀስ አለብን።

የቀለም ቀንድ፡- አመሰግናለሁ።

መልዕክተ ኢትዮጵያ

# ለኢትዮጵያ ከምስራቅም ሆነ ከምዕራብ የሚቀዳ የፖሊሲ ምንጭ የለም

## ለውጭ ፖሊሲ ከመጨነቅ በፊት . . .



ሸንቁጥ አየለ
(shenkutayele@yahoo.com)

የኢትዮጵያዉያን ምሁሮችና ፖለቲከኞች የኢትዮጵያን ድህነትና ብልጽግና አንዴ ከምስራቅ አንዴም ከምዕራብ ፈልፍለዉ ሊያገኙት ሲባትቱ:: በአንድ ወቅት ምዕራቦች ላይ የነበረዉ ተስፋ ሲሰበር እንደገና ወደ ምስራቅ ማንጋጠጥ ሆነ:: የምስራቁ የፈዉስ ምንጭ አልመነጭ ሲል ዳግም ወደ ምዕራብ:: የምዕራቡ የድህነትና የፈዉስ ምንጭ አንደሚፈለገዉ አልፈስ ሲል ዳግም ወደ ምስራቅ:: እናም አሁንም ሀገሪቱን በሚገዙት ሀይሎች: ነገ ሀገሪቱን የመግዛት ወይም የመምራት እድል ቢገጥመን ብለዉ በሚባትቱት ተቃዋሚ ሀይሎች እንዲሁም በሀገሪቱ ምሁራን መሃከል የሚደረገዉ የሀሳብ ግብግብ እንደጦፈ ይገኛል::የኢትዮጵያ ብጽግናና ድህነት ከምስራቅ ወይስ ከምዕራብ የሚመነጭ የሚል ተጠይቆች ይጎርፋሉ:: የኢትዮጵያ የዉጭ ፖሊሶ መሰረታዊ ቅኝቱ ምን መህልቅ ላይ ቢቆም ይበጃል? የሚሉት ጥያቄዎች ቀጣይ ያልተቁዋጩ የሀሳብ ትንቅንቅ የሚደረግባቸ ጉዳዮች ናቸዉ::

አንዲት ሀገር ሀገር ነኝ ካለች ስለ ዉጭ ፖሊሲዋ ከመጨነቅ በፊት ሙሉ ለሙሉ መጀመሪያ በራሱዋ እግር መቆም አለባት:: እማንም ላይ መንጠልጠል የለባትም:: ወደ ሌላዉ ከመንጠልጠልና ስለ ወጭ ፖሊሲ ከመጨነቅ በፊት መጀመሪያ ወደ ዉስጥ የማዬት ፍልስፍና በጥልቅ ሊኖራት ይገባል:: ቀጥሎም ግንኙነት ልትመሰርታቸዉ ስለምታስባቸዉ ዉጫዊ ሀይሎች በቂ ትንታኔ ማድረግ አለባት::ደግሞም የምዕራባዉያንን እና የምስራቃዉያንን ፖለቲከኞች ስነልቦና በሚገባ ሁኔታ ጠንቅቃ መረዳት አለባት:: እናም መጀመሪያ ስለምስራቅና ምዕራብ ፖለቲከኞች ተጨባጭ መገለጫ ጥቂት ጥቂት ነጥቦችን አንስቶ መወያዬት ተገቢ ነዉ::

የምዕራብ ፖለቲከኞች ከጥንት ጀምሮ ሀይለኛ ጦረኞች: ብልጦች: ብልሆች: ሸፍጠኞች: በሀገራቸዉ ጥቅም ላይ መደራደር የማያዉቁ: ማንኛዉንም የሌላ ሀገር ህዝብ መስዋዕት አድርገዉ ሀገራቸዉን እና ህዝባቸዉን ወደፊት የሚያራምዱ ናቸዉ:: የሀገራቸዉን ጥቅም ለማስከበር ከዲያቢሎስ ጋር የሚደራደሩ ካስፈለገም ከዲያቢሎስ ጋር እንኩዋን የሚዋጉ ሀያላን ጦረኞች ናቸዉ:: ከማንኛዉም ሀገር ጋር የሚያደርጉት መስተጋብር በዳሪዊኒዝም ፍልስፍና የሚመራ ነዉ:: ረግጦ ማለፍ:: ጥሎ ማለፍ:: ብሎም የራሳቸዉን ጥቅም በአስተማማኝ ማስጠበቅ::

ከሌላዉ ሀገር ህዝብ ጋር መስተጋብ ሲያደርጉ የፖለቲካ መርሃቸዉ ዳርዊኒዝምና ዳርዊኒዝም ብቻ ነዉ:: ዲሞክራሲ: ሞራል : እዉነትና ሀቅ የዲፕሎማሲ ቁዋንቁዋና በመድረክ ላይ መዉረግረጊያ ስልታቸዉ ብቻ ነች:: ሀይለኛና ጨካኝ ፖለቲከኞች ናቸዉ:: ታላቁ መጽሀፍ እንደሚለዉ የዚህ አለም ልጆች ከብርሃን ዓለም ልጆች ይልቅ ለመንግስታቸዉ ጨካኝ ናቸዉ የሚላቸዉ በትክክል እነዚህን ሳይሆን አይቀርም:: ቢሆንም ብልህ ባል እዉቀትና በስርዓት የሚመሩ ፖለቲከኞች ስለሆኑ ሊከበሩ እንጅ ሊናቁ ወይም ሊጠሉ አይገባም:: ለነገሩ ማንም ቢጠላቸዉ ጉዳያቸዉ አይደለም:: የመንግስታቸዉን እና የህዝባቸዉን ጥቅም በማንኛዉም መንገድ የሚያረጋግጡ ጀግኖች ናቸዉና ጥላቻና ንቀት ከቶም ልባቸዉን ድጭ አያደርግባቸዉም::የምዕራብ ፖለቲከኞች ስም በዲሞክራሲ እየማሉ ዲያቢሎሳዊ ስራቸዉን ግን ከመጋረጃ ጀርባ በመላዉ ድሃ ሀገራት ላይ ሲጭኑ የሚያሳስባቸዉ ወንድማማችነት ሰበአዊነትና የየሃገራቱ ዲሞክራሲና ብልጽግና አይደለም:: ሀፍረታቸዉን ወደጎን ጥለዉ ግብረሰዶማዊነትን እንኩዋን ካልተቀበላችሁ በርሃብ የሚያልቀዉን ህዝባችሁን አንረዳም እስከማለት የሚደርሱ ብሎም እነሱ ያመኑበትን ነገር በማንም ሀገር እምነት እና ባህል ላይ ለመጫን ወይም የፖለቲካ ጥቅማቸዉን በሀገራት የመፍረስ ህልዉና ላይ እንኩዋን ለማራመድ ወደሁዋላ የማይሉ ጨካኝ ፖለቲከኞች ናቸዉ::

ምስራቃዉያን (በዋናነትም ሩሲያ ቻይ ጃፓን እንዲሁም ሌሎች ሀገራት) ኩሩና ሀይለኛ ህዝቦች ናቸዉ:: በባህላቸዉ የታነጹ : ለማንነታቸዉ እስከመጨረሻዉ የሚሞቱና የጠላቶቻቸዉ ምላስ ማዉጫ መሆንን የሚጠሉ ህዝቦች ናቸዉ:: እነዚህ ህዝቦች ጠላቶቻቸዉን ጠንቅቀዉ የሚያዉቁ በአባታቸዉ ሀገር ላይ የማይደራደሩና ታላላቅ መሪዎችን በተከታታይ ማፍለቅ የሚችሉ ህዝቦች ናቸዉ::

> ... ሀፍረታቸዉን ወደጎን ጥለዉ ግብረሰዶማዊነትን እንኩዋን ካልተቀበላችሁ በርሃብ የሚያልቀዉን ህዝባችሁን አንረዳም እስከማለት የሚደርሱ ብሎም እነሱ ያመኑበትን ነገር በማንም ሀገር እምነት እና ባህል ላይ ለመጫን ወይም የፖለቲካ ጥቅማቸዉን በሀገራት የመፍረስ ህልዉና ላይ እንኩዋን ለማራመድ ወደሁዋላ የማይሉ ጨካኝ ፖለቲከኞች ናቸዉ:: ...

ያፈለቁዋቸዉን መሪዎችም እስከመጨረሻዉ የሚከተሉና የሚያከብሩ ሀይለኛና ኩሩ ህዝቦች ናቸዉ:: ከእነዚህ ህዝቦች የሚወጡም መሪዎች እንደ ምዕራብያዉያን መሪዎች ከሌላ ሀገር ህዝቦች ጋር መስተጋብር በሚያደርጉበት ወቅት የራሳቸዉን ፍላጎት በሌላዉ ሀገር ላይ በአስተማማኝ መጫን ብቻ ሳይሆን የገቡበትን ህዝብ አድቅቀዉ እና ረግጠዉ የሚገዙ ናቸዉ:: ሩሲያ ባንድ ወቅት በኢትዮጵያና በበርካታ የአለም ህዝቦች ላይ ይሄን ጨካኝ ስራ ፈጽማለች:: ልክ ዛሬ አሜሪካኖቹ በዲሞክራሲ እየማሉ ዲያቢሎሳዊ ስራቸዉን ግን ከመጋረጃ ጀርባ በመላዉ ድሃ ሀገራት ላይ እንደሚተዉኑት ማለት ነዉ:: ዛሬ ቻይናዉያን የመላዉ ታዳጊ ሀገራትን ጨቅላ ኢንዱስትሪዎች እየዋጡና እያኮሰመኑ ለአምባገነን መሪዎች ጥቂት ፍርፋሪ እርዳታ እየበተኑ የየሀገራቱን የመጭ ጊዜ ኢኮኖሚ ከአናቱ ተቆጣጥረዉታል:: በታዳጊ ሀገራት ብቅ ብቅ የሚሉት ጨቅላ ኢንዱስትሪዎች ለአንዴና ለመጨርሻ ጊዜ በቻይናዉያን ነጋዴዎችና ባለሃብቶች ይዋጣሉ ወይም ደግሞ የየሀገራቱ ገባያዎች የቻይና ሸቀጥ ማራገፊያ ስለሚሆኑ ምንም አይነት ሀገራዊ ምርት የማስተናገድ ፋላጎትም ሆነ አቅም አይኖራቸዉም:: ብልጦቹና ጨካኞቹ የቻይና ፖለቲከኞች እኛ በሃገራት ፖሊሲ ዉስጥ ጣልቃ አንገባም የሚል አልምጥ ዲፕሎማሲያዊ መልስ ቢሰጡም የሚገቡባቸዉን ሀገራት የኢንዱስትሪ የኢኮኖሚ እና አጠቃላይ የልማት ፖሊሲ የሚዘዉሩት እነሱ ናቸዉ::

ምስራቃዉያን ፖለቲከኞች በሌላዉ ሀገር ላይ ያላቸዉ ጭካኔና ንቀት ከምዕራቦቹ አይተናነስም:: ይህ አጠቃላይ በበላይነትና በአሸናፊነት መርህ የሚመራ ፖለቲካቸዉ ሁል ጊዜ ብልጦቹን እና ጥበበኞቹን ምዕራባዉያን እንዳበሳጫቸዉና እንዳነጫነጫቸዉ ነዉ:: በምዕራቦችና በምስራቅ ሀገራት መሃከል ያለዉ የዉጭ ጉዳይ ፖሊሲ በመርህ ላይ የቆመ ቢመስልም ፍጹም በሆነ ቀድሞ ስትራቴጅክ ቁልፉዋን ያነሳ በሚል የብልጠት የጥበብ እና የጭካኔ መርህ ላይ የቆመ ነዉ:: ለዚህም የሰሞኑ የሩሲያ ፖለቲከኞችና የአሜሪካዉያን ፖለቲከኞች የብልጠት ጨዋታ ዩክሬን በማፈራረስ ላይ ያሳዩት ሚና ጥሩ ምሳሌ ነዉ:: አንዱ በዚህኛዉ ጫፍ ላይ ቆሞ የሚጎትታት ስትራቴጅክ ገመድ ከአንድኛዉ ወገን የምታስከትለዉ ምላሽ ዩክሬናዉያንን እንደ ሀገር እንዳይቆሙ ፍርስርሳቸዉን ወደሚያወጣ ጎዳና ይዞአቸዉ እየገባ ነዉ::

በአጠቃላይ ሀያላኖቹ የምስራቅ ፖለቲከኞች ሀያለኞቹን የምዕራብ ፖለቲከኞችን ሁል ጊዜ እንደተገዳደሩዋቸዉ እንዳንዴም እንደበለጡዋቸዉ ነዉ:: አሁን ሰሞኑን ኮምጫጫዉ ፑቲን እንዴታ ታላቁን የሩሲያን ህዝብ እንዳኮሩትና ምዕራቦቹን ግን ኩም እንዳደረጉዋቸዉ ማስተዋል በቂ ነዉ:: ከዚህ የሰሞኑ የፖለቲካ ሁኔታ ልማር ያለ ሀገር አንድ ሽህ አንድ ትምህርቶችን መቅሰም ይችላል:: ደግሞም የሰሞኑ የቻይናና የአሜሪካ ፍጥጫ (በጃፓን : በፊሊፒንስና በሌሎችም የቻይና አጎራባች ደሴቶች ላይ) የምዕራቦችና የምስራቆች የዉጭ ፖሊስ በምን መሰርት ላይ እንደቆመ በገሃድ ይታያል:: ማንም ከምንም የሚጠብቀዉ በረከት የለም:: ሁለቱም ወገኖች ግን ይፈላለጋሉ:: ልክ እንደ ጨካኝ እና ክፉ ፍቅረኛሞች እስከመጠፋፋት አንዱ ባንዱ ላይ እያደባ እንኩዋን በዉጭ ፖሊሲያቸዉ ወግ እና ስርዓት ያለዉ ግንኙነት ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት ያደጋሉ:: ወዳጅነትና አንዱን ተስፋ አደረግሁት ብሎ እጅ አጣጥፎ መቀመጥ ግን ከቶም የሁለቱም ወገኖች ፖለቲከኞች የሚያስቡት አይደለም::

ይሄ የሁለቱ ወገኖች ሀያልነት እዉነት ነዉ:: እዉነት ነዉና የሆኑትን ክፉ: ጨካኝ: ሀያላን: ጥበበኞችና ኮምጫጮች ብለን ልንገልጻቸዉ ይገባል:: እንዳንዴም ቅናት እስኪያሲዙን ድረስ ለማንነታቸዉና ለጥቅማቸዉ ብሎም ለሀገራቸዉ ያላቸዉ ቁርጠኝነት ሊያስጮህን ወይም ሊያስለቅሰን ይችላል:: የሰሞኑ የሩሲያ መሪ ድርጊትና ምዕራባዉያንን ያሳፈሩበት አካሄድ ቅናት ያሲዛል:: በሩሲያ ላይ የሚመጣ አደገኛ ሁኔታን ሁሉ በሀይል በጥበብና ዉስብስብ በሆነ መልክ አምክነዉታል:: የናቶ ወደ ምስራቅ አዉሮፓ ግስጋሴ በትካዜ ዉስጥ እንዲገባ አድርገዉታል::

የኢትዮጵያዉያን ምሁራንና ፖለቲከኞች ይሄን ቀላል የፖለቲካ ቀመርና እዉነታ ሁል ጊዜ እየረሱ እንዱን ሲያወድሱ ያ ወገን እነሱን ከመከራ የሚያወጣቸዉ እየመሰላቸዉ ሌላዉ ወገን ጠላት ይመስላቸዋል:: ሲገለበጡ ደግሞ ያንዱን ቦታ በሌላዉ ይተኩታል:: በዉዳሴና በማሞካሸት የዉጭ ጉዳይ ፖሊሲና ግንኙነት የሚሰምር ጉዳይ ይመስል አንዱን ወገን አንዴ አወድሰዉ ሌላ ጊዜ ደግሞ ረግመዉ የዉጭ ግንኙነት ፖሊስን ከሀገሪቱ አጠቃላይ የማንነት ህልዉና ጋር ለረጅም ጊዜ ማስተሳሰር ሲያቅታቸዉ ይስተዋላል::

ምዕራባዉያንም ሆኑ ምስራቃዉያን ለኢትዮጵያ ፖለቲካ መኮስመን የሚጠየቁትበ ሁኔታ የለም::ስለምንስ አንድኛቸዉ ጠላት ወይ ወዳጅ ተደርገዉ ይፈረጃሉ? በሀገራት የፖለቲካ መስተጋብር ሂደት ዉስጥ ጠላትም ሆነ ወዳጅ የለም:: ሌላዉ ቀርቶ አሜሪካኖቹ የጀርመኑዋን ጠቅላይ ሚኒስቴር ግለ ሚስጥር ሳይቀር በርብረዉ መሰለላቸዉ የሚነግረን እዉነት ይሄንኑ ሀቅ ነዉ:: አሜሪካኖቹ ቢቻላቸዉ ምን ያደርጉ ነበር? ጀርመንን የጫማቸዉ ጭቃ ጠራጊ ያደርጉዋቸታል:: ሀያላኖቹ ጀርመኖች ግን ይሄን አይፈቅዱም:: ሆኖም የጀርመን እና የአሜሪካ የዉጭ ፖሊሲ እጅግ የጠበቀና በመከባበር ላይ የተመሰረተ ነዉ::

ደርግ ምዕራቦቹን ረግሞ ስለማይጠግብ ምዕራቦችን መሳደብ ሲጀምር ጠርሙስ ወርዉሮ መሰባበር ያረካዉ ነበር:: ጥላቻዉን ተጨባጭ ለማድረግ መሆኑ ነዉ:: ደግሞም ምስራቃዉያንን ለማወደስ ኢትዮጵያዉያንን ሁሉ በሰልፍ በማስወጣት ዜማ ያስዜም ነበር:: አሁን አገሪቱን የሚገዙት ሀይሎች በአንድ ወቅት ምዕራቦችን ለማወደስ ቃላት ከማጣታቸዉ የተነሳ የሰዓታት ዜማና ዉዳሴ መቆም ይወዱ ነበር:: ምዕራቦችን የነካባቸዉን ሁሉ እርኩስ እንጨት ያደርጉት ነበር:: አሁን ደግሞ በምዕራቦቹ ለምን እንደተናደዱ በወል ባይታወቅም (ፖለቲከኞቻችን ስለሚያስቡት ቀመር በቂ መርጃ ስለማናገኝ) በምዕራብ ሀገራት ላይ በኢቲቪ የሚለቁት የኩነኔ ናዳን ያስገርማል:: በሀገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ ሀገራት ያሉ ተቃዋሚ ፖለቲከኞቻችንም በምዕራባዉያን ግፊት ዲሞክራሲ የሚመጣ እየመሰላቸዉ (ተጨባጭና መሰረት የያዘ የትግል ስልት ከመንደፍና በሱ ላይ ከመስራት ይልቅ) ምዕራቦችን አንዴ ሲያወድሱ አንዴም ሲኮንኑ ይታያሉ:: አንዳንዴም ምዕራቦችን ሲያባብሉ እና ሲለማመጡ ምዕራቦች የሆነ ታምር የሚፈጥሩላቸዉ ይመስል የምዕራብ ኢምባሲዎችን ሙጥኝ ብለዉ ሲማጸኑ ይስተዋላል :: ተቃዋሚ ፓርቲም ሆነ ሀገር ገዥዉ ማዬት ያለበት ወደ ዉስጥ ወደ ኢትዮጵያ ከርሰ ማህጸን ነዉ:: መፈትሄዉም በረከቱም ያለዉ ከዉስጥ ነዉ::ኢትዮጵያ ማህጸን ዉስጥ::

ምዕራቦች ለማንም ሀገር ጥቂት ሽክና(ስኒ) አጉዋት (የወተተ እንጭፍጫፊ) የሚሰጡት ከዚያች ሀገር ቢያንስ ጋን ሙሉ ወተት ማለብ ከቻሉ ብቻ ነዉ:: የምስራቃዉያንም ፍልስፍና ይሄው ነዉ:: ምስራቆች ጻድቅ ናቸዉ ብሎ የሚያስብ ካለ የዋህ ነዉ:: የሚኖር ግን አይመስለኝም:: ሆኖም የሀገራችን የዉጭ ፖሊስ አዉጭዎች (ወይም ስለ ዉጭ ሀገራት መስተጋብር ተፈላሳፊዎች) በየወቅቱ የሚከተሉት ጎዳናና ፍልስፍና ሲመዘን እና ሲበረበር ወደ ዉስጣቸዉ ለራሳቸዉ ህዝብ ከሚሰጡት ክብር በላይ የዉጭ ሀይላትን ለማስደስት የሚያደርጉት ደፋ ቀና አስገራሚ ነዉ::

የሶሻሊስት ዝንባሌ ያላቸዉ ፖለቲከኞችና ምሁራን ከምስራቅ የሆነ ተአምራዊ እርዳታ ጠብ ቢል አሁንም ኢትዮጵያ ወደፊት የምትስፈነጠር ይመስላቸዋል:: እዉነታዉ ግን ምስራቆችም ሆኑ ምዕራቦች ኢትዮጵያንም ሆነ የትኛዉም ሀገር ቢዘቅጥ ወይም ቢፈርስ ጉዳያቸዉ አይደለም::

አንዳንዱ ምሁርና ፖለቲከኛ ደግሞ ምዕራቦቹን በመደገፉ ብቻ የምዕራቦቹ የዲሞክራሲ ስርአት ለእርሱም ሀገር የሚሆን እየመሰለዉ መከራዉን ያያል::ሌላዉ ደግሞ ምዕራቦች ይሄን እና ያንን አላደረጉልን ብሎ በማኩረፍ ስለ እነሱ ፈጽሞ አይነገር ሲል ቡራ ከረዩ ይላል:: በማንም ሀገር ላይ ጣት መቀሰር ወይም እስክስታ መዉረድ አለዚያም ወዳጄ ሲሆን አልረዳኝም ብሎ ማላዘን አይቻለም:: የሀገራት መሰረታዊ የግንኙነት ፖሊሲ ይሄን አይነት ህሳቤን ዉድቅ ያደርገዋል:: መሰረታዊዉ የሀገራት የዉጭ ፖሊሲ ፍልስፍና የሚለዉ አንድ ነገር ብቻ ነዉ:: ለራስህ በረከት እና ድህነት ምንጩ እራስህ ብቻ ነዉ::

ኢትዮጵያ ሀገር ነኝ ካለች እነከሌ እንዲህ አላደረጉልኝ እንዲህ አላደረጉልኝ እያለች መዉቀስ አትችልም:: ኢትዮጵያም እነዚህን ሀገራት ብትወቅስም እነዚህ ሀገራት ጉዳያቸዉ አይደለም:: ወቃሽ ሆና ከቀጠለች እንደ ሀገርም በእግሩዋ ለመቆም መቼም አትችልም:: ሀገር በእግሩ መቆም ያለበት በራሱ ፍልስፍ እና በራሱ ሀይል ብቻ ነዉ:: የዉጭ ፖሊሲ ፍልስፍናዉም መመስረት ያለበት ከሀገራዊ ፍልስፍናዉ ተሰንጥቆ በሚወጣዉ የፍልስፍና መሰረታዊ ጭብጥ ላይ ነዉ:: ይህ ሀገራዊ ፍልስፍና ዋና ማሳለጫዉም ወደ ዉስጥ የማዬት መርህ ላይ የቆመ መሆን አለበት::

ሀገር በራሱ እግር ሲቆም በራሱ ጉዳይ ገብተዉ የማይፈተፍቱ "ወዳጆች" ይኖሩታል:: ወዳጆች የሚለዉ ቃል ትምህርተ ጥቅስ ዉስጥ መሆኑን አንዘንጋ:: የወዳጅነት ግንኙነቱ እንደሚባለዉ "ወዳጅነት" ሳይሆን በሀይል: በሸፍጥ: በጉልበት: የራስን ጥቅም በማስጠበቅ ብሎም ለራስ ማንነት ከፍ ያለ ዋጋ በመስጠት ላይ የተመሰረት ይሆናል:: የአለም ሀገራት የፖለቲካ ቀመር በዬትኛዉም ዘመን ከዚህ ዘሎ አያዉቅም:: የሀገራት የዉጭ ፖሊሲ ቀመሩ በመሰረታዊነት የሚቆመዉና የሚገነባዉ ግን በአንድ ነገር ላይ ነዉ:: ወደ ዉስጥ በሚያስተዉል ጥልቅ ፍልስፍና ነዉ:: ጥያቄዉ ኢትዮጵያ ወደ ዉስጡዋ አስተዉላ ከዉስጡዋ የመነጨ ፖሊስ ቀርጻ ታዉቃለች ወይ የሚለዉ ነዉ?

አንዳንድ ምሁራንና ዜጎቻችን በምዕራብ ሀገራት መኖር ስለቻሉ ምዕራቦች ለኛ ያዘኑ ይመስላቸዋል:: ምዕራባዉያን ግን የምሁራኖቻችንን አዕምሮ እና የዜጎቻችንን ጉልበት ስለሚፈልጉ ብቻ ነዉ አስጠግተዉ የሚያኖሩዋቸዉ:: ይሄ ብዙ ተጋኖ እንደዉለታ የሚቆጠር ጉዳይ አይደለም:: ብልሆቹ ምዕራባዉያን የሌላዉ ሀገራትን ባለ አዕምሮዎች እየሰበሰቡ ነዉ ሀገራቸዉን የሚያበለጽጉት:: አንዳንድ ሰዎች ደግሞ በቀደመዉ ዘመን ሩሲያና ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ስለሆኑ ሩሲያዉያን ለኛ ወዳጅ የሆኑ ይመስላቸዋል:: ይሄም ሞኝነት ነዉ:: እዉነተኛ ወዳጅ ከምስራቅም ሆነ ከምዕራብ የለም:: አይኖርምም:: ለኢትዮጵያ ፈዉስና ድህነት ከምስራቅም ሆነ ከምዕራብ አይፈልቅም::

አንዳንድ የዋሆች ደግሞ ያለዉን ፍጥጥ ያለ እዉነት በተራ ፕሮፖጋንዳ ሊሸፍኑት ይሞክራሉ:: ወይም ደግሞ ስለዚህ አገር አልስማ አላድምጥ በማለት የሽሽት ስትራቴጅ ሊከተሉ ይሞክራሉ:: ለምሳሌ አሜሪካዉያን ሀያላን ናቸዉ:: የሚያስደምመን ነገር ይሰራሉ:: መደመማችንን እየተኛደድንባቸዉም ቢሆን መግለጽ አለብን:: ምክንያቱም ስንገልጻቸዉ የሆነ ነገር እንማራለን እና ነዉ:: እንዲሁም ሩሲያዉያን ደግሞ ሀያላን እና ኩሩ ህዝቦች ናቸዉ:: የሚያስቀናና የሚያስገርመን ነገር ያደርጋሉ:: ይሄንንም መግለጽ መቻል አለብን:: ብንጠላቸዉም ብንወዳቸዉም መግለጽ ግን አለብን:: የምንማረዉ ስንገልጻቸዉ ነዉ::

ከዚህ ዉጭ እከሌን ወደድን ወይም ጠላን ተብሎ ስለ አለም ፖለቲካ ከበሮ

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

# ክርኅራኄ መንፈስ የሚወለደው በጎ አድራጊነት

ገብረመድኅን ወልደአረጋዊ

ሩኅሩህነት በራሱ ተፈጥሮአዊ ስጦታ ነው። ሩኅሩህነት የሰውን ልጅ ስቃይና እንግልት፣ መራብና መጠማት፣ በአጠቃላይ መጎሳቆሉን ብቻ ሳይሆን የእንስሳዎችንና የአዕዋፋትንም፣ ለፍጡራን ህልውና መድኅን የሆኑ ተክሎችን፣ ተክሎቹም ሊበቅሉና ሊያፈሩ የሚያስችላቸውን የአፈርና የውሃ፣ የአየርንም መጎዳት፣መውደም፣ መጥፋትና መበከል ተመልክቶ ማዘንን፣ስለዚህም ነገር ሁሉ መጨነቅና መጠበብን የሚገልጽ፣ የሚወክል የስሜት ነጸብራቅ ነው። “ ጻድቅ ሰው ለእንስሳውም ይራራል ” እንዲል ሥነ-መለኮታዊው አስተምህሮ፤ ጻድቅ የሚሆነውም ሰው ባሕሪ የሚገለጸው በተፈጥሮ በሚታደለው የርኅራኄው መንፈስ ነው።

እንዲህ ዓይነቱ መንፈስ የረበበት ሰው ወይም የዚህ መሰሉ ባሕርይ ባለቤት ሆኖ የተፈጠረ ሰው፤ ምንግዜም መለያ ባሕርዩ በተግባርና በተግባር ብቻ ፍጡራን ሲንገላቱና ሲጎሳቆሉ የሚመለከትበትን ሁኔታ ቢቻል ለማስቀረት፣ የማይቻል ሆኖ ቢገኝ እንኳን አድማሳቸው እንዳይሰፋ ለማድረግ፣ ለመቀነስና በዚህም መሰሉ ተግባር ለመሳተፍ ፍላጎቱ ያላቸው ወገኖች እንዲተባበሩት አቅሙ በፈቀደው መጠን፤ በተግባርም በቃልም ለማስተማር በመሞከር ነው። ለዚህን መሰሉ ተፈጥሮአዊ ስጦታ ወይም ወደ ተግባር ተሸጋግሮ በተጨባጩ ዓለም ወደር የሌለው ሞገስን ላገኘው ተግባር መሰረት መሆን የቻለውና ታሪኩም “ ስም ከመቃብር ባላይ ይውላል ” እንዲሉ፤ ስሙ በወርቅ ቀለም የተጻፈው ዠን ሔነሪ ዱና ነው።

የዚህ ሰው አብነቱ ብዙ ነው። በጎነቱ ከእሱ አልፎ ለመላው ዓለም የተትረፈረፈ ነው። ሔነሪ ዱና ክርኅራኄ መንፈስ ጋር የተፈጠረ ብቻ ሳይሆን አንዳንዶች እንደሚሉት ርኅራኄውን ከወላጅ እናቱ አንቷን ኮላዶን በደም የወረሰ ነው። ከአባቱም ዠን ዠክ ዱና የበጎ አድራጊነትን ቅዱስ ሙያ ክህነት ተቀብሎ በእጥፍና ድርብ አለምልሞ አበልጽጎታል። ፍሬውም ይኸውና ዓለማችን ቀን በቀንና በየሰዓቱም ለምትፈጥራቸው መከረኞች የቀጣይ ሕይወታቸው ዋስትና መሆን ችሏል። የዚህን ከ186 ዓመታት በፊት በስዊትዘርላንድ ከተማ ጄኔቫ የተወለደውን በርኅራኄ የተመላ የበጎ አድራጎት ተግባር ፋና ወጊ ሰው ማንነት ከፈረንጅ አፍ ወደ አማርኛ በመመለስ በይበልጥ እንድናውቀው ላደረጉን ለአቶ ጌታቸው በቀለና ታሪኩንም ለህትመት ላበቃው ለኢትዮጵያ ቀይ መስቀል ማኅበር ምስጋና ይግባቸውና፤ ሔነሪ ዱና ከእሱም በፊት ለነበሩትም ይሁን ከእሱም በስተኋላ ለተፈጠሩት በርኅራኄ መንፈስ ለሚመሩ በጎ አድራጊዎች በሙሉ ዓይነተኛ ምሳሌ ነው።

ሔነሪ ዱና ክርኅራኄ ጋር ቢፈጠርም የበጎ አድራጊነትን እውቀት ያዳበረው ከቤተሰቡና ቤተሰቡም ከፈለቀበት ማኅበረሰብ ነው። መልካም ዛፍ መልካም ፍሬን ያፈራል እንደሚባል፤ ሩኅሩሁን ሔነሪ ቤተሰቡና ያደገበት ማኅበረሰብ በጎነትን ለም ሆኖ በተፈጠረው አዕምሮውና በርኅራኄ በተመላው ልቡ ውስጥ ዘራበት። የሔነሪም አዕምሮና ልብም የበጎ አድራጊነትን የተቀደሰ መንፈስ ዘር ከጄነቫ ምድር አውጥተው በዓለም ላይ ናኙት። ምድር አውሮጳ፣ አሜሪካ፣ መካከለኛውና ሩቅ ምሥራቅ፣ ኤዢያና አፍሪካ ተቀባብለው በጎ አድራጊነትን በቀይ መስቀልና በቀይ ጨረቃ መሰረተ ጽኑ አደረጉት። ግን ይህም ሁሉ ሳይሆን በፊት የአራት ዓመቱ ጭቅላ ሔነሪ ከሩህሩኂ እናቱ ስር ተቀምጦ የበጎችንና የተኩላዎችን የ “ ወዳጅነት ” ጉዳይ ከዕውቁ ፈረንሳዊ ደራሲ ዠን ዶ ላፎንቴን የብዕር ወጤት እየጠቀሰች ስታብለት፤ “ ተኩላዎቹ እኮ በጎቹን በልተው ሊጨርሷቸው ነው… ” እያለ ትረካዋን እንድታቆም መወትወቱና በለቅሶም ጭምር መማጸኑ፤ በስተኋላ “ሔነሪ ከተጠቂዎችና ከሰላባዎች አጠገብ የሚሰለፍ ሁነኛ ሰው ሊሆን ይችላል ” የሚለውን መላምት ያዋለደ አልነበርም። “ እንደው የተለመደ የልጅ ፍርሃትና ለቅሶ ቢሆን ነው እንጂ ” ከማለት ባለፈ።

ነገር ግን በአራት ዓመት ዕድሜው በሔነሪ ስብዕና ውስጥ ብልጭታው የታየው የርኅራኄ መንፈስ፤ በሰባት ዓመቱ ከወላጅ አባቱ ጋር ወደ ፈረንሳይ ወደብ በሄደበት ወቅት “ በእግረ ሙቅ የታሰሩ ሰዎች ከባባድ ጭነቶችን ከኃያል ስቃይ ጋር ሲያራግፉና ሲጭኑ ” በተመለከተበት አጋጣሚ ጎልቶ ወጣ። እንዲህና እንዲያም እያለ ዝርዝር ሂደቱን ማተት ሳያስፈልግ፤ ከእሱ ጋር የተፈጠረው የርኅራኄ መንፈስ ታላቁን የበጎ አድራጎት ተግባር በጦርነት መሀል ጀምሮ ልዩና አንጸባራቂ የሰብዓዊነት እና ያለማዳላት መርሆ አራማጅ የሆነውን ቀይ መስቀልን አዋለደ። ቀይ መስቀል እያበበ፣ እያፈራ፣ እየጎመራ ሲሄድም መንፈሳዊ ቅናትን ከስቶ ቀይ ጨረቃን በአጋርነት ማፍራት ቻለ። እንዲህም ነው እንግዲህ አብሮ የሚፈጠር የርኅራኄ መንፈስ በጎነትን በተግባር አወልዶ ምድራችን፤ የእንግልት፣የአድሎአዊነት፣የመረሳት፣ የመናቅ፣ የመተው፣የአረመኔያዊነት፣የዘግቶ በሌነት፣የሰቆቃና የምርኮኝነት…ብቻ ሆና እንዳትቀር በተካላካይነት፣ በዓለማችን ምሬት አጣፋጭነትና በሚሊዮን ለሚቆጠሩ መከረኞች የተስፋ ፀዳል ለመሆን የበቃው።


ይኸውና በምድራችን ላይ በሔነሪ ዱና እና እሱን በመሰሉ የርኅራኄ መንፈስ የተዋሀዳቸው ቅን የሰው ልጅ አገልጋዮች አማካይነት የበጎ አድራጎት ተግባር መሰረተ ጽኑ ሆነ። ይህ ማለት ከነሔነሪ በፊት በዓለም ላይ የርኅራኄ መንፈስ አልነበርም ማለት አይደለም። በምድር ላይ ከእነ ማዘር ቴሬዛ በፊት ወይም ከእነሱ የቀደመ በጎ አድራጊዎች አልነበሩም ማለትም ሊሆን አይችልም። ግን በዓለማችን እየተባባሰ በመጣው ድህነት፣ አድሎአዊነት፣ ጦርነትና እነዚህም በሚፈለፍሉት የግለኝነትና የስግብግብነት፣ የጭካኔና የክፋት ድርጊት ብዛት መጠን የርኅራኄው መንፈስና ከእሱም የሚወለደው የበጎ አድራጊነት ቅዱስ ተግባር አድማሱን ማስፋት አልሆነለትም። ይህ እንዲሆን ዓለማችን እነ ሔነሪ ዱናን ወደ በጎ አደራጊነት መስክ ወዳሰማራው አስከፊና ሰቅጣጭ ጦርነት ዓለማችን መመለስ አለባት ወይ? የሚለው መቼም ቢሆን መቼ በጥያቄነት መቅረብ የሚገባው አይደለም።

ምድራችን አሁን የምንመለከተውና ባሻገር ሆነን የምንሰማው ጦርነትና ፍጅት አይሎባታል። ሩህሩህ መንፈስ ጠፍቶ፣ የጭካኔ ሃሳብ በርትቶ፣ የእብድ ገላጋዩ ፈልቶ አለምን ያምሳል ። ከጎረቤት ሱዳን ብንጀምር ሕፃናትን፣ ሴቶችን፣ አዛውንቶችን፣የአካል ጉዳተኞችን ሳይቀር ይህ ነው ተብሎ ለማይገለጽ ሰቆቃ አሳልፎ የሰጠው ጦርነት ነው። ጦርነትም መሰረቱ የበጎ አሳቢነት ስሜት መንጠፍ ውጤት ነው። የስሜቱ መንጠፍ ሰበበ ምክንያትም ለጦረኝነት አምልኮ መንፈስ ራሳቸውን ማስገዛት በፈለጉ ሰብዓዊ ፍጡራን አዕምሮ ወስጥ ከቶውንም የርኅራኄ ባሕርይ ነጸብራቅ ሊኖር አለመቻሉ ነው።

አንዳንድ የዋህ ሰዎች ሰላም ጠፍቷል ሲባል፤ በሶሪያ፣ በኢራቅ፣ በፓኪስታን፣ በአፍጋኒስታን፣ በሊቢያ፣ በደቡብ ሱዳን፣ በሶማሊያ፣ አሁን በቅርቡም በዩክሬን እንደሚሆነውና እንደሚሰማው ዓይነት ወይም የአንደኛውና የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ሆኖ ብቻ ይሰማቸዋል። “ሰላም ነው” ሲባልም የተኩስ አለመኖር ብቻ ነው ብለው ያምናሉ፤ይገምታሉም። ነገር ግን ዓለማችንን የሚንጣትና የሚያናውጣት ዋንኛው ጦርነት እዚያም ወዲያም የሚታየው በጦር መሣሪያ የታገዘ ፍጭትና ግጭት ብቻ አይደለም። ይልቁንም ትክክለኛውና መሰረታዊው ጦርነት በተኩሱ አለመኖር ውስጥ የሚብላላውና “ አንጻራዊ ሰላም ” እና “ ሰላም ነው ” በሚባለው ቃል ውስጥ የታጀለው መሰሪነትና መሸነጋገልናሽፅ የበዛው ንጥቂያና ቅሚያ ፣ አድሎአዊነትና ኢ-ፍትሀዊነት፣ የቅንነት መንፈስ መጓደል ወዘተ ነው። ክርኅራኄና ከአዛኝነት ይልቅ የክፋትና የግድ የለሽነት አመልና ልማድ መንሰራፋት ነው። እነዚህ ሲጓደሉና ሲንሰራፉ በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ጦርነት መኖሩን፣ በሂደትም ድብልቅልቅ ያለው ተኩስ ሊቀጥል መቻሉን ማንም ሊክድ አይችልም። እርግጠኛ መሆን የማይቻለውም ተኩሱ በማን? እንዴት? የት? መቼ? ይከፈታል የሚሉትን ጥያቄዎች መመለሱ ላይ ብቻ ነው።

የዓለማችን እውነት ይሄ ሲሆን፤ የሚፈለገው ነገር ደግሞ ጦርነትንና የእሱም ጓዝ እንደሆነ የሚታወቀውን ከወሰን ያለፈ የግለኝነትና የስግብግበነትን መጥፎ መንፈስ ማስወገድ ነው። ይህንንም ለማስወገድ ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ የሚለውን የፈጣሪን ትዕዛዝ መጠበቁ ዋና ነው ። ከህገ አራዊት ስርአት እና አስተሳሰብ፣ ከተኩላዊ አመለካከት፣ ከጭልፊታዊ ብልጣ ብልጥነት ስብዕናውን ነጻ ለማድረግ መጣጣር የሁሉም ሰብአው ፍጡር ሞራላዊ ግዴታ ነው ። እንዲህ ካልሆነና ሰው በማኅበረሰቡ መሀል ሲኖር ኗሪነቱ ለራሱ ጥቅም ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ህልውና ጭምር መሆኑን ካልተገነዘበ፤ በሩህሩህነቱ የሚጋራውን የፈጣሪውን ባህሪ ያጣል። ክርኅራኄ፣ ከቅንነት፣ ከአርቆ አስተዋይነት፣ ለሌሎች ጥሩውን ነገር ከመመኘት እና በተግባርም ከማድረግ በራቅን ቁጥር እርካታ እያጣን እንደምንሄድ ግልፅ ነው። ይህ እሳቤ እንደተጠበቀ ሆኖ የዓለማችንን የጉስቁልና መልክ የሚለውጠው፤ ክርኅራኄ መንፈስ በሚወለደው፣ በቅንነት ስሜት በሚያበረታታው፣ ከአርቆ አሳቢነት ፅዱ ምንጭ በሚጨለፈው፣ ጥሩውን ነገር በተግባር ከመመኘት ኃይል ጥንካሬውን ከሚያገኘው፤ በጎ አድራጊነት ነው።

በጎ ማድረግ በጎ ከማሰብ ይጀምራል !



ቃልኪዳን ኃይሉ
kalkidan hailu

## ታጋቹ

ዶክተር መልካ እጅግ በጣም እንደ ደነገጠ ያስታውቃል፤ ያ ምቾትና ድሎት የሞላበት ፊቱ ወዘና ርቆት ቀን ቀን የሚለብሰውን ጋወን መስሏል። ያለበት ክፍል መልካም ያልሆነ ጠረን አለው፤ ለነገሩ ሌሊቱን ሙሉ እዚሁ ታግቶ ስላደረ ከሚተነፍገው ጠረን ጋር ተላምዷል። አንድ ትንሽዬ መስኮት እና ባለሁለት ተካፋች የብረት በር ያለው ሰፊ ክፍል ውስጥ ነው። ክፍሉ ከጣራው በታች በአቡጀዴ የተሰራ ኮርኒስ ባይኖረውም ለኮርኒስ መስሪያ ነው መሰል አጣናዎች በየቦታው ከቆርቆሮው ጣሪያ በታች ከቤቱ ዋና ማገር ላይ አንድ ላይ ተመተዋል።

በአንድ ጥግ በኩል ተጠርጎ በማያውቀው ወለል ላይ ብዙ ዘይት ይሁን ጋዝ ያበላሻቸው በርሜሎች ብቻቸውን እንዲሁም አንዳቸው በአንዳቸው ላይ ተደራርበው ተቀምጠዋል። የክፍሉ ግርግዳ ቢጫ ቀለም እንደተቀባ ባይካድም ቀለሙ ለቆ እንዲሁም በጣም ቆሽሿል።

የውስጥ ደዌ ሐኪሙ መልካ ከወደ ጥግ አካባቢ ባለች የጥጥ ፍርሽ ላይ የላብ እና የአቧራ ድብልቅ ጠረን ያለውን አዳፋ ብርድ ልብስ ተከናንቦ ኩርምት ብሎ ተቀምጧል። ችግር የሆነበት ለምን እዚህ እንደመጣ መልስ የሚሰጠው ሰው ማጣቱ ነው። አሁን ቅርብ ጊዜ ነው ከእንቅልፉ የነቃው። ሌሊቱን ሙሉ እንቅልፍ ባይኑ ሳይዞር ነበር ያደረው። ግን ለወጉ ያህል ወፍ ጭጭ ሲል እንቅልፍ አይሉት ሰመመን ሽለብ አድርጎት ነበር። ቢሆንም እንቅልፉን በወኑ ሳያጣጥም ነበር ብትት ያለው።

ነገሮችን በቅጡ ለማስተዋል እየሞከረ ነው። ለምን እዚህ መጣ? እነማናቸው እዚህ ያመጡት? ከማን ጋር ተጣልቶ ነበር? ግራ ገባው። ማንን ይጠርጥር? በቅርቡ ማንን አስቀይሞ ነበር? ሁሉንም ታካሚዎቹን በደንብ ነው ያስተናገደው። ታዲያ ማን ለምን እዚህ አመጣው?

ሶስት ሰአት ከአርባ አካባቢ ከማርቆስ ግሮሰሪ ሁለት ደብል ጅንና ሦስት ተኪላ በአንዳንድ ትንፋሹ ጠጥቶ ሲወጣ ነው የያዙት።ከጓደኞቹ ጋር ሰላማዊ የሆነ ጨዋታ ሲያደርግ ነበር።በእርግጥ ስለ መንግስት ፍትሕ አልባነት፤በሀገሪቱ መልካም አስተዳደር እንደሌለ፤ይህች ሀገር በኢህአዴግ መተዳደር እንደሌለባት ሲደሰኩር ነበር። ሰዎች እንዲያምኑት እና እንዲያደምጡትም ያደጉ ሀገራት የሚባሉትን ልምድ እና ተሞክሮ አጣቅሶ ወዳጆቹን ሊያስረዳ ሞክሯል።

በብሄር የተከፋፈል ሀገር መጨረሻው መፈራረስ እንጂ በአንድነት ተዋዶና ተፋቅሮ መቅረት እንዳልሆነ ሩስያን እያነሳ አብረውት ለሚጠጡት ጓደኞቹ አስረዳቸው፤ መንግስት ላወጣው ሕግ ሳይገዛ፤ ላረቀቀው ፖሊሲ ሳይታዘዝ እንዴት ሕዝቡን ሊያስገድድ ይችላል ብሏል። ትውልድን መቅረፅ ቀርቶ ማደንዘዝ ማፍዘዝ ተይዟል፤ የትምህርት ፖሊሰው ለድሃው ኢትዮጵያዊ ማዶልዶሚያ እንጂ ለባለስልጣናቱ ማቲዎች እንደማይመጥናቸው በፌዝ ተሳልቋል፤ የመንግስት ሰራተኛ የሚከፈለው ደሞዝ ከኮሮው ጋር እንደማይመጣጠን፤ እኩል የትምህርት ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች የተለያየ ደሞዝ የማግኘታቸው ጉዳይ እስቆጥቶታል፤ እንደውም የአንድ የጤና ባለሙያ እና አንድ የሂሳብ ባለሙያ እኩል ተቀጥረው ባመቱ መጨረሻ ግን አካውታንቱ የጤና ባለሙያውን ከሁለት ሺህ በበለጠ የወር ደሞዝተኛ ይሆናል ብሏል፤ የሚኒስትሩ የቀን አበል ለሌላው ደሞዝ መሆን እንደሌለበት በድፍረት ተናግሯል፤ ስለዚህም በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ሊወርድ ይገባል ብሏል።

ከተቻለ በምርጫ ካልተቻለ ግን አመፅ አይንን የማያሳሽ አማራጭ እንደሆነ በድፍረት ለጓደኞቹ አጫውቷቸዋል። የስራ ማቆም አድማ፤ ከመንግስት ተቋማት ምንም አይነት ግብይት አለማድረግ፤ ሕዝቡ የብሔርና የጎጥ ጥያቄ ወደ ጎን ገፋ አድርጎ የአንድነትና የነፃነት ጥያቄ ማስቀደም እንደሚገባ ገልጿል፤ምሁራኑም ወጣቶቹን አስተባብረው ኢትዮጵያን የነፃነት ጎህ ሊያቀዳጁ ይገባል ብሏል።እራሱ ዶክተር መልካ።የማታው ነገር እየታወሰው ነው።ምነው አፌን በቆረጠው አለ።ግን አለወትሮው ትናንት ምን አስቀባጠረው?

ትናንት ዶክትር መልካ ከልክ በላይ ተበሳጭቶ ነበር። ከሚሰራበት ፓውሎስ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ውስጥ ከውስጥ ደዌ ህክምና የትምህርት ክፍል ኃላፊነት እንዲነሳ ተደረገ። የተነሳበት ምክንያት ነው ይብሱኑ ደሙን ያፈላው። አንድ ለአምስት በቅጡ አታወያይም፤ በስርህ ያሉትን ሰዎች በአጠቃላይ እንደ ኮካ ጠርሙስ አንድ አይነት አድርገህ አላበቃሀቸውም፤ እርስ በእርስ አትገማገሙም፤ በስርህ አንድም አባል አልመለመልክም በሚሉ ስንኩልና ከሙያው ጋር በማይገናኙ ምክንያቶች ከቦታው አነሱት።

ዶክተር መልካ ደብዳቤው ከደረሰው በኋላ እንዲህ እያለ ለራሱ ይደሰኩር ጀመር። “ለሕዝብ የሚጠቅመው አንደ ለአምስት፣ ተጓዳኝ.. ምናምን ሳይሆን የሆስፒታሉን ስራና ሰራተኞች ማዘመን ነው። በዘመድ ባዝማድ የሚያክሙና የሚያሳክሙትን የሆስፒታሉን ሰራተኞች ማረቅ ነው። ከጥበቃ ጀምሮ እስከ ሀኪሙ ድረስ መመናጨቅ እና መንገላታታ የሚደርስበትን ሕዝብ ምንድነው ችግሩ ብሎ ማድመጥ ይቀል ነበር። ሐኪሙ ሳይሆን አልጋ ገፊው እራሱ የፈጣሪ ያህል በበሽተኛው ላይ ስልጣን ባለበት ጊቢ ውስጥ አንድ ለአምስት ብሎ ቅንጠት አይገባኝም። ፓውሎስ ለመታከም የፈለገ ሰው ከጤና ጣቢያ መሸኛ ደብዳቤ ብቻ አያስፈልገውም፤ ቢቻል እዚያው የሚሰራ ሐኪም መሆን ካልሆነ ፓውሎስ የሚሰራ ፅዳት ሰራተኛ ዘመድ ማግኘት በሚያጓጓበት መስሪያ ቤት አባል ሁኑ አትሁኑ ብሎ መመልመል መቼም ሹፈት ነው። ትልቅ ስላቅ።”

ዶክትር መልካ ንዴቱ ሳይበርድ ቀኑን ሙሉ ዋለ። ቢቀልልኝ ብሎ የአምስተኛ አመት የህክምና ተማሪዎቹን ለማስተማር ሄደ። በእለቱም ቤድ ሳይድ ስለነበር፤ ቤድ ሳይድ ላይ አንዱን ተማሪ የንዴቱ መወጫ አደረገው። የመቶ ሁለት ቁጥር አልጋ የስኳር በሽተኛ ላይ ነበር ለማስተማር አቅዶ የነበረው። እጬው ሐኪም ተዘጋጀሁ ብሎ ልቡ ውልቅ ብሎ ነበር። ቢሆንም ከመልካ ጋር ሊገናኑ አልቻሉም። ዛሬ መልካ ባይናደድ ኖሮ እንደ አቅሙ እና መመለስ የነበረበትን ይጠይቀው ነበር። ግን ተናዷል ስለዚህ ጭልጥ አድርጎ የሸመደደውን የህክምና ሳይንስ ትምህርት ሁሉ ይተነትነው ጀመር።

መልካ እንዲህ ተማሪዎቹ ከሚያውቁት በላይ የሚጠይቃቸው፤ አላስፈላጊ ሀቲት የሚያበዛባቸው በአራት ምክንያት ነው። አንደኛው ዋርድ ውስጥ ቆንጆና ወጣት ሴት አስታማማዎች ካሉ፤ ተማሪዎቹ በእውቀት የተገዳደሩት ሲመስለው እነሱን እንደማያውቁ ከእሱ እንደማይበልጡ ለማሳየት፤ተማሪን ከተማሪ የእውቀት ደረጃቸውን ለመለየት እነዚህ ሁሉ ካልሆኑ ግን እንዲህ እንደዛሬው ከተናደደ ነው።እጬ ሐኪሞቹን የሚያደናብራቸው ያልጠበቁትን የአንድ፣የሁለትና የሶስተኛ አመት ትምህርታቸውን ልክ እንደ አናቶሚ፣ፊዚዮሎጂ፣ባዮኬሚስትሪ፣ኢፒዲሞሎጂ… የመሳሰለውን የትምህርት አይነት እየጠየቀ ነው።

እጬ ሐኪሞቹ አጠናን ብለው ልባቸው ውልቅ ሲል ባዶ አድርጎ ወደ ዶርምና ቤተመጻሕፍት ይመልሳቸዋል። የዛኔ ልቡ ቅቤ ይጠጣል። ዛሬ ግን ያቅሙን ያህል ከአናቶሚ እስከ በሽታው ፓቶ ፊዚዮሎጂ፤ ከበሽታው ታሪካዊ አመጣጥ እስከ ኢፒዲሞሎጂ ብትንትኑ አውጥቶ ለተማሪዎቹ ቢጠይቃቸው፣ ቢያስረዳቸውም ሆነ ነግሮ ቢያስደነግጣቸው ጠብታ ደስታ ከልቡ ጠፋ፤ ድቃቂ እርካታም ከአእምሮው ጓዳ ብቅ አልል አለ።

ዶክተር መልካ የስልጣን ጥማት የለበትም። ግን ትምህርት በጣም ነው የሚጠማው። የዲፓርትምንት ኃላፊ ሁን ሲሉትም ሳያቅማማ እሺ ያለው የትምህርት እድል በአፋጣኝ አገኛለሁ ብሎ ነበር። የልብ ቀዶጥገና ሰብ ስፔሻሊስት የመሆን ህልሙን ለማሳካት ሲል ስልጣኑን ተቀበለ። ተጓዳኝ፣ አንድ ለአምስት፣ ግምገማ… ምናምን ሲሉት እሺ.

ሳምንት ይቀጥላል

## ሰላማዊ ህዝባዊ ...

ከገጽ 6 የዞረ

ይሾማል።ይህ ሲደረግ የተሿሚዎቹ ፖለቲካዊ አቋም ግምት ውስጥ አይገባም።የዚህ አይነት መንግስታት ዋናው አላማ ሃገርን ከገባችበት ማጥ ማውጣት ስለሆነ የሚፈለገው ሙያዊ ብቃታቸው እንጅ ፖለቲካዊ አቋማቸው አይደለም፤ስልጣን ላይ የሚቆዩትም ለጥቂት አመታት ነው።

ይህን ዘዴ ጣሊያን ከሶስት አመት በፊት ተጠቅማበት ነበር።በወቅቱ ጣሊያን በከፍተኛ የኢኮኖሚ ዝቅጠት ላይ የነበረችበት ወቅት ነበር።ይህን ተከትሎ የሃገሪቱ መራሄ መንግስት የነበሩት ቤርሉስኮኒ የጣሊያን ፓርላማ በመንግስታቸው ላይ ያለውን እምነት የሚለካበት (Vote of confidence) አሰርተው ያገኙት ውጤት ዝቅተኛ ሆነ። ይህም ለሃገሪቱ ፕሬዚዳንት ቀርቦ ውይይት ከተደረገበት በኋላ ለሁለት አመት የሚቆይ የቴክኖክራቶች መንግስት ተቋቋመ። አዲሱን ካቢኔ እንዲመሩ የተደረጉት በወቅቱ በአውሮፓ ህብረት ሴንትራል ባንክ ውስጥ ይሰሩ የነበሩት ማሪያ ሞንቴ ሲሆኑ ሰውየው በሙያዊ ብቃታቸው እና በፖለቲካዊ ስብዕናቸው መልካምነት የተመሰከረላቸው እንደሆኑ በሰፊው ተዘግቦ ነበር። እንደተጠበቀውም ማሪያ ሞንቴ እውቅ ባለሙያዎችን በየሚኒስተር መስሪያቤቱ መድበው ካቢኔያቸውን አዋቅረው ሃገሪቱም ከችግሯ አገግማ ወደ ተሻለ መንገድ እንድትጓዝ ሁለት አመት በርትተው ከሰሩ በኋላ ሃገራዊ ምርጫ ተደርጎ ለተመረጠው መንግስት ሃገሪቱን አስረክበዋል።

ኢትዮጵያም ከኢህአዴግ ጋር ስላልተስማሙ ብቻ ለሃገራቸው በሙያቸው ማገልገል እየፈለጉ ያልቻሉ፣ይህም እንደሚቆጫቸው የሚናገሩ በርካታ ምሁራን አሏትና ይህን መከወኑ አይገዳቸውም። ዋናው ጥያቄ ኢህአዴግ 'ይህ ይሆን ዘንድ ይፈቅዳል ወይ?' የሚለው ነው። መልሱ አዎንታዊ እንደ ማይሆን መገመት አያዳግትም።የኢህአዴግ መርህ ሁሉን ማግኘት ወይም ሁሉን ማጣት እንደሆነ አቶ በረከት ስምኦን "የሁለት ምርጫዎች ወግ" ባሉት በፅሃፋቸው በርካታ ገጾች ላይ ተደጋግሞ የተገለፀ ነው። በእኔ እይታ የመፍትሄ መንገድ የመሰሉኝ ከላይ የተጠቀሱት ሁለት መንገዶች ደግሞ ሁሉን ማግኘትን የሚያስችሉ ባለመሆናቸው ላይመርጣቸው ይችላል።ነገር ግን ሁሉን ማግኘትን የሚያልመው ኢህአዴግ ይህን መሰል አማራጮችን መጠቀም ባልፈለገ ቁጥር ሁሉን ማጣት ሊመጣ እንደሚችል አብሮ ማጤን አለበት።የሰላም አማራጮችን አሻፈረኝ ብሎ ወደ አምባገነንነቱ በሸመጠጠ ቁጥር ሊታገሉት ነፍጥ ላነሱ ቡድኖች ለረዥም ጊዜ ያጡትን ስኬት ያገኙ ዘንድ አስተዋፅኦ እያደረገ እንደሆነ ሰከን ብሎ የማሰቢያው ጊዜ አሁን ነው።

## ለኢትዮጵያ ከምስራቅም ...

ከገጽ 10 የዞረ

መምታት ስህተት ብቻ ሳይሆን ሁለት እጥፍ ስህተት ይሆንብናል። ማንም ሀገር ወደንሃል ብለን ከበሮ ብንመታለት ቅንጣትም ወዳጅ ሊሆነን እንደማይችል ማወቅ ተገቢ ነዉ። ወይም ጠላንህ እያልን ብናቅራራ ከቶም ልቡ ድጭ አይልም።

ኢትዮጵያዉያን ቢያዉቁበት መጀመሪያ ለራሳቸዉ እራሳቸዉ ብቻ ናቸዉ ወዳጅ መሆን የሚችሉት። እራሱን የሚወድ ህዝብ ከዉጭ ፖሊሲዉ ይልቅ ሊያስጨንቀዉ የሚገባዉ የዉስጥ ፖሊሲዉ ነዉ። የዉስጥ ፖሊሲዉ ሁሉን አቀፍ : አካታች: ቀጣይነት ያለዉ መሰረትን የሚጥል: ለነገ ትዉልድ መሰረት የሚጥል እንጅ ትዉልድን የማያባላ: የሃገራዊ አንድነትና እሴትን አጠንክሮ የሚቀርጽ ብሎም ለብልጽግና መሰረታዊ ዋልታ የሚሆን ፖሊሲ መሆኑን ማረጋገጥ ብቸኛዉ መፍትሄ ነዉ። ከሁሉም በላይ ዛሬ ስልጣን የያዘ ሀይል በሌላ ባለ ጊዜ ሲተካ የማይፈርስ መሰረትን መገንባት የሚችል ፖሊሲን አምጠዉ መዉለድ ያለባቸዉ ኢትዮጵያዉያን ፃና ያልሰሩት የቤት ስራ ሲታሰብ ያሳዝናል። ከምዕራባዉያን ብልጥና ብልህ ፖለቲከኞች ሊማሩት የሚገባ የመቻቻል እና አገርን የጋር የማድረግ ፖሊሲ ገና በርቀት እንኳዋን ጭል ጭል ሲል አይታይም። መጀመሪያ አገር የጋራ የምትሆንበትን መሰረታዊ ፖሊሲ መሬት ላይ ማሳረፍ ዋናዉ የኢትዮጵያዉያን ፖለቲከኞችና ምሁራን የቤት ስራ ነዉ። ያኔም ኢትዮጵያዊ ሁሉ አገሩን እና እራሱን ይወዳል።

እራሱን የሚወድ ህዝብ ታላላቅና የሚያኮሩት መሪዎችን ማፍለቅ ይችላል። ያኔም እነዚህ መሪዎች በጨካኙ የአለም ፖለቲካ ዉስጥ በጭካኔ ስለሀገራቸዉ እና ስለ ህዝባቸዉ በጥበብ: በብልሃት :በሀይልና በጭካኔ ይሰራሉ። ያኔም ከምስራቅም ሆነ ከምዕራብ ሀገራት ጋር ሀገራዊ ግንኙነት ለማድረግ የሚነደፈዉ የዉጭ ፖሊሲ የሰመረ ይሆናል። ያኔም በኢትዮጵያ ላይ ምላሱን የሚያወጣ የቅርብ ወይም የሩቅ ሀገር አይኖርም። ኢትዮጵያዉያኖች ወደ ዉስጣቸዉ እየተመለከቱ መጀመሪያ በጋራ መሰረት ላይ በከፍተኛ የሀሳብ ፍጭትና ዉይይት የሚመሰረት ሀገራዊ ፖሊሲና ሀገራዊ መርህ ለሁሉም ወገን መቆሚያ መሆን የሚችል መደላድል ማዘጋጀት አለባቸዉ። ያኔም የብልጽግና ምንጭ ለኢትዮጵያ ከዚህ መሰረት ስር ይመነጭ ዘንድ ይችላል። ለኢትዮጵያ መባረክ ከምስራቅ ወይም ከምዕራብ የሚፈልቅ ታምር የለም። ምንጩ የሚፈልቀዉ ከዚሁ ከሀገሪቱ መሰረታዊ የፖሊሲ ዉቅረት ከርሰ ምድር ዉስጥ ነዉ። ያኔ ነዉ በኢትዮጵያ ላይ የሚያሹፉባት "ወዳጅ ሀገራት" ከፊት ለፊት ጥርሳቸዉን ከሁዋላ ደግሞ ምላሳቸዉ ለሀገሪቱ የማያሳዩዋት። ያኔ ነዉ ህዝቡዋም ተደፈርኩና ተዋረድሁ ብሎ ልቡን ከቤንዚል ሀይል እንኩዋን በሚያቃጥል ሀይለኛ የመዋረድ ስሜት ከመቃተል የሚድነዉ።

የዓለም ህግ ይሄዉ ነዉ። መጽሃፉ የዚህ አለም ልጆች ከብርሃን አለም ልጆች ይልቅ ለመንግስታቸዉ ጨካኝ ናቸዉ ያለዉ ይሄን ሁሉ ሲያመሰጥር ነዉ። ስለ ስነ መንግስት ካወራን ስለ ስነመንግስት ባህሪያት በደንብ መረዳት መልካም ነዉ። አሳዛኙ ነገር ግን በዚህ ዘመን የኢትዮጵያ ፖለቲከኞችና ምሁራን አዕምሮአቸዉን ወይ በምስራቃዉያን ወይም በምዕራባዉያን ጥገኝነት ስር ወሽቀዉታል። ዲሞክራሲንም ሆነ ብልጽግናን ለማምጣት ከማንነታቸዉና ከራሳቸዉ ኩሩ ህዝብ ከመጀመር ይልቅ ድርድራቸዉ የሚጀመረዉ ከምስራቅ ወይ ከምዕራብ ነዉ። እዉነታዉ ግን አንድ ነዉ። ከምዕራብ ወይም ከምስራቅ በረከት የለም። ለኢትዮጵያ መድቀቅ ምስራቅንም ሆነ ምዕራብን መኮነን መፍትሄ አይደለም። መኮነንም አይቻልም። የወደቅን እኛዉ ነን። እኛዉ ኢትዮጵያዉያን ብቻ ነን። መነሳት ያለብንም እኛዉ ኢትዮጵያዉያን ነን። የዉጭ ፖሊሲዉም መቃኘት ያለብት ከላይ በተነሱት መሰረታዊ ጭብጦች ላይ ተንተርሶ መሆን አለበት። መጀመሪያ ወደ ዉስጥ መመልከት የስትራቴጅዉ ቁልፍ ነዉ።

## ገብሬ ...

ከገጽ 7 የዞረ

*አለቃ ደስታ ነገዎ*

### ኮሌጅ እና ወጣትነት

የአባቱ የተማጽኖ ደብዳቤ ከእቴጌይቱ ዘንድ ሞገስ ያገኘለት ገብረክርስቶስ በአዲሱ ጄኔራል ዊንጌት የአዳሪዎች ትምህርት ቤት ገብቶ ያቋረጠውን ትምህርት ጀመረ። ለሦስት ዓመት በት/ቤቱ ውስጥ የቆየው ገብረክርስቶስ በቀለም ትምህርቱ ባሳየው ትጋት የሁለት ተከታታይ ዓመታት ተሸላሚ ለመሆን ችሏል። በዊንጌት ቆይታው ከቀለም ትምህርቱ ጎን ለጎን ስለጥንታዊውና ዘመናዊው የአውሮፓ ስነጽሑፍና ሥነጥበብ በሰፊው ለመተዋወቅ የቻለ ሲሆን የጥበብ አጋሩ ከሆነው ባለቅኔ ሰለሞን ዴሬሳ ጋር የተዋወቀውም እዚያው ነበር። በጥበቡ ዓለም መንታ ስለት ያሉት ገብረክርስቶስ ቅድመ-ኮሌጅ ሕይወቱን ያሳለፈበት የዊንጌት ት/ቤት በኋለኛው ዘመኑ ተለይቶ ለታወቀበት የረቂቅ /አብስትራክት/ ስዕል ዘዬው የዋዜማ መስኮት ነበር ማለት ይቻላል። በቀለም ትምህርቱ የመትጋቱን ያህል በስነጥበብ ዘርፍ ያለውን ዕውቀት ለማስፋትና በልጅነት አባቱ የብራና ጽሑፎችን በሃረግ ሲያስጌጡ የተጋባበትን የጥበብ ዛር ለማንቃት በብዙ ታትሯል። ከጓደኞቹ ጋር የስዕል ኤግዚቢሽን እስከማሳየትም ደርሰዋል። አንድ ወቅት እንዲያውም /1942 ዓ.ም. የመጨረሻ ዓመት ተማሪ ሳለ ነው/ የት/ቤቱን ዓመታዊ በዓል መከበር ምክንያት በማድረግ ከተማሪዎች ጋር ባዘጋጁት ኤግዚቢሽን ላይ ሪአሊስቲክ፣ ሰሚ አብስትራክት እና አብስትራክት ስዕሎችን ሲያሳይ ተገኝተው የነበሩት ንጉሰ ነገስት ቀዳማዊ ኃ/ሥላሴ በአድናቆት እንዳነጋገሩትና አብስትራክት ስዕሎቹን እያዩ #...መቼም ነገሩን አጥተኸው ሳይሆን ሆን ብለህ ለማበላሸት ነው; በማለት በፈገግታ እንዳወሩት ብርሃነ መስቀል በጥናቱ ላይ ከትቧል።

1943 ዓ.ም. ባለታሪካችን ለሃገራችን የመጀመሪያ የሆነው ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ከተቀበላቸው ጥቂት ወጣቶች መካከል አንዱ ሆኖ ተቀላቀለ። ግና ኮሌጁ የጥበብ ፍላጎቱን የሚያረካለት ዓይነት አልነበረም፤ ስለዚህም አውጥቶ አውርዶ የወሰነው የሃገሪቱ ኢኮኖሚ መሰረት በሆነው ግብርና ዘርፍ ለመግፋት እርሻ ማጥናትን ነው። ደራሲ ዓለማየሁ ገላጋይ ሲድኒ ሄድ የተባለ ጋዜጠኛ ለአፍሪካን አርት መጽሔት ከገብረክርስቶስ ጋር ያደረገውን ቆይታ ፈርጥ ላይ ሲጽፍ የገብሬን ቃል እንዲህ አኑሮታል፡- #... አባቴ የግራፊክስ ሙያተኛ ስለነበሩ በሥዕል ጉዳይ ከሕፃንነቴ ጀምረው ያበረታቱኝ ነበር። እርሳቸውም በብራና ላይ የተፃፉ የኃይማኖት መፃሕፍትን ያስጌጡና ይሰሩ የነበሩ ሰው ናቸው፤ በመጀመሪያ ወታደር የመሆን ፍላጎት ነበረኝ። በኋላ ፍላጎቴ ወደ ዘመናዊ እርሻ ጥናት ስለተዛወረ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የሳይንስ ክፍል ገብቼ ለሁለት ዓመታት ተማርኩ። ኮሌጁ ውስጥ የገባሁት የተጨበጠ ስራ ያስይዘኛል ብዬ በመገመት ነበር። ሥዕል ለደህና ኑሮ መገንቢያነቱ በአገራችን አልታመነበትም፤ ቤተሰቦቼም የእርሻ ትምህርት እንድማር ይፈልጉ ነበር፤ እንደኛ ላለች ሃገር የእርሻ ትምህርት መከታተል አስፈላጊ በመሆኑ እኔም ታላቅ ምርጫ አድርጌው ነበር። ይሁን እንጂ ቆይቼ ከሥዕል ሥራ ፈጽሜ ርቄ እንደማልቀር መገንዘብ ጀመርኩ። ከዚያም ከትምህርት ቤት ወጥቼ ሠዓሊ ለመሆን በሚቻለኝ መንገድ መማር ጀመርኩ።; ከዚህ በኋላ እስከ 1948 ዓ.ም. ድረስ የነበሩት ተከታታይ ዓመታት ለገብሬ አታካችና መራራ ወቅቶች ነበሩ። ራሱን ፍለጋ ያልገባበት የለም። እንደ ብርሃነ መስቀል የጥናት ጽሑፍ ለእንጀራ ሲል ሥራ መያዝ የነበረበት ገብረክርስቶስ በበርካታ መ/ቤቶች ሰርቷል። በመጀመሪያ በአውራ ጎዳና ባለሥልጣን ተቀጠረ፤ የአፈር ምርምር ባለሙያም ሆኖ በዚህ ድርጅት ጥቂት ጊዜ ሰራ። በስራው የመንፈስ እርካታ ስላላገኘ ጥሎት ወጣ። ጥቂት ጊዜ ቤት ከተቀመጠ በኋላ ሲንክላር የተባለው የነዳጅ ድርጅት ቀጠረው፣ ሐረርጌ። ኦጋዴን ጥቂት ጊዜ ሰራ፤ ዓመቱን ሳይደፍን ሥራውን ጠልቶት ተመለሰ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ በወቅቱ ዘመናዊ በሆነው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ስታትስቲሺያን ሆኖ ተቀጠረ። እዚህም ብዙ ሳይሰራ ተወው። ነፋስ ስልክ በሚገኘው የሰብስቴ ነጋሲ አንደኛ ደ/ት/ቤት ቢሻል ብሎ በመምህርነት ተቀጥሮም ሰርቷል፤ እንግሊዝኛ፣ ጂኦግራፊና ሳይንስንም አስተምሯል፤ ግና አልገፋበትም - በመታከት ተወው። ከዚህ በኋላ ነው ሁሉንም እርግፍ አድርጎ ትቶ ቤቱን ዘግቶ የስዕል ስራዎቹን በመስራት የተጠመደው። በ 1947 ዓ.ም. በሕይወቱ ታላቅ ሰው የሚላቸውን አባቱን በሞት ተነጠቀ። በአባቱ ሞት መሪር ሃዘን ላይ ወደቀ።

### ሰዓሊው ገብረክርስቶስ

ገብረክርስቶስ ከአባቱ ሞት ተጽናኖት መልስ ጥቂት ወራት ቆይቶ 'ፖይንት ፎር ኢዱኬሽን' ይባል በነበረው የአሜሪካ የትምህርትና የባሕል ድርጅት በሕፃናት መፃሕፍት ሕትመት ዝግጅት ክፍል በሰዓሊነት ተቀጠረ። ሙሉ ጊዜውን ፍላጎቱንና ዝንባሌውን አስተባብሮ በስራው እየረካ የግል የሥዕል ሥራዎቹንም ፍሬያማ በሆነ መንገድ እያከናወነ ለሁለት ዓመት ያህል ሰራ። በ 1949 ዓ.ም. ኒው ደልሂ ላይ በተደረገ የዓለም አቀፍ ወጣቶች ሰዓልያን ትርዒት ላይ የመካፈል ዕድል አግኝቶ የተሳካ ስራ አቅርቦ ተመለሰ። ከህንድ መልስ የነበረው ጊዜ ግን ለገብሬ ጥሩ ጊዜ አልነበረም፤ በተደጋጋሚ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታዎችን ከመጋፈጡም በላይ ብስጭትና ራስ ምታት ተደራረቡበት። በተደጋጋሚ ወደ ውጭ ሃገር ሄዶ ለመማር የነበረው ፍላጎት አንዳንድ ሰዎች መንገዱ ላይ በመቆማቸው ምክንያት እንዳልተሳካለት ማወቁም የበለጠ አሳመመው። ከሕመሙ አገግሞ ሲመለስ ግና ቀሪ ሕይወቱን ሙሉ ያልተለየው የለምጽ ምልክት በፊቱና በእጁ ላይ ወጣበት። በመሰል ጉዳቶቹ ተስፋ ያልቆረጠው ገብረክርስቶስ በ 1950 ዓ.ም. ጀርመን ከሚገኘው ከኮሎኝ የሥነጥበብ አካዳሚ የነፃ ትምህርት ዕድል ለማግኘት ሲፃፃፍ ቆይቶ ስለተሳካለት ወደ ምዕራብ ጀርመን ተጓዘ። ከዛስ? ሳምንት እንመለስበት።

## እኔ ነኝ ...

ከገጽ 14 የዞረ

ጥንካሬ እና ብርታት መሰረት እንደሆነ የታመነበት የብረት ማንጠሪያ ወይንም "ፈርነስ" የምንለዉ እሳት የላሰ ምድጃ ገድል አለያም በሸክላ ሥራዉ ላይ የሚታየዉ እደ-ጥበብ ሥራ ሂደት ውስጥ ያለ የአመራረት መላነዉ። ክርክሩ ለአፈሩ ያላቸውን ክብር እና ፍቅር ያሳያል ሊባል ይችላል፤ ማሳበቢያ ተደርጎ ሲወሰድ ነዉ ችግሩ!

አንዳንዴም እንደሰው ሃገር ሰው ባይተዋር ወይም እንግዳ ሀገሬዉ ሰፈራዉን ከከወነ በኋላ መምጣቱን በምክንያትነት የሚያስቀምጡ አሉ። ሌላ ዓይነት በትዕምርተ ጥቅስ "እንግዳ" የሚሉት ከሌለ በቀር መጤ የምንለዉ ሁሉ መሀል ከተማዉን ይዞ ሰርቶ ሲኖርበት የፉጋዉን ሥራ ዉጤት እያሻሻጠ ነግዶ ሲከብርበት፣ይህን ቤተሰብዕ ብቻ ነጥሎ ከከተማ ጥግ የሚያወጣዉ ምን ይሉት ፈሊጥ ነዉ? በአሰፋፈር እንኳ ስንወስድ አንድ ያፈነገጥንበት ፉጋዉን ገበሬ/ገጠሬም ከተሜም አርገን አለመዉሰዳችን ነዉ። የሆነ ነገር እንደታየን ግልፅ ቢሆንም ያ! ነገር ምን እንደሆነ አልተናገርንም፣ በሥሜ ይነገድበታል እንጂ የመንግስት ሥርዓታችንም የእድገት ትልሙ እርሱን በአጀንዳነት ብቻ ሳይሆን በተቋምነት ይዞ እደ-ጥበባዊም ሆነ ሥነ-ዉበታዊ ተዋስኦዉን መነሻ ሲያደርገዉ አልታየም። በዓለም ታሪክ ከተማን ያመጣዉ ማነዉ? ታሪካዊት ባቢሎንን ማን ሰራት? ስንል እነ ለማ አዲያሞ መሆናቸዉ ጭርሱን አይከሰትልንም።

ሌላዉም ምክንያት ከሥልጣኔ ትርክት የተያያዘ ነዉ፤ ሥልጣኔ ወለድ የመበላለጥ ሥጋት። የሥጋቱም ምንጭ ይኸ የማንንም እጅ ሳይጠብቅ፤ ምንም ዓይነት ይኸ ነዉ የተባለ የመሬት ርስት ሳይኖረዉ፤ ግን ምኔም የሚለዉ እጁንና ለሥነ-ዉበት የሚጨነቅና የሚጠበብ አይምሮና ልቡና ያለዉ ሰዉና ቤተሰቡ ነዉ፤ የምኒልክ ምስቅልቅል የልጅነት ታሪኩ ንግርቱም ተጨምሮ የሚያረጋግጥልን ይህንኑ ሥጋት ወለድ ትርክት ነዉ።ከዚህ ሳይሆን ይቀራል "የፈሩት ይደርሳል፤ የጠሉት ይወርሳል" መባሉ?

የዚህኛው ክርክር አንጓ፤ በፉጋ ላይ የተጣለዉ ማህበረሰባዊ እቀባ፤ እንደሚገመተዉ ከንቀት ሳይሆን ከሥጋትምሊሆን እንደሚችል ሊታሰብ ይገባል። ያለፉጋዉ ተዋስኦ ሰርግ፣ ሞት፣ በዓለ ሲመት፣ ዓመት በዓል፣ የትኛዉም ቢሆን ምን ሊመስል እንደሚችል ስናስብ መሪዉ ማን እንደሆነ፣ ኃያሉ፣ አራጊ ፈጣሪዉ ማን እንደሆነ እንገነዘባለን። አንድ እኛ ኢትዮጵያዊያን በታሪካችን አንድ ነገር አሳክተናል ካልን ከአድዋ ድላችን ፊት የሚቆም ትርክት የለንም፤ ፉጋዉ ባይኖር አድዋ አድዋን አይሆንም ነበር። ፉጋነታችን የቅራኔያችን ይዘት እና አያዎ ትክልት ነዉ። እንቆቅልሽ፡ ከሥልጣኔ እና ከሥልጣን?ደግሞም፣ ክርክር አለብን፡- ሥልጣኔ ሥልጣን ነዉ! የሚል። በቅድሚያ ግን ሥልጣን ሥልጣኔ እንዳይደለ እሙን እዉን ይሁን!

ፉጋ እና ቡርዧ

ላለፉት 300-400 ዓመታት በዓለማችን ተንሰራፍቶ ያገኘነዉ የዓለምአቀፍ ካፒታሊስት ሥርዓት ህልዉና መሠረት ሆኖ፤ መሬትና ተፈጥሮ ላይ ከተቆራኘ የሀብት ግንኙነት ራሱን ሙሉ በሙሉ አላቆ፤ አዲስ በገንዘብና ገበያ ላይ የቆመ ሥርዓትን ያመጣዉ ኃይል ማነዉ? ከእንደዚህ ዓይነቱ ቤተሰብ የተገኘዉ ቡርዧው ነዉ- የያኔዉ የፈረንጅ ፉጋ!። ዛሬ ላይ የኢንዱስትሪ ባለቤት፤ ፎርቹን 500፤ሴሌብሪቲ እያልን የምናሞካሻቸው የአለማችን ቱጃሮች፤አባት አያቶቻቸዉ፣ የያኔዎቹ ፉጎች፣ ሸክለኞች (ሴራሚስቶች)፣ ፋቂዎች፤ ወዘተ የነበሩ ናቸዉ። ዛሬም ቢሆን በቂ ሃብት ያላቸዉ የዓለማችን ቱጃሮች በፋብሪካ ለማንም የተመረተን አርቲቡርቲ አንፈልግም ሲሉ የሚሄዱበት አማራጭ ወደእነዚሁ ዘመን አይሽሬ ፉጎች ጋመሄድና በልካቸዉ አዝዘዉ የልባቸዉን መሙላት ነዉ፤ ዋጋቸዉ ታዲያ ትንግርት ነዉ!

የጊዜ እና የቦታ ጉዳይ ሆኖ እንጂ ቡርዧ ፉጋ፤ ፉጋም ቡርዧ ነበር። ፉጋ ከሁሉም በላይ ለነፃነቱ ዋጋ የሚሰጥ የትልቁ ቤተሰብዕ አንጓ ነዉ። ልበሙሉ ያገር ሃብትና ባለሀገር ነዉ። ቡርዧ ማለት ምን እንደሆነ ከየት፣ እንዴት፣ እንደተነሳ መተንተን እንደሚያስፈልግ ይገባኛል። ለሌላጊዜ ላሳድረዉና አንድ ታላቅ ፋይዳዉን በቡርዧው ትርክት ተተግኜ ስለፉጋዉ ልብ ልናገር፡ - ለነፃነቱ ሟች! ለማንም አልገብርም፤ አልሰግድም፤ ነፃነቴን! ነፃነቴን! ባይ የከተማ ልጅ ነዉእንጂ የመብት ቀበኞች "ፃድቃን" ነን ባዮች እንደሚያስቡት(...) አይደለም! ፉጋን ያላከበረ፣ ፉጋ ያልሆነ፣ ለፉጋ ተቀጥሮ ያልሰራ ሰው፣ ቤተሰብዕና ሀገር አስተማማኝ አቅም ብቃትና ልብ ኖሮት የገዛ ዓለሙ እና የሀገሩ ባለቤት የመሆን እድል አይኖረዉም! ያየነዉም ይህንን ነዉ! የዛሬዉን እንዲህ ብዬ ልቋጫ፡- ጨዋ ተብዬ ባሪያ ሆኜ ከምኖር፤ ፉጋ ሆኜ በነፃነት-ሳልኮፈስ ሳልኮሰምንም- መሬቷን እኩል ረግጬ መኖር ምርጫዬ ነዉ። (ይቀጥላል!)

እኔ ለማ አዲያሞ ነኝ!

(መልካምሰው አባተ)

# ቭላድሚር ዘ ግሬት

ያቺ የፑቲን ሰንጢ ክሬሚያ ታሪካዊ ስፍራ ናት። መቼም ክሬሚያ የሌለችበት የምስራቅ አውሮፓ ታሪክ ፈልጎ ማግኘት ያስቸግራል። ክሬሚያ የከባቢው ፖለቲካ ማብላያ መሆን የጀመረችው ገና ከጥንት ከ2,500 ዓመታት በፊት ጀምሮ ነው፤ በግሪካውያን ቅኝ ስር ከነበረችበት ጊዜ አንስቶ። ሞቅ ደመቅ ያለው ፖለቲካዊ ታሪኳን የምናገኘው ደግሞ በ10ኛው ክፍለ ዘመን ገደማ ነው። በዚህ ወቅት የዛሬዎቹን ራሽያና ዩክሬን (በጥንቱ አጠራር ሩስና ኬቭ) ጠቅልሎ ይገዛ የነበረ አንድ አረማዊ (pagan) ንጉስ ነበረ፤ ቭላድሚር ዘ ግሬት ይሰኛል። በ988 ዓ.ም. በዛሬይቱ ክሬሚያ ቭላድሚር የኦርቶዶክስ ክርስትናን ተጠመቀ፤ አጥማቂዋ የቤዛንታይን ቤተክርስቲያን ነበረች። ቭላድሚር ክርስትናን በተቀበለ በማግስቱ መላ ሩስና ኬቭ ያመልኩባቸው የነበሩ ጣዖታትን ሰብስቦ ሙት ባህር ጨመራቸውና ከጣዖት አምላኪዎች ጋር ክፉኛ ተጣላ። ሆኖም ጉልቤ ስለነበር አኩራፊውን ሁላ ዝም አሰኝቶ የተቀበለውን እምነት አፀና።

ቭላድሚር እንዴት የቤዛንታይን ኢምፓዬር አርቶዶክሳዊ ክርስትናን ሊቀበል ቻለ? የሚለውን ጥያቄ ስናነሳ ደግሞ ሁለት መልክ ያለው የሚያዝናና መልስ እናገኛለን። እንግዲህ በወቅቱ የቭላድሚር ግዛት ሩስና ኬቭ በክርስቲያኖች፤ ሙስሊሞችና አይሁዶች የተከበቡ ነበሩ። ቭላድሚር መልዕክተኞቹን ወደ ሶስት አቅጣጫ ልኮ ለሩሶችና ኬቮች የሚስማማው የትኛው ሃይማኖት እንደሆን አጥንተው እንዲመጡ አደረገ። መልዕክተኞቹ የቡልጋሪያ ሙስሊሞችን፤ የቤዛንታይን ክርስቲያኖችን እና የአይሁድ ስደተኞችን ሃይማኖታዊ ባህል ከመረመሩ በኋላ ከቭላድሚር ግርማ ሞገስ ስር አጎንብሰው የጥናት ውጤታቸውን አቀረቡ። የጥናት ውጤታቸው እንዲህ ይጠቀለላል «ንጉስ ሆይ! የቡልጋሪያ እስላሞች ሃይማኖታዊ ባህል መልካም ሆኖ ሳለ የሩሶችና ኬቮች የደስታ ምንጭ የሆነውን መጠጥ አጥብቆ ይከለክላል፤ አይሁዶች ደግሞ እየሩሳሌምን ከደው የሸሹ እንደመሆናቸው መጠን በየተሰደዱበት አገር ሁሉ የተጠሉ መሆናቸውን አረጋግጠናል፤ የቤዛንታይን ክርስትያኖችን ሃይማኖታዊ ስርዓት መርምረን ለማቅረብ ግን ከስርዓቱ ማማር የተነሳ አቅም አንሶናል፤ በውነቱ በስፍራው ከተገኘንበት ቅፅበት ጀምሮ በገነት እንሁን በምድር ማስታወስ አልተቻለንም ነበር።....»

በወቅቱ የቤዛንታይን ንጉስ የነበረው ባዚል 2ኛ ቭላድሚር ዘ ግሬት እምነት እያማረጠ መሆኑን ሰምቶ ኖሮ የሩስ ንጉስ መልዕክተኞች ሲመጡ ድንቅ ሃይማኖታዊ ፕሮግራም እንዲከናወን ቀሳውስቱን አዟቸው ነበር አሉ። በዚህ መልኩም አረማዊው ቭላድሚር በቆስንጠንጢንዮስ ክርስትና ተጠመደ። በክሬሚያም ተጠመቀና ጣዖት አምላኪ የነበሩትን ሁሉ በተለይም ደግሞ ስላቮችን እያስገደደ አጠመቃቸው።


ሌላ የታሪክ መዝገብ ደግሞ የቭላድሚርን መክረስተን በሌላ መልኩ ያብራራዋል። ቭላድሚር ለጉብኝት ቆስጠንጢንዮስ በተገኘበት አጋጣሚ አና በተባለች የንጉስ ባዚል 2ኛ እህት ፍቅር ወደቀ። ካገሩ ተመልሶ ነገሩን ካብላላ በኋላ ‹እህትህን ዳርልኝ!› ብሎ ለባዚል ላከበት። ባዚል ግን እንዲህ የሚል መልስ መለሰለት፡ «አንተ ደፋር አረማዊ፤ የቤዛንታይን ንጉስ እህት ለማግባት መመኘትህ በውነቱ ድፍረት ነው። ከዚህ ቀደም እንዲህ እንዳንተ የደፈረኝን ወደል አላስታውስም፤...... ይሁን እንጅ ጀግና መሆንህን አውቃለሁ፤ እምነቴን ከተቀበልክ ውድ እህቴን አናን እድርልሃለሁ፤ በዚህ ከተስማማህ 6ሺ እግረኛ ላክልኝና ዙፋኔ ላይ ያመፁብኝን እነ ባርዳስን ላጥፋቸው።.....»

ቭላድሚር አይኑን አላሸም። የባዚልን ጥያቄ ተቀበለ። 6ሺ እግረኛ ልኮ ባዚል ላይ ያመፀውን ባርዳስን ደመሰሰለት። በክሬሚያም ተጠመቀ፤ የ27 ዓመቷን ልዕልት አናንም አገባ።

****

እንግዲህ ይሄን ታሪክ በከንቱ አላነሳነውም። የቭላድሚር ዘ ግሬት በክሬሚያ መጠመቅ በዛሬይቱ አለም ፖለቲካ ላይ ተፅዕኖ ማሳረፉ ስላልቀረ ነው። የዛሬዎቹ ራሽያና ዩክሬን ጠላቶች ይመስሉ ይሆናል፤ ምናልባትም በዘመኑ የራሽያ ‹ዛር› ቭላድሚር ፑቲን ጉዳይ አይስማሙም ይባል ይሆናል። ቭላድሚር ዘ ግሬት በሚባለው ሌላኛው ቭላድሚራቸው ግን አንድነት አላቸው። በዩክሬን ዋና ከተማ ኬቭ የሚገኘው ትልቁ ካቴድራል በቭላድሚር ዘ ግሬት ስም የሚጠራ ሲሆን የኬቭ ዩኒቨርሲቲም እንደዚሁ። በራሽያ ደግሞ ቭላድሚር ዘ ግሬት ታላቅ ብቻ ሳይሆን ቅዱስ ጭምር ነው፤ ቅዱስ ቭላድሚር። የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን እና ምስራቅ ኦርቶዶክሳውያን ጁላይ 15ን የቅዱስ ቭላድሚር ቀን ብለው በየዓመቱ ያከብሩታል። የዚህ ሁሉ ምክንያቱ ቭላድሚር አውሮፓን ክርስቲያን በማድረግ ከማንም የላቀ አስተዋፅኦ በማበርከቱ ነው። በዚህ ዘመን ደግሞ ከጥንቱ ቭላድሚር አፅም ላይ የበቀለ ሌላ ቭላድሚር መጣ፤ ቭላድሚር ቭላድሚሮቪች ፑቲን። ፑቲን ክሬሚያ በራሽያ ከመጠቅለሏ ከሰዓታት በፊት እንዲህ ብሎ ሲናገር በጆሮዬ በቀዳዳው ሰምቸዋለሁ፡ «በ10ኛው ክፍለ ዘመን ቭላድሚር ዘ ግሬት በክሬሚያ የተቀበለው ኦርቶዶክሳዊ ክርስትና የፅናት መንፈስ የእኛ ራሺያዎች፤ ዩክሬኖችና ቤላሩሶች ወዘተ አይነተኛ መገለጫ ነው።.....»

ምርጫው ወይም ሪፈረንደሙ ክሬሚያን ወደ ራሺያ በጠቀለለ ማግስት የመጨረሻው የሶቪዬት ህብረት መሪ ሚካኤል ጎርቫቾቭ ለፑቲን አንድ መልዕክት አስተላለፉ፡ «የራሽያ አካል የሆኑት ክሬሚያውያን ብቻ አይደሉም፤ ዩክሬናያውያን ጭምር ናቸው፤ ጎሽ የኔ ልጅ! አይዞህ ግፋ!» ሚካኤል ጎርቫቾቭ እንዲህ የተናገሩት በቅዠት አሊያም እርጅና በተጫነው ስሜት መስሎኝ መቀባጠራቸውን ለማረጋገጥ አንዳንድ መዛግብትን ሳገላብጥ ‹ነገደ ሩስ› ቢያንስ አስራ አራት በሚሆኑ የምስራቅ አውሮፓ አገራት የፖለቲካ ትኩሳት ለመጫር በሚያስችል መጠን መሰራጨቱን አረጋገጥኩ። ጥቂት የሩስያ ዘሮች የሚኖሩባቸው ምስራቅ አውሮፓ እና ስካንዲኒቪያ አገሮች ፊንላንድ፤ አዘርባጃን እና ታጃኪስታን ናቸው (1%)፤ ብዙ ቁጥር ያላቸው ሩስያውያን የሚገኙት ደግሞ በክሬሚያ ነው (58%)።




ሶቭዬት ህብረት ስትፈራርስ በወቅቱ ወጣቶች በነበሩ የዛሬይቱ ራሽያ መሪዎች ላይ የአገር አልባነት ስሜት ፈጥሯል፤ አገር አልባነት የሚወልደው የበታችነት ስሜት ምን ያህል ከባድ መሆኑን ደግሞ አገር የለንም ብላችሁ የምታስቡ ዜጎች ሁሉ ታውቁታላችሁ። ፑቲን ክሬሚያን በመውረራቸው በተቃዋሚዎቻቸው ሳይቀር ከሚደገፉባቸው ምክንያቶች አንዱ ይሄው ስሜት መሆኑን የአካባቢውን ጅኦፖለቲካ የሚተነትኑ ፀኃፊዎች ሁሉ ደጋግመው የሚናገሩት ነው። በማንኛውም ራሽያዊ ልብ ውስጥ ሶቭዬትን ወይም ሶቭዬትን የምትመስል ሃያል አገር የመመለስ ታላቅ ምኞት አለ። እነኚህን ምኞቶች ሁሉ የሚመራው ደግሞ የቭላድሚሮቪች ፑቲን ምኞት ነው።

በነገራችን ላይ በሶቭዬት አስተዳደር ዘመን ክሬሚያ አስቀድማ በራሽያ ክፍለ ሀገር ስር የነበረች ሲሆን ወደ ዩክሬን ግዛት የተጠቀለለችው በ1954 ዓ.ም. በኒኪታ ክሩስቼቭ የፕሬዚንዳንትነት ዘመን ነው። ታይም መፅሄት ‹ክሩስቼቭ ክሬሚያ በዩክሬን ክፍለሃገር ስር እንድትሆን የቀረበውን ሰነድ ሲፈርሙ ጥንብዝ ብለው ሰክረው ነበር!› ብሎ ፅፏል። በርግጥ በዚያን ወቅት ሶቭዬት ተበታትና ክሬሚያ የአካባቢው ፖለቲካ የውጥረት ምንጭ ትሆናለች ብሎ የገመተ ስላልነበረ ክሩስቼቭ ባይሰክሩም እንኳ ሰነዱን ሊፈርሙ እንደሚችሉ የታመነ ነው፤ ለነገሩ አሁን ኢትዮጵያ ከዘጠኝ ብትበታተን አማሮች ማለቴ ጎንደሮች (አማራ የሚባል ጎሳ የለም ስለተባለ ልጎንድረው ብዬ ነው....) ሁመራን ከትግራይ ለመንጠቅ ጦርነት ያውጃሉ ብሎ እንደመጠርጠር ያለ ነገርኮ ነው።

## ሳልሳዊት ሮማ - ሞስኮ

ያልኩትን ልድገመውና የምዕራቡ ዓለም ሚዲያ እንደሚያወራው የሶቭዬት ህብረት መፍረስ በፑቲን እና የዘመን ተጋሪ ራሽያውያን ከባድ የዝቅተኝነት ስሜት ፈጥሯል። በዚህ የተነሳ ፑቲን አሜሪካ በተነሳች ቁጥር ከቁም ነገሩ በፊት አንድ ፌዝ ጣል ማድረግ ግዴታቸው የሆነ ይመስላቸዋል። የራሽያ ህፃናት በአሜሪካ ዜጎች በማዳጎ እንዳይሰጡ የሚከለክለውን አዋጅ በፈረሙበት ወቅት ፑቲን ምን አሉ ተባለ «አንድ የራሽያ ህፃን የአሜሪካ በሬ ጡት ወተት አይስማማውም።....»

እንዳው ነገር ፍለጋ ካልሆነ ከመቼ ወዲህ በሬ ወተት የሚሸከም ጡት አበቀለ? ግብረሰዶማዊ ለማድረግ ልጆቼን ለአሜሪካ አልሰጥም እያሉ ነው ፑቲን። (አሜሪካ የተመሳሳይ ፆታ ጋብቻን የመፍቀድና የማስፈቀድ የ‹ሞራል ዝቅተት› ጉዳይ እነ ሙጋቤንም ቀልደኛ አድርጓል። «ወንድሜ አባማ በዚምባቡዌ ምድር የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻን እንድፈቅድ የሚፈልግ ከሆነ፤ መልካም ምሳሌ ለመሆን መጀመሪያ እኔ እሱን ላግባው!» ብሎ ተናገረ አሉ ሙጋቤ በቅርቡ፤ ሙጋቤ ይህን ነገር የተናገረበትን ምንጭ ብፈልግ አጣሁት። ምንጭ ደረቀ እሚባለው እንዲህ ሲሆን ይሆን እንዴ?!)

ጆርጅ ቡሽ ትንሹ በአንድ ትረካቸው ላይ ከፑቲን ጋር የነበራቸውን ቆይታ ያነሱና ‹በውይይታችን መሃል በጥፊ ላልሰው ምንም አልቀረኝ ነበር!› ሲሉ በወሬ መሃል ፑቲን ያሳያቸው የነበረው ንቀት የሚያበሳጭ እንደነበር ጠቅሰዋል። ይሁን እንጅ የፑቲን አላማ ምዕራባውያን መሪዎችን ከማበሳጨት የሚያልፍ ነው። ፑቲን የቀድሞዋን ሶቭዬት በራሱ ስታይል የመመለስ ጥልቅ ምኞት ካለው እንደ ጆርጅ ቡሽ አይነት ገራገር ሲገኝ የስነልቦና ጦርነት ከፍቶ ልክ ማስገባትም የትግሉ አካል ነው። ፑቲን በፖለቲካ፤ በኤኮኖሚ እና ባህል የጠነከረ አንድነት ያላቸውን ራሽያ፤ ዩክሬን፤ ካዛኪስታን እና ቤላሩስ አንድ በማድረግ ‹ዩሮዥያ› የተሰኘ አዲስ አለም መፍጠር ይፈልጋል። በፑቲን አስተሳሰብ አለምን በ‹ሞራል ከዘቀጠው አሜሪካዊነት› ለመከላከል ዋንኛው አማራጭ ቢያንስ አሜሪካን የሚያክል ተቀናቃኝ ሃይል መፍጠር መቻል ነው። እንደ ጥንታዊት ሮማ ቄሳሮች ወግና ባህል ከሞስኮ የሚነሳ ህግና ስርዓት የአለምን ግማሽ ክፍል እንዲቆጣጠር ማድረግ የፑቲን ራዕይ ነው። አሜሪካን የምትወዱ አንባቢያን አይሳካለትም አትበሉ፤ ለምን ቢባል ‹ዩሮዥያ› የፑቲን ህልም ብቻ አይደለችም፤ በመላው ምስራቅ አውሮፓ የተበተኑ ነገደ ሩስና አፍቃሪ ራሽያ ጭምር እንጅ። የፑቲን ግላዊ ስብዕና የተገነባው በሁለት ነገሮች ነው ይባላል፤ ዋንኛው ከነቅዱስ ቭላድሚር የተወረሰው ጠንካራ መንፈሳዊነቱ ነው፤ ሁለተኛው የራሺያ ታሪካዊ ጠላት የሆነችውን አሜሪካን ከመጥላት ነው። በርግጥ ጥላቻና መንፈሳዊነት አብሮው አይሄዱም፤ ሆኖም ፑቲን ‹ዩሮዥያ›ን ሲያልምም ሆነ ሲቃዥ ኮስታራ የፖለቲካ - ኤኮኖሚ አዲስ አለም ለመፍጠር እንጅ ሰማያዊት እየሩሳሌምን ለመውረስ አይደለም። ከመካከለኛው ዘመን ጀምሮ የነበሩ የራሽያ ዛሮች (ነገስታት) የአለም ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችን የመጠበቅ ክርስቶሳዊና ቭላድሚራዊ ሃላፊነት አለብን ባዮች ናቸው። ራሺያውን አንድ የኦርቶዶክስ ክርስቲያን ከአልቃይዳ ቦምብ ጥቃት በተዓምር ቢያመልጥ የ‹ቭላድሚር መንፈስ ጠብቆት ነው› እስከ ማለት የሚያደርስ ሃይማኖታዊ ትዕቢት የሚተናነቃቸው ናቸው። ካራቲስት ከመሆኑ በፊት ዳዊት በመድገም ያደገው ፑቲን የዚህ አስተሳሰብ ሰለባ ባይሆን ነበር የሚገርመን።

## አባት አገር ወይም ሞት!

ለማንኛውም ፑቲን ከምዕራባውያን የተነጠለ የዩሮዥያ አለም የመፍጠር ህልሙ ይሳካል ወይስ አይሳካም የሚለውን ለትንቢተኞች ትተን እያየን ያለውን ብንገምት ይሻላል። ዩክሬን ከጅኦፖለቲካዊ ጠቀሜታዋ አኳያ አሜሪካና ራሺያ አይን ላፈር እስኪባባሉ ቢራኮቱባት ፍርድ የለም። በወንድማችን ባራክ አባማ ዘመን የአሜሪካ ሃይልነት በራሽያ መደፈሩ ግን ትንሽ ቅር ያሰኛል። ቭላድሚር ፑቲን ምዕራባውያንን ቡጢ ሲገጥም የጅዶ ችሎታውን ተማምኖ አይደለም፤ የተጫወተው በእግሩ ሳይሆን በአዕምሮው ነው። ራሽያ ከአሜሪካ ጋር ዘለቄታዊ ወዳጅነት እንደማይኖራት ማንም ያውቃል፤ በአሜሪካና ራሽያ መካከል ያለው የንግድ ልውውጥ 4% ብቻ ነው። የ2008ቱ የኤኮኖሚ ቀውስ አሜሪካን ከነአጋሮቿ ሲያሽምደምድ ራሽያን ግን ጠቅሟታል። ራሽያ ከነዳጅ አምራች ድርጅቶቿ በታሪኳ ታይቶ የማይታወቅ ትርፍ ያገኘችው ከኤኮኖሚ ቀውሱ ወዲህ ነው፤ ያገኘችውን ትርፍ የጦር ቃል ኪዳኑን ድርጅት (NATO) ጦር ሊቋቋም የሚችል ወታደራዊ ጡንቻ ገንብታበታለች። ዕድሜ ለተባራሪው ፕሬዚዳንት ቪክቶር ያኑኮቪች ዩክሬን የራሽያን ብድር በአጭር ጊዜ ውስጥ በመመለስ የኤኮኖሚ ነፃነትን ለመጎናፀፍ ተዓምር ያስፈልጋታል። እንደ ጣሊያን ያሉት የአውሮፓ ህብረት አባል አገራት ደግሞ በራሽያ ነዳጅ ሱስ ተጠምደዋል። ጀርመን 40% የሚሆነውን የነዳጅ ፍጆታዋን የምትገዛው ከራሽያ ነው። እንግሊዝ ራሺያ ላይ የሚጣለው ማዕቀብ ገደብ ካልተቀመጠለት መልሶ እኔኑ ይኮረኩመኛል ብላለች። እንግዲህ ፑቲን አንድ ወታደር ወደ ዩክሬን ሳይልክ የዩክሬንን ፖለቲካ ያመሰው በኤኮኖሚ መደላድል ላይ ሆኖ አዕምሮውን በሚገባ በማሰራት ነው። በ2008 ዓ.ም. ጆርጂያን በመውረር ትልቁን የዩሮዥያ ህልም ተግባራዊ ለማድረግ ሞክሮ ነበር። ሆኖም አልተሳካለትም፤ የአለም ኤኮኖሚ ቀውስ ገና በጅማሬ ላይ ስለነበር የአሜሪካና አውሮፓ ህብረትን የተባበረ ክንድ መመከት አልቻለም። በወቅቱ የጆርጅያ ፕሬዚዳንት ሚካኤል ሳካቪሊ «የራሽያ ጦር ከጆርጅያ የማይወጣ ከሆነ አሜሪካና አውሮፓ ህብረት ራሽያን እንደሚወሩ የሚገልፅ ደብዳቤ ልከውልኛል ሲል ለፑቲን በስልክ ነገረው። የፑቲን መልስ ቃል በቃል እንዲህ ይላል «ወረቀቱን ጠቅልልና ቂጣቸው ስር ወትፍላቸው!»

## ራሽያ ምኔ ናት?

ራሽያ ምንም ላትጠቅመኝ አንድ ሙሉ ገፅ አልሰጣትም። ዊንስተን ቸርችል እንዳለው ሩስያውያን አገራቸውም ልባቸውም ሩቅ ቢሆንም ቅሉ ጠቀሜታቸው ግን አይናቅም። ከሁሉ በላይ ግን የፑቲንን ሃይለኛነት ያዩ አንድ ጀግና ተነስቶ ‹ግዛታቸን እስከ እየሩሳሌም መሆኑን ተናግሮ ቢያደፋፍረኝ ወድጀው በሞትኩ ነበር!» በዚህ የመነጣጠልና የመበጣጠስ ክፉ ዘመን አንድ ጀግና ተነስቶ ልጠቅልላችሁ ካላለን በውነቱ መላም የለን፤ ወጣቱ ግን እንደ ስፊንክስ እልም ብሎ የተኛ ይመስላል፤.....

‹ያገሬ ወጣቶች ተነሱ እባካችሁ


................ፑቲንን አይታችሁ!

ብዬ እስከገጥም ለምን ትጠብቃላችሁ?›

የፑቲን ራዕይ ከተሳካ አገሬ ሌላም ቭላድሚራዊ ጥቅም አታጣም። እንደሃሳቡ ፑቲን አሜሪካን የሚገዳደር ሌላ ዓለም መፍጠሩ ነውና የድሆች አማራጭ በአንድ መጠን ከፍ አለ ማለት ነው። እነ ዶክተር ኢንጂነር እንደነገሩን ቭላድሚር ፑቲን ኢትዮጵያውያንን የማልማት ከፍተኛ ፍላጎት እንዳለውም አንርሳ። በአጭሩ የራሽያ ማዬል ድህነትን፤ ዘረኝነትንና አምባገነንነትን ለማምለጥ ሌላ መጠጊያ ይፈጥርልናል። ..........እና የፑቲን ‹ዩሮዥያ› መምጣቷ ካልቀረ መጥታም ዲቪ መጀመሯ ካልቀረ ካሁኑ የሩስያ ቋንቋ መማር ሳይሻል ይቀራል ብላችሁ ነው? ለማንኛውም есть благословенный выходные ብለናል (‹የተቀደሰ ሳምንት ይሁንላችሁ› እያልኳችሁ ነው በተስፋይቱ ምድር ‹ዩሮዥያ› ቋንቋ!)





# እኔ ለማ አዲያሞ ነኝ! የአጤ ምኒልክ አያት!

ከኃይለየሱስ ባላ ጥርቦ(ፒኤች ዲ ተማሪ)



(ጠብቀዉ የሚነበቡ ፊደሎችን አድምቂያቸዋለሁ፤ ለምሳሌ "ጥብቅ" ሳልቶ ሲነበብ "ጥብቅ" ጠብቆ ይነበባል)

‹ምንይልህ ሸዋ› ቅዳሜ ነሐሴ 12 ቀን በ1836 በሥልጣኔዋ ሀገር ኢትዮጵያ ከምትገኝ አንኮበር በምትባል ከተማ እንደነዉር ከምትቆጠር ከአንዲት ገረድና ድሃ ተወለደ:: ይህች ሰው ወ/ሮ እጅጋየሁ ለማ አዲያሞ ትባላለች:: የንጉሥ ሣህለሥላሴ ሚስት የወ/ሮ በዛብሽ ገረድና የልጆች ሞግዚትየነበረች::

የአንኮበር ቤተክርስቲያን አለቃ የነበሩት የመምህር ምላት ገረድ አንድ ቀን ጧት ለጓደኞችዋ "ዛሬ ማታ በህልሜ ከብልቴ ፀሐይ ስትወጣ አየሁ"! ስትል ትነግራቸዋለች:: አለቃ ምላትም ወሬዉን ሲሰሙ ‹እንግዲያዉ ይህ ከሆነ "ላይ ቤት ትሂድ!"› … የአንኮበሩ የንጉሥ ሣህለስላሴ ቤተመንግስት ኮረብታ ላይ በመሆኑ አገሬዉ በተለምዶዉ "ላይ ቤት" ይለዋል::

የንጉሥ ሣህለስላሴ ባለቤት ወ/ሮ በዛብሽ "ያ!" በህልም የታየዉ "ፀሐይ" ከልጃቸዉ ከሰይፉ እንዲወለድ ፈለጉ፤ ግን ሰይፉ የሚወዳት ሌላ ሴት አለችዉ፤ … ለወንድሙ "ሌላ ሴት ከሌለህ እሜቴ የላኳትን ያቺን ገረድ! ውሰድልኝ" አለዉ፤ ልጁ ተፀነሰ! ሲወለድም "ምንይልህ ሸዋ በሉት" አሉ::

በህልማቸዉ ከምንይልህ ጋር አብረዉ ቆመዉ ከእሳቸዉ ጥላ የልጁ የምንይልህ ሸዋ ጥላ በልጦ- በእግር የረገጡትን መሬት ሲያለካኩ የልጁ ረዝሞ አዩ- ከዚያም "ምኒልክ የኔ ስም አይደለም፤ የሱ ነው" አሉ::

በአንድ ጎኑ የእጅጋየሁ ለማ አዲያሞ ልጅ መሆኑ በምኒልክ እድገት ላይ ከባድ ተፅእኖ ነበረዉ:: ከገረድ ከድሃ መወለድ እንደነዉር ተቆጥሮ "ስለህዝብ ዕረፍትና ጤና" ሲባል በአንጎለላ መቅደላ ኪዳነምህረት ተነስቶ ጠምቄ በሚባል አገር በሞግዚት አኖሩት፤ መንዝ ዉስጥም ጠምቄ በሚባለዉ አምባም ከእናቱ ጋር ሰባት ዓመት ተቀመጠ::

በኢትዮጵያ የዕድገት ታሪክ ተዋስኦ ላይ ፤በሃዋሳ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የታሪክ መምህር እና ተንታኝ ከሆነዉ አባቡ አሊጋዝ ጋር ስንጨዋወት፤ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲት ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት መምህሩ ከነበሩት ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ጋር አንኮበር ለመስክ ጥናት ልምምድ በሄደበት የታዘበዉንና በአስረጂነት የጠቀሰልኝን እዚህ ጋ አነሳለሁ:: የኢትዮጵያ ታሪክ በአባቡ አሊጋዝ እጅ ያምራል፤ እስከነሚዛናዊነቱ! አንድ ቀን እርሱ ራሱ እንደሚያጫዉተን እና በቀለም ቀንድ እንደሚመጣ ተስፋ በማድረግ ስለአንኮበር ያጫወተኝን ይኸዉ::

በአባቡ ትንታኔአንኮበር እንደመልክዐ-ምድራዊ አቀማመጥዋ ሁሉ የአሰፋፈር ታሪኳም በላይና ታች ቅራኔ ላይ የተመሠረተ ነው፤ ከተለያዩ የሀገሪቱ ከተሞች የአሰፋፈር ታክቲክ ታሪክ አንፃር ከታየአንኮበር ጢኒጥዋኢትዮጵያ ናት:: በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ያሉ መኖሪያ ከተሞች ሽንሽናቸዉ በአንኮበር ልክ የተሰፋ ይመስላል:: ከተማዎቹ ሲቀደዱ የትኛዉ ቤተሰብ መሃል እና ኮረብታማዉን ክፍል የትኛዉ ወደጥግ እንደሚገፋ ለማወቅ አንኮበርን እስከተመሳቀለ ማንነቷ ማየቱ አስረጅ ይሆናል::

አንኮበር ላይና ታች አላት፤ ኮረብታና ግርጌ:: የምኒልክ እናት ወ/ሮ እጅጋየሁ ለማ አዲያሞ መሠረቷ ከታችኛዉ የአንኮበር ሰፈር ነዉ:: የቤተመንግስቱ እና መኳንንቱ መቀመጫ ከላይኛዉ አንኮበር ነዉ::ሸማዉ፣ መጎናጸፊያዉ፣ ዘውዱ፣ የማዕረግ ቀሚሱ፣ ልብሰ መንግስቱ፣ ልብሰ ተክህኖዉ፣ መጫሚያዉ፣ መዋቢያ ጌጥና አምባሩ፣ መቀመጫዉ ከዙፋኑ እስከ በርኩማዉ፣ ቋሚዉ አግዳሚዉ ታች ሰፈር ይሰራል:: የገበታ ዕቃዉ፤ የብር፣ የነሃስ፣ የወርቅ መቅረቢያዉ፣ ማቅረቢያዉ፣ ማብሰያዉ፣ መስሪያዉ፣ ሰፌቱ ከዚያዉ ነዉ:: የሁሉም ነገር ማምረቻዉና ገበያዉ እነለማ አዲያሞ ሰፈር ነዉ:: የሥነ ዉበት ንድፍ አውጭዎቹ ና ባለቤቶቹ እነ ለማ አዲያሞ ናቸዉ:: ሚናቸዉ ዝምብሎ ያለውን እውነታን ማንፀባረቅ ብቻ አይደለም፤ አዳዲስና ማራኪ የሆኑ ምናባዊ ቅርጾችን በማዉጣት በመፍጠር ለራሳቸዉ ሳይሆን ለሌላዉ ደስታ ማስገኘት ነዉ:: መንፈሳዊም ቁሳዊም:: የአምልኮ እቃዉ መስቀሉ፣ ከበሮዉ፤ ጽናጽሉ፤ መቋሚያዉ፤ መለከቱ፣ ነጋሪቱ፤ የጦር እቃዉ ሁሉ ጋሻዉ፣ ጦሩ፣ ጎራዴዉ፣ ሰገባዉ፣ ኮርቻዉ፣ ግላሱ መምጫዉ የት ነዉ? አይባልም! ታች አንኮበር ነዉ:: ብልሃተኛዉ፣ ወጌሻዉ፣ ወቅት ተንባዩ፣ ሐኪሙ፣ አናፂዉ ማነው?ቢባል በመሠረቱ የራሱ ዓለም የሌለዉ በሰዉ ዓለም በሰዉ ቤት በህልሙም ሳይቀር የሚፈጋዉ፣ በግልፅ አማርኛ ሲቀመጥ፣ ፉጋ ፋቂ ቀጥቃጭ አንጥረኛዉ ወዘተረፈናሰፈሩ ነዉ::ይኸ ጥብቅ ሰፈር ነዉ፤ ለምን? አንድ ነገር ይወጣል ተብሎ ስለሚጠበቅ፤ "የፈሩት ይደርሳል፣ የጠሉት ይወርሳል!" እንዲል ብሂሉ:: ምኒልክ የትና እምን ውስጥ ተወለደ? አራስ ሳለ ?ዕልል ስንት? ተብሎለት ይሆን?

ሥልጣኔና እንቆቅልሽ

ልክ እንደአንኮበር ሁሉ የምኒልክ ታሪክም የሚሊዮኖች ኢትዮጵያዊያን ታሪክ እና የዕለት ተዕለት ዉሎአችን ስንክሳር ነው:: በየአካባቢያችን የአሰፋፈር ታሪካችን ስንፈትሽ"ታች አንኮበር" አለበት፤ ለማ አዲያሞዎች አለንበት/አሉን፤ እጅጋየሁዎች አለንበት/አሉን:: ይህ ታሪክ ከተፈፀመ 200 ዓመት ሊሆነዉ 20 ዓመት ቀርቶት ባለንበት የተገኘ አዲስ ነገር ቢኖር ሁሉም ክብሩና ስብዕናዉ ከያኔው "ታች አንኮበር" ብሶ የታች ታች መሆኑ ነዉ:: ራስን መሆን ራስን ከመቁጠር ይጀምራል፤ ራስንና የራስን ከመዝለል በፍፁም!በነገራችን ላይ፤ "የአድዋ ታሪክ የመሪዎች ታሪክ" ብለዉ ለሚያብጠለጥሉ እና ስቅቅ የሚል መከራከሪያ ለሚያሰሙ የኢህአዴግ ሚኒስትርና ዴዕታዎች፤ አጤ ምኒልክ የባሪያ ልጅ መሆኑ እንዲህ በግልጥ ሲቀመጥ (አያዩትም እንጂ፤ ንቀታቸዉ!) ምን ያህል ብያኔያቸዉጭፍን፣ካልሰከነ አይምሮ እና ሩሁን ከሳተ ህሊና እንደፈሰሰ ይረዱት ነበር::

ፉጋ ሲጤን

ብዙ ፀሀፊዎቻችን የፉጋ ነዉራችንን እዉነታ በቁጭት እና እልህ በተቀላቀለበት ስሜት በቅንዓት ማብጠልጠል ይቀናቸዋል:: ነገሩ እንቆቅልሽ አለዉ፤ ቀዳዳዉ ከዚህ ሲሰፋ ከዚያኛዉ በኩል ብል እንደበላዉ ጨርቅ እየተተረተረ ማስቸገሩና ግራ ማጋባቱ:: በ1987 ዓ/ም በታተመዉ የወላይታ ምሳሌያዊ አባባሎች መዝገብ ላይ የታዘብኩት ለዚህ አባባሌ ዓይነተኛ ማስረጃ ነዉ:: እዚህ ላይ የመዝገበ ምሳሌዉ ሥራ በባለቤትነት የተያዘዉ በባህል ሚኒስቴር መሆኑ ምሳሌዎቹም በአካባቢዉ ካሉት የተለያዩ ዘዬ ተናጋሪዎች የተሰባሰቡ መሆናቸዉ በቅድሚያ ሊሰመርበት የተገባ ነዉ:: በዚህ የአስተሳሰብና የርዕየ-ህሊና ምጥቀትን እንደሚያሳይ በታመነ ግሩምና ድንቅ የምሳሌዎች ስብስብ፤ የአባባሉ ገስጋሽ ወይም ተቀባይ ማንነት የሚያመለክተዉ ከላይ "የተፈራዉ ወይም የተጠላዉ" ያልኩት ፉጋ፣ ፋቂ፣ ወዘተ ተዋስኦን የያዘ ከሆነ ልክ በቃል "እንትና፣ እነእንትና" እንደሚባለዉ በ … (ሦስት ነጠብጣቦች) ይገለፃል:: ምንማለት ነዉ? ምንድነዉ ያቃታቸው? ስንቶች ነን ያልተነገርን እንዲህ በነጠብጣብ የቀረን? ስንቶች ነን መነገር የማይገባን? የማንነገርስ? ለምን? እስቲ አንዳንድ ትንታኔዎች:-

ኢትዮጵያዊው ሶሽየል አንትሮፖሎጂስት ፕሮፌሰር ዳታ ዴአ በዚህ ረገድ ብዙ ዓለም አቀፍ እዉቅናን ያተረፉ በጥልቅ ሳይንሳዊ ስልቶች ተደግፎ ያበረከታቸዉ በግልም በጥምር ያወጣቸዉ ሥራዎች አሉት:: የፉጋን የአሰፋፈር እዉነታዎችን በመረመረበት በአንድ ሥራዉ ላይ፤ፈልፍሎ ያወጣዉ ትርክት እንደሚያስረዳዉ ችግሩ ከመሬት ጥበት ጋር የተገናኘ ወይም ከሃብት ድልድል መዛባት የመጣ ሳይሆን ከሌላ "ሥልጣኔ ከተል" እና እምነት ቀመስ ፈሊጥ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ይነግረናል::

ችግሩን ባጠናበት አካባቢ ባለዉ "የላይ ሰፈር" ሰው እምነት ከሆነ፤ መገለልና መገፋቱ የመጣው: -‹ከሁሉም በላይ ለሁላችንም "የህይወታችን ህልዉና መሠረት" በምንለዉ አፈር ላይ ያላቸዉ አመለካከት እና ድርጊታቸው ነዉ ለዚህ ያበቃቸዉ:: እነኝህ ሰዎች አፈሩን ያቃጠሉ ለማን ይመለሳሉ? አፈርን ማቃጠል ፈፅሞ ከሰው ልጅ የማይጠበቅ ድርጊት ነዉ፤ ነዉር ነዉ› ሚል ነዉ:: ጥያቄዉ:- ለቆዳ አለስላሹስ? ከሰማይ ተነጋግሮ (ምንም ትንግርት ቢመስልም) ሀገሬዉን የገበያ ዉሎዉን ሊያበላሽበት የተንጠለጠለ ደመናን የጥበብ እቃዉን እያጫወተ እያዝናና ለሚበትነዉስ? በነገራችን ላይ ይህ ከላይ አፈር ማቃጠል ተብሎ የተብጠለጠለዉ ዓላማዉ አፈር ማቃጠል ሆኖ አይደለም፤ ባዮቹም አያጡትም:: የዘመናዊዉ ዓለም ቴክኖሎጂ መሰረትና የአገራትና መንግስታት ኢኮኖሚ

# <<አልዘሩ - በቀል!>>

ደራሲ ይባቤ አዳነ
E-mail፡- wisdomtare27@gmail.com

ከተነጠፊው ጀንዲ ላይ ተነጥፌያለኹ:: ሌላ ሰው መጥቶ ቢገነደስብኝ አልፈርድበትም፤ እኔ 'ራሴ ለምንጣፍነት የተሰናዳሁ ጀንዲ እንጂ፣ ምንጣፍ ላይ ለመተኛት ሥልጣን የተሰጠኝ ክቡር ሰው አልመስልም:: አባጣ-ጎርባጣ ቅርፃቅርጼ ተደምጥጦ የጋለሞታ አነባብሮ መስያለሁ:: ምንጣፌ ላይ ምንጣፍ ኾኛለሁ:: በጢንብራዬ ተተክያለሁ:: ጀንዲው ከከብት ቆዳ መሠራቱን ዘነጋሁት መሰለኝ አይሸተኝም፤ ወይም የማሽተት ሥልጣን የተሰጠው የስሜት ሕዋሴ እንደ ኢሕአዴግ ሓላፊነቱን ዘንግቶ መቼ-አባቱ ሙስና እንደለመደ አላውቅም፣ የግል ሥራውን ለመሥራት ወደ ውጭ ወጥቷል::

የቁራ መልእክተኛ የሆነ አካል የተሸከመውን ሓላፊነት አሽቀንጥሮ ጥሎ ለግላዊ ጥቅሙ ብቻ እንደቆመ ይኖራል:: ‹እኔ ከሞትኹ ሰርዶ…› አለች - የኔ ጎረቤት የሆነችው ዕድሜ-ጠገቧ አህያ::

ጭልጥ ያለ እንቅልፍ፤ አእምሮዬ ሥራውን ወጥኗል:: በሕልም ታንኳ ላይ ተሳፍሮ ስለ ተፈጥሮ ያወጣ - ያወርድ ጀመረ፥ ‹‹አንተን ከጭቃ ጠፍጥፎ የገነባህ አምላክ፣ የውኃ ሦስተኛውን እጅ ወደ ሰማይ አወጣው፤ ጠፈርም አደረገው:: እስከ ምድር ዳርቻ ድረስም አጸናው:: ሲነጋ በመጣ ጊዜም ወደ ጥልቁ ይወርድ ዘንድ ውቅያኖስን አዘዘው:: ውኃው ከወሰኑ እንዳያልፍ ገሰጸው፤ ውኃዎች እንዳይጣሉም በቃሉ ማዕቀብ ጣለባቸው፤ መሬትንም በውኃ ላይ አስቀመጣት:::››

‹‹በሌላኛው ቀንም፥ ‹አምላኬ ሆይ፥ የምለብሰውን ልብስ ስጠኝ!› ብላ ምድር ፈጣሪዋን ለመነችው፤ ፈጣሪዋም የቻይና ሱሪ (ቻይና እና ሌሎች ዓለማት ያኔም በ'ርሱ› ዘንድ ነበሩ) አስመጥቶ ሊወጣጥራት አልፈለገም፤ እሷነቷን እንዳታጣ በልዩ ጥንቃቄ ሊጠብቃት እንደሚገባ አልዘነጋውም፤ በሱሪ ኃይል የመሬትን ክብ ቅርጽነቷን ሊያሳጣት አልወደደም፤ ገላዋ ላይ የሚመላለሱ መባርቅትን እና የሚነፍሱ ነፋሳትን አሳጥቶ መልካም ጠረኗን እንድታጣ አልፈቀደም፤ በነፋስ ሽውታ የመናፈስ መብትን ለመላ አካሏ አከናነበው እንጂ:::››

‹‹ስለሆነም በማጭድ የሚታጨዱ ሳሮችን፣ በምሳር የሚቆረጡ ዕፅዋትን፣ በእጅ የሚለቀሙ አትክልትን በየወገኑ ለመሬት ሰጣት:: ነጻ ምሳ የለምና ፈጣሪዋ አስከትሎም፥ አዕዋፍን፣ እንስሳትን፣ አራዊትን በየወገኑ ታስገኝ ዘንድ ምድርን አዘዛት፤ ምድርም ከምትፈልገው ይልቅ የሚያስፈልጋትን ማስተናገድ ነበረባትና ‹ለምን በቻይና ሱሪ አላጣበቅኸኝም!› ብላ ሳታኮርፍ፣ በታዘዘችው መሠረት እነዚህ ፍጡራን ወንድ፣ ሴት፣ ታናሽ እና ታላቅ ሆነው እንዲገኙ አደረገች:::››

አእምሮዬ ምቹ መኻታ ላይ መተኛቱን ተገንዝቧል፤ ጎርበጥበጥ ያለ መኻታ ይመቸዋል:: ምቹ ፍራሽ ለቂጥ ሥራ እንጂ ለአእምሮ ተግባር ትግበራ የማይረባ መሆኑን ነገረኝና ፈጣሪ ስለሸመናቸው ሌሎች ተፈጥሮዎች ቀጠለ፥ ‹‹የፀሐይ፣ የጨረቃና የከዋክብት ነገረ-ተፈጥሯቸው እንደሚከተለው ነው፡- የጨረቃና የከዋክብት አፈጣጠራቸው፥ ከነፋስ፣ ከውኃና ከብርሃን ነው፤ የፀሐይ አፈጣጠሯ ደግሞ ከእሳት፣ ከነፋስና ከብረሃን:::››

‹‹ይህን ሁሉ ድግስ ደግሶ ነው፣ አምላክ ካለመኖር ወደ መኖር ዓለም የጠራህ፤ እናም አንተ ሁሌም የፈጣሪህ ዕንግዳ ነህ፤ ዘላለማዊ ዕንግዳ:: ፈጣሪህ በፈጠረልህ ፍጡራን ስትስተናገድ እንድትኖር ሥልጣን የሰጠህ የዘላለም ዕንግዳ ነህ፤ አድረህ - ውለህም መዳብ የማትሆን ወርቅ ዕንግዳ:: አንተ ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ የተፈጠርኽ ልዩ ዕንግዳ፤ ምድረ-ገነት የሆነችው ኢትዮጵያ ልጅ:: ይህን ግን ታውቃለህ? ቀሽም! አካላዊ ዐይንህን ይመስል የ'ሩቁን ማንጋጠጥ እንጂ የቅርብህን የማታይ ጅላጅል ነህ! ነጻ ሆነህ መፈጠርኽን የማታውቅ ሞኝ! ነጻ ሆነህ ባትፈጠር ኖሮ ስንት ፈረንጅ ሀገርኽን ረግጦ እየገዛ እንደ ፍላጎቱ እየደፈጠጠህ ይኖር ነበር!? ይህን ባለመገንዘብህ ነጻነትን የሚያጎናጽፍ አካል አንጋጠህ ስታይ ዕድሜ-ዘመንህ እንዲሁ ባከነ:: ነጻነትን ተጎናጽፈህ መፈጠርኽን ለምን አትገነዘብም!? ነጻነትን የሚያቀዳጅ አካል ሳይሆን መፈለግ ያለብህ ነጻነትኽን እየሸረሸሩ ለሚኖሩ ደንባራ ባለሥልጣናት እጅ አለመስጠት ነው:::››

‹‹ይህን ባለመረዳትህ የ'ሩቅ ባለሥልጣናት ነጻ ያወጡኛል ብለህ የምትማፀን ቂል ሆነኻል:: እነርሱ ይህን ማድረግ የሚፈልጉና የሚችሉ ቢሆን ኖሮ በሳምንታት ውስጥ አያጠናቅቁትም ነበር!? ያንተ መሪ ከእነርሱ ጋራ በጥቅም የተሳሰረና የእነርሱ ገረድ መሆኑን አታውቅማ! ነገረ-ሥራው ሁሉ ‹ለክፉ ቀኔ› ለሚላቸው ሀገራት አንፋሽ - አከንፋሽ፤ ሀገሩንና ዜጎቹን ደግሞ አኮሳሽ- ደቋሽ መሆኑን ዘንግተኸዋላ! ላገቡለትም ላስገቡለትም ምዕራባዊ ሀገራትና አምልኳቸው እንደ ሆቴል አስተናጋጅ እጁን አጣምሮ ‹ምን ልታዘዝ?› እያለ የሥልጣን ዕድሜውን የሚያራዝም አሽርጋጅ መሆኑን ልብ አላልከውማ!… ለዚህም ነው የራስህን ኃይል ቅርቃር ውስጥ ወሽቀህ የሌላው ኃይል (ሰዋዊ) ይታደገኛል ብለህ ስትባዝን የምትኖረው፤ አልዘሩ በቀል!›› አለኝ - ተበሳጭቶ::

‹‹አለዘሩ - በቀል!› እስከማለት የደረስኸው ይህን ያክል ምን አጠፋኹ?›› አልኩት - ቅጭም ብየ::

‹‹ምን አጠፋሁ!? ጥፋትኽስ ልክ አለው?! የለውም:: ጥፋትኽን ዘርዝሬ ከምጨርስልህ ፀጉርህን ቆጥሬ ባሳውቅህ ይቀለኛል:: የምትጽፈው - የምታወራው ሌላ የምትኖረው ሌላ፤ ስለትዳር ምንነት አውራ ቢሉህ፣ መዐት ነገር ትዘከዝካለህ፤ ቤትህ ሲፈተሽ ግን ሚስትህን ባዶ ቤት አስታቅፈኻት እስከሌሊቱ ስምንት - ዐሥር ሰዓት ድረስ ትጠጣለህ፣ ትዛብራለህ፣ ትስክራለህ፣ ‹ለማዝናናት የተፈጠረ› በሚል ምሥጢራዊ ሽፋን ዐለምን ለማዝናጋትና ለማደንቆር የተፈበረከው የእናጅሬው› እግር ኳስ ካለም፣ ከወንድምህ ጋራ እየተዳማህ አንዱን ትደግፋለህ ሌላው እንዲወድቅ ትሳላለህ፤ ያንተ ሕይወት መውደቅ የጀመረው ያኔ እንደሆነ ግን አይታይህም- ዐይነ-ልቦናህ ተጋርዶ:::››

‹‹ካልሲ ነው ቸልሲ (ለእነዚህ የሚሆን ጉርጅ ስላላዘጋጀሁ ስማቸውን በቅጡ ላልጠራው እችላለሁ፤ አንተ ግን የተጫዋቾችን የጫማ ቁጥርም ታውቀዋለህ:: የቤትህን ቁጥር ቀበሌ ቢጠይቅህ ግን ማስታወሻ ወደማገላበጡ ትሔዳለህ - ለዚያውም ከጻፍኸው) ብቻ ከሁለቱ አንዱና ማንቸስተር በእግር ሲራገጡ አንተም ለመዝናናት መሔድኽን ትረሳውና በገዛ ‹ሪሞትህ ወደመጉላላቱ ትሸጋገራለህ:: 'ራስኽን እየረገጥህ እንቅልፍ አጥተህ ስትነፍዝ ውለህ - ታድራለህ:: አሁንማ ብለህ ብለህ ደሞ ኢትዮጵያዊነትን መስበክ ትተህ ‹እኛ ብራዚል ነን!› ማለት ጀምረኻል አሉ፤ ወይ መደናቆር! ጠርዝ የሌለው ድንቁርና!››

‹‹ኸረ ምኑ ቅጡ፤ ‹ካልዋሹ መኖር አይቻልም› እያልኽ ሕዝብና ጥበብ ላይ ሳይቀር ደፋር ውሸት መዋሸት ጀምረኻል አሉ:: (ይህ ደፋርና ያገጠጠ ውሸት የተወለደበት በዓለ-ልደት ባለፈው ግንቦት 20 መከበሩን አስታውሼህ ልለፍ መሰለኝ:: መቼም አንተ አታፍርም፤ ‹ለብሔር ብሔረ-ሰቦች የነጻነት ጎሕ የቀደደበት ዕለት ነው› ብለህ አሁንም ትቀደድብኝ ይሆናል)››

‹‹በዘመነ-መንግሥትህ ‹ውሸት› በ'የዕለቱ የሚከበር ቢሆንም ግንቦት 20 ግን በልዩ ኹኔታ ይከበራል:: (የሚያመልኩትም አሉ) የ‹ውሸት› ቀን መከበሩን የሚያበስር ብስራት፣ ገና የአህያ ሆድ እንደመሰለ ርችት ነው ኩርንችት የሚሉት ይተኮሳል- በዕለተ-ውሸቱ ልክ:::›› ውሸት ውሸት ውሸት ውሸት ውሸት ውሸት ውሸት ውሸት ውሸት ውሸት ውሸት ውሸት ውሸት ውሸት ውሸ…ት ሃያ ሦስት ዓመት ሙሉ ውሸት፤ እንደገና ለሃያ ዐራተኛ ዓመት ውሸት ተጀመረ… 2007 ዓ.ም. ላይ ገመዱን ቁርጥ - እምሽክ!››

‹‹ለዚህ ሁሉ ልፍለፋዬ የሚገላግለኝ የታላቁ ባለ-ቅኔ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድኅን ለዐፄ ምኒልክ የገጠመው ተውኔታዊ ግጥም ሳይሆን አይቀርም፤ ተከታተለኝ!

‹‹የአውሮፓ ኃያላን በርሊን፣ የአፍሪካን ካርታ በጫጭቀው
ተካፍለው፣ ዳግም እንደ ጨርቅ፣ መልሰው ተብትበው ሰፍተው
የታሪክ ቡትቶ አልብሰው
እናንተው ይሉናል፣ የማትስማሙ ስንኩሎች
የእርስ በርስ የአንድነት ጠሮች
ያልታደሉ::
ጨለማ በርቶላችኋል
ብርሃን ጨልሞባችኋል
ደስ ይበላችሁ ይላሉ
ያልታደሉ::
ወገኖቼ ምን ዘመን ነው?!
እውነተኛነት እንደሐሰት፣ ሐሰተኛነት እንደእውነት
የተገለባበጠበት?!
ጮሌ የተከበረበት
ሌባ የተጀገነበት
ቀላል የተሞገሰበት
ጨዋ ሰው የቀለለበት
ፍትሕ የተጨለመበት
ደንቆሮ ብቻ እሚያውቅበት
ሊቅ የሚደነቁርበት
ምን ዘመን ነው ዘመዶቼ?!
ባላንጦች ጋራ፣ መደራደር መቼ ዋዛ
ቅስም ያከስማል ቀኖናቸው፣ ሳይበስል እንደጠነዛ
ዳዋ እንደለከፈው ዋንዛ!
አጥንት ያረግባል ዜቃቸው
ብቻ ለሥልጣኔ ተክል
እማይከፍለው ዋጋ የለም
አገር ነውና የታሪክ ደም…በሥልጣኔ እሚታደም::…
ሥልጣኔ እኮ ፅንስ ነው



# አገር ስጡኝ - አገር አልባ ባለሀገር (ባላገር)

(በእውተኛ ታሪክ ላይ ተመስርቶ የተለያዩ ሰዎችን ቃለ መጠይቅ በማድረግ የተዘጋጀ)

በሙሉቀን ተስፋዉ (የክፉ ሰዉ ሽንት መጽሀፍ ደራሲ)
Email: mulukentesfaw@gmail.com

ክፍል ሁለት

**ባለፈው ሳምንት ባልደረባችን ሙሉቀን ተስፋዉ <አገር ስጡኝ - አገር አልባ ባለሀገር (ባላገር) በሚል የጀመረውን የአንድ ወጣት የስቆቃ ታሪክ ጽሁፍ ቀጣይ ክፍል ይተርክልናል። ግለሰቡ አገሩን <ቀሽም> እያለ ይሰድባል። አገሩን የሚሳደብበት የስድብ ፋብሪካ ቢኖር ምናለበት እያለም ይመኛል። ክፍል ሁለት እነሆ . . .**

እያሉ እያሉ ወያኔዎቹ በእኛ ሰፈር በግልጽ መታዬት ጀመሩ። ሰፈራታችን ገደል ይበዘዋል። ሀረግና ቅጠል እየለበሱ ሲለማመዱ ይዉሉና ወደ ማታ ከዋርካው ስር ሆነው በትግርኛ ሙዚቃ ያቀልጡታል። አንድ ቀን ጠዋት ያለልማዴ ከተኛሁበት መደብ ሊነጋጋ ሲል ነቃው። ሰማዩ ገና የአያ ሆድ አልመሰለም። የተኛውበትን አጎዛ ግድግዳ ላይ ሰቀልኩና ወደ ውጭ ስወጣ በባልዲ የተቦካ ብዙ ሊጥ እንጀራ እናቴ ትጋግራለች። ሁለት ቁምጣ የለበሱ እንግዳ ሰዎች ከእሳቱ ዳርና ዳር ተቀምጠው ግራ በገባው አማርኛ ያዋሯታል። እኔም ምስቅልቅል ያለ ስሜት መጣብኝ። አንደኛ እንደዚህ ያለ አማርኛ የሚናገር ሰው በዚያ ላይ ጸጉራቸው መቀስ አይቶት የማያውቅ የተንጨባረረ አይቼ አላውቅም። ሁለተኛ እናቴ በባልዲ ያለ ሊጥ ስትጋግር አይቼ አላውቅም። የእኔ እናት ሊጥ የሚቦካበት እቃ ከሸክላ የተሰራ ‹‹ቡሃቃ›› ወይም ‹‹ቡሆ እቃ›› የሚባል እንስራ ነው።

ሶስተኛው ደግሞ እናቴ ያን ያክል እንጀራ በውድቅት ሌሊት ለምን ትጋግራለች አልኩ። በእርግጥ ሁሌም ቢሆን ቤተሰባችን ብዛት ስላለው በርካታ እንጀራ ትጋግራለች። ግን ይህን ያክል አይሆንም። እንጀራው ደግሞ ከመጠን በላይ ነጭ ነው (ቆይቶ ግን የስንዴ እንጀራ መሆኑን አውቂያለሁ)።

ከቤተሰብ ካሉት ሴት ልጆች የሚዳር አለ ብየ እንዳላስብ የሰርግ ሰዓት አልነበረም። ሁዳዴ ይሁን የታህሳስ (የገና) በደንብ የማላስታውሰው ጾም ይጾማል። ብዙ ጊዜ እህቶቼ ሲዳሩ እነርሱም እኛም ሳንሰማ ለሰርግ ዝግጅት ሲደረግ ብቻ ‹‹ነቄ›› እንላለን። ከኔ በላይ ያሉት ከሁለቱ ውጭ ሁሉም በዚህ መልክ አግብተዋል። እንዲያውም እናቴ፣አባቴ ጦርነት ሂዶ ከቀረና ወንድምጋሽም ከሞተ በኋላ ብቻዬን ከምሆን እያለች የሁለቱን ልጆቿን ባሎች ከእኛ ጋ ‹‹ውሻ ቁጭ›› አስምጥታቸዋለች። በባህላችን ሴት ናት የተወለደችበትን ቦታ ከባሏ ዘመዶች ጋር ሂዳ ጎጆ መቀለስ ያለባት። በተገላቢጦሽ ከሆነ ግን የመጣው አማች ‹‹ውሻ ቁጭ መጣ›› እየተባለ በዘመነኛ አነጋገር ይፎገራል። ስለሆነም ሁለት ውሻ ቁጭ የመጡ አማቾች ነበሩን።

ወደቀደመው ነገር ስመለስ እናቴን እንዳልጠይቅም በእርስ በእርሳቸው በእንግዳ ቋንቋ ከእናቴ ጋር ደግሞ ወደ አማርኛ በተጠጋ ምልክት በበዛበት ቋንቋ ሲያወሩ ፈራሁ። በእኛ አካባቢ ሌላ ቋንቋ ተሰምቶ አይታወቅም በዚያን ዘመን። እርግጥ ከሰሞኑ ወያኔዎች/ታጋዮች ሲጮኹ ሰንብተዋል። እነርሱም የትግራይ አገር ሰዎች እንደሆኑ ሰምቻለሁ።

ወያኔዎቹ ከሰፈራችን ከሌሉ (ከተሰወሩ) ከብት ስንጠብቅ የምንውለው ጉብሎች እነርሱ የሚያደርጉትን ሀረግና ቅጠል እየለበስን ተኩስ እንለማመዳለን። ወያኔዎቹ ሲጠራሩ ብዙ ጊዜ ‹‹በርሄ›› ‹‹ገ/ማርያም›› ... እያሉ ስለሆነ እኛም በእነርሱ ስያሜ ስማችን እንሰይምና እንጮሃለን።

አንድ ቀን በሰፈር ከሚገለባበጡት ሚጎች ይሁን ከሌላ አውሮፕላን ብቻ አንደ ኬሻ ሙሉ ነገር ከብት ከምንጠብቅበት አካባቢ ወደቀ (እኔ በዚያ ሰዓት ከከብት ጥበቃ አልፌ እርፍ ሁሉ አገላብጬ አርስ ነበር። ግን በጋ ላይ ጎረምሳዎች ሁሉ ከብት ይጠብቁ ነበር እርሻ ስለሌለ)። የወደቀው ፈንጅ ይሁን መና አላወቅንም ግን ለመያዝ ተሯሯጥን። ኬሻውን ስንቀደው ግን በቀይና በቢጫ ወረቀት በአማርኛ ፊደል የተጻፈ በራሪ ወረቀት ነበር። አቦዬ ጻዲቁ ቤተ ክርስቲያን ካሉት የኔታ ጋር የተማርኳት አቦጊዳ ፊደል ተጠቅሜ ለማንበብ ብሞክር ትርጉም አይሰጥም (ለካስ የተጻፈው በትግርኛ ቋንቋ ነበር)። የነበረነው ልጆች ተከፋፍለን ወደየቤታችን ወሰድነው። ከዚያ ቤታችን የአጋምና የግራር እሾህ እየለቀምን እንደ ስቴፕለር መምቻ በመጠቀም ቤታችንን በጋዜጣ አደመቅነው። በጣም የሚያምር ሆነ።

ነገርን ነገር እያሳው የጀመርኩት ጉዳይ ዘነጋሁት። ካቆምኩበት ስጀምር እነዚያ ሁለት ቀጭንና ጨበሬ ሰዎች የተጋገረውን እንጀራ ተሸክመውት ሄዱ። ያን እለት በሌሊት ያስነሳኝን ውቃቢዬን አመሰገንኩት። እናቴን ጠየቅኳት እነ ማን እንደሆኑ።

‹‹ታጋይ ናቸው›› አለችኝ።

‹‹ለምን መጡ? ለምን እንጀራ ጋገርሽላቸው? ስንት ሰዓት ላይ ቀሰቀሱሽ?›› የጥያቄ መዓት አዥጎደጎድኩላት።

‹‹በውድቅት ሌሊት መጡ። አንደኛውን እኮ ውሻው በልቶት በማሰሻ ቶኮስኩለት!! እርቂሁን ባይደርስ ኖሮ ይጨርሰው ነበር።›› አለችኝ ከእናትነት በመነጨ አዘኔታ። (ማሰሻ የእንጀራ ምጣድ ላይ ሊጡ ከመቀባቱ በፊት ለማለስለሻ የሚሆን ከጎመንዘር የተዘጋጀ ዱቄት ነው።) እርቂሁን የታላቋ እህቴ ባል ነው።

እናቴ እንደደበራት ይታወቅባታል። በኋላ ላይ ‹‹ጦርነቱ ከእኛ በቅርብ ቀን መድረሱ አይቀርም።›› አለችኝ። የጦር ወሬ መሰማት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ ባላገሩ ሁሉ በየቤቱ ጥልቅ ጉድጓድ ይቆፍር ነበር። ለምሳሌ ከእኛ ቤት የተቆፈረው ጉድጓድ ከአስር ክንድ በላይ ይረዝም ነበር። ውስጡን በድንብ በእበት ከለቀለቅነው በኋላ እህል በያይነቱ ሞላነው። ከታች ቶሎ የማይበላሹ እንደ ዳጉሳ ያሉ ይቀመጥበታል። በላይ ደግሞ በቀላሉ የሚበላሹት እንደ ገብስ ያሉት አስቀመጥነበት። የተቆፈረው ጉድጓድ አንድ ክንድ ከስንዝር አካባቢ ሲቀር መረባርብ ሰርተን አፈር ሞላነው። በላይ በቃ እንደነበረ ተፈጥሯዊ ቅርጹን እንደያዘ ቀረ። በገበሬ መጠነ እውቀት ማንኛውም የጦር መሳሪያ ቤቱ እንኳ ቢቃጠል ከዚያ በላይ መግባት ስለማይችል ክረምቱን ሳንራብ ለመክረም ነበር።

በዚህ ዓመት ሰላም ቢሆን ኖሮ ከአንዷ እህቴ ጋር ለመዳር እቅድ ነበራትእናቴ። እኔን ብቻ እንዳይድሩኝ ለወታደርነት ደርሷል ብለው ታጣቂዎች አፍነው ይወስዱኛል። ስለሆነም የተዳሩት ሴቶች እንደሆኑ እንዲወራ ታቅዶ ነበር። እንደሰማሁት ከሆነ ከግራርያ (ከእኛ አገር የአምስትና የስድስት ሠዓት የእግር ጉዞ ያስኬዳል) የአንድ ባላባት ልጅ ታጭታልኝ ነበር። እርሷ ግን እንደኔ እህቶች ሳታውቅ ይሆናል የምትዳረው።

ግን እድለኛ ስላልነበርኩ ሠላም በአገራችን ጠፋ። አገር ቁልቢጥ ሆነች። ሰው ወጥቶ መቅረት እንደቀላል የተቆጠረበት ዘመን ሆነ። እንኳን እኔ ላገባ ያገቡትም ባለአልቦ ጋለሞታ ሆነዋል። አንድም ጦርነት ሂደው ሞተውባቸዋል አሊያም ሸፍተውባቸዋል። አገሪቱስ ቢሆን ከወታደር ባሏ ጋር ለመፋታት ሙግት ላይ አይደለች? የተረገመች አገር ከጦርነት ውጭ ሽሏ የማይሞቅ፣ ለማንም ሸፍታ ጭኗን የምትከፍት፣ የወለደቻቸውን ልጆች በልታ የማትጠረቃ ቀሽም ሀገር!!

(አንዳንዴ አገሬን ሳስባት ለመጠቃት የደረሰች ሽለ ሙቅ ላም/ ጊደር ትመስለኛለች። ብዙ ኮርማዎች ሲያሯሩጧት ከዋሉ በኋላ ትደራለች። በመጀመሪያ ግን ኮርማዎቹ እርስ በእርሳቸው ሲዋጉ ይውላሉ። ያሸነፈው ሽለ ሙቋን ጊደር ይጠቃል። በመካከል ግን ተሸናፊዎች ገደል ገብተው ሊሞቱ ሁሉ ይችላሉ።)

የእውነት ኢትዮጵያ በጣም ቀሽም ከርሳም ሀገር ናት። የስድብ ፋብሪካ ባገኝ በጅምላ ተረክቤ ብወርድባት ምንኛ አንጀቴ እንደተቃጠለ ባቃጠልኳት!! ባዲስ መስመር ታሪኬን ልቀጥል...

ወያኔዎቹ እንደሄዱ በዚያው ቀን ረፋድ ላይ በርቀት የምንሰማው የተኩስ ድምጽ እየበረታ መጣ። ከጉና ተራራ እና ከደብረ ታቦር ኢየሱስ የሚተኮሱ ረጅም ተወንጫፊ የጦር መሳሪያዎች ወደ እኛ ሰፈር ማረፍ ጀምረዋል።

ብዙ ሰዎች ሀብት ንብረታቸውን ትተው መሸሽ ጀመሩ። አለማወቅ ከባድ ነው። ወደ የት ብንሸሽ እንኳ በህይወት መቆየት እንደምንችል አናውቅም። ሽሽቱ በደመነብስ የሚደረግ ነበር የሚመስለው። ጠዋት በግምት አራት ሰዓት አካባቢ አንዲት የጦር ሄሊኮፍተር ‹መር› ከተባለ አካባቢ አረፈችና አንድ ሰው ይዛ በጣም ከመሬት ሳትርቅ በእኛ ሰፈር አድርጋ ስታልፍ መስኮቶቿ ሁሉ ተከፋፍተው ይታዩ ነበር። በኋላ ላይ ሲያወሩ እንደሰማሁት ወያኔዎቹ ደብረታቦርን ስለተቆጣጠሩት ሀይሌ መለሠ ወደ ‹ግርቢ› ሸሽቶ በሬዲዮ ተገናኝተው ያቺ የጦር አውሮፕላን የጫነችው እሱን ነው አሉ።

እናቴ፣ እህቶቼ እና የሁለቱ እህቶቼ ባሎች ከኛ ቤት ተሰብስበው ወደ የት መሰደድ እንዳለብን እየመከሩ ነው። እኔ፣ የቤቱ ብቸኛው ወንድ ልጅ የሚተኮስ ጥይት ከብቶቹን እንዳይመታቸው መጠጊያ ወዳለበት ቦታ ለመውሰድ ተፍ ተፍ እላለው።

ድምጹ ከጆሮ ታንቡር የመቋቋም ችሎታ በላይ የሆነ ድምጽ ሰምቼ ስዞር የእኛ ቤት ላይ ቁመቱ ሰማይ ላይ ያለውን ዳመና አልፎ የሚሄድ ቃጠሎና አቧራ ተመለከትኩ። ምን እንደተፈጠረ አላወቅኩም። የሰማሁት ድምጽ ከእኛ ሰፈር እንዳረፈ ገምቻለሁ። ‹ምናለ በህልሜ ቢሆን› ስል ተመኘው። ከቤት ውስጥ እኔ እንኳ ያየኋቸው አስር የሚሆኑ ዘመድ አዝማዶቻችን ነበሩ።

አካባቢው ሁሉ በእሳት ቃጠሎና በጭስ ታፈነ። ለምን ያክል ጊዜ ደንዝዤ እንደተቀመጥኩ አላስታውስም አሊያም አላውቅም። ብቻ በየቦታው የሚያርፍ የጦር መሳሪያ አገሩን ሁሉ በቃጠሎና በጢስ ሸፍኖታል። በየቦታው ቤት፣ ጭድ (የከብቶች መኖ)፣ ባህር ዛፍ፣ ሸንበቆ.... ይቃጠላል።

ከእኛ ቤት አካባቢ የነበረው ቃጠሎ እየቀነሰ ሲሄድ የእኛን ቤት በአይኔ ፈለግኩት። ከቦታው ላይ የለም። መሬት ድረስ የተጋሰ (የተቆፈረ) አፈረ እና የሚነዱ ነገሮች በአካባቢው ይታዩ ነበር። ሰማይ ምድሩ ዞረብኝ። ‹‹እናቴ የት ትሆን? እህቶቼስ?››

መቼም በዚያ ሁኔታ ላይ ሰው ይተርፋል ተብሎ አይታሰብም። ህሊናዬ ግን ማመን አልፈለገም። የሞቀ ነገር ፊቴ ላይ ሲወርድ ታወቀኝ። አዎ እንባዬ ነው። ‹እሪ ኡኡኡ› ልል ፈለግኩና ከአካባቢየ እንኳ ሰው የለም። ጀምበሪቱደም እንደመሰለች አቅጣጫዋን ቀይራለች። (በክፉ ዘመን አሊያም በችግር ጊዜ በጮራዋ (ጸሀይ) ዙሪያ ደም የመሰለ ነገር ይታያል።)

አፌ ደም ደም እየሸተተ ዝም ብየ ጉዞ ጀመርኩ- ጠዋት ሄሊኮፍትሯ ወደመጣችበት አቅጣጫ። የመር ጫካ ግን እየነደደ ይታየኛል። እርግጥ ነው የአሁኑ ጉዞዬ ህይወት የማትረፍ ነገር አይመስለኝም።

አንድ አባቱ የት እንደገባ የማይታወቅ፣ ብቸኛ ወንድሙ በስቅላት የሞተበት፣ ሙሉ ቤተሰቡ በአንድ ከባድ መሳሪያ የተጨፈለቁበት ብቸኛ ምስኪን ልጅ በህይወት ኖረ አልኖረ ምን ትርጉም ይሰጣል? በቃ እኔ ማለት ያ ልጅ ነኝ። ይህ የማወራው ተረት ሊመስል ይችላል -ግን እውነት ነው።

> **አንዳንዴ ሀገሬን ሳስባት ለመጠቃት የደረሰች አገር ትመስለኛለች ፤ አገር ቁልቢጥ ሆነች ሰው ወጥቶ መቅረት እንደ ቀላል የተቆጠረበት ዘመን ሆነ**

ጉማራ ወንዝ አካባቢ ካለ ዋሻ የሰው ድምጽ ሰማው። ያለቁትን ዘመዶቼን ፍለጋ ይመስል የሚንጫጫ ሰው ወደሰማሁበት አቅጣጫ ሄድኩ። በመንገድ ላይ ብዙ የወዳደቀ የሰው አስከሬን አይቻለው። የት ላይ እንደተመታ የማይታወቅ ዝም ብሎ ደፋ ያለ፣ ጭንቅላቱ አሊያም እግ የተቆረጠ ሰው ሬሳ በየቦታው አለ። ይግረምህ ተብዬ ወደ ሰው እየቀረብኩ ስመጣ እስካሁን ድረስ ከህሊናዬ ጋ ፎቶው ያልጠፋ ነገር ተመለከትኩ። አንዲት እናት ህጻን ልጇን ታቅፋ እያጠባች በነበረበት በጥይት ተመትታ ወድቃለች። ህጻኗ ደግሞ የሞተችውን እናቷን ትጠባለች። ባለቅኔው፣

ሞጣ ቀራኒዮ ምነው አይታረስ፣
በሬ ሳላይ መጣሁ ከዚያ አስከዚህ ድረስ።

ያለው እውነት ነው ለካ። እነዚህ ሙታን እድለኞች ናቸው። ቢያንስ አስከሬናቸው ወዳድቆ አለ። የኔ ዘመዶች ግን ተቃጥለዋል። በዘር የመጣ ይመስል ከአያቴ ጀምሮ የዘመዶቼ ሬሳ በክብር ተቀብረው አያውቅም። ይኸው አባቴ እንኳ በሰው ሀገር ቀርቷል።

*****************************************

*****************

ጦርነቱ እንደገና ወደ ጉና እና ጋይንት ተመለሰ፣ ወያኔ አፈገፈገች ተባለ። ስደተኛው ሁሉ ወደየቤቱ ተመለሰ። እኔም ተመለስኩ። ግን ቤታችን የነበረበትን አካባቢ ሳይ ህሊናዬ ተነካ። ያባቴ ወንድሞች ሊያጽናኑኝ ሞክረዋል። ግማሽ እብድ እና ግማሽ ጤነኛ ሰው ስሆንባቸው የጦርነቱ ጉዳይ ከለየለት በኋላ ጸበል ይዘውኝ እንደሚሄዱ ሲያወሩ ሰምቻለሁ። አንድ ቀን ከአጎቴ ቤት ‹ወጀጅ› ብየ ጠፋው። አመድ በር (አሁን አለም በር) ገበያ በአሞራ ገደል አድርጌ ሄድኩ። አንድ አውቶቡስ ቆሞ ተመለከትኩና ወደ ውስጥ እየፈራወው ገባሁ። ለመጓጓዣ ገንዘብ እንደሚከፈል አውቃለሁ። ነፍሱን ይማረውና ወንድምጋሽ ይነግረኝ ነበር። እርሱ እስከ ወረታ ድረስ ለምን እንደሆነ ባላውቅም ሂዶ ነበር።

ከመኪናው የኋላ ወንበር አካባቢ ወንበር ስር ገብቼ ተኛው። አውቶቡሱ ጥቅጥቅ ብሎ በሰው ከተሞላ በኋላ እየተንገጫገጨ መጓዝ ጀመረ። ልቤን አጥወለወለኝና አስመለሰኝ። ከተኛሁበት ላይ ለቅቅኩት። አውቶቡሱ በየቦታው እያወረደ ይጓዛል። በመጨረሻ ትኬት መልሱ እያለ አውታንቲው (ረዳቱ) ትኬት ይሰበስብ ጀመር። አውታንቲው ወንበር ስር ከትውኪያዬ ጋር ስጨማለቅ አየኝና የታለ ትኬትህ አለኝ። ዝም አልኩ። መኪናው እየሄደ በሩን ከፍቶ ወደ ውጭ አምዘገዘገኝ።

መንገድ ላይ ራሴን ስቼ ለምን ያህል ጊዜ እንደቆዬው አላውቅም። ምናልባትም መኪና ስላልመጣ እንጅ ሊሄድብኝ ይችል ነበር። ከጊዜ በኋላ ቀስ ብዬ ከመንገድ ወጥቼ እስከ ምሽት ድረስ ተኛው። አንድ ሰው መንገድ ዳር ለምን እንደተኛው ቀስቅሶ ጠየቀኝ። ጸበል እየሄድኩ እንደሆነ ከነገርኩት በኋላ ከቤቱ ወስዶ አስተናገደኝ። ምሽት ያስተናገዱኝ ሰዎች ሲያወሩ ቦታው ደራ አፈረዋናት ሀሙሲት አካባቢ መሆኑን አወቅኩ።

ደራ የመገኜቴ ነገር ሳላስበው ወደ አቡነ ሐራ ድንግል ለመጸበል አሰብኩ (አቡነ ሐራ ጸበል በድፍን በጌምድር የታወቀ ነው)። ከአረፍኩበት ብዙም ሩቅ አልነበረም። ደራ አቡነ ሐራ ገዳም ለአንድ ወር ያክል ተጠመቅኩ። ወያኔም አገሪቱን እንደተቆጣጠረ የገዳሙ መነኮሳት ሲያወሩ ሰማሁ። (ይቀጥላል)

---

የወላድ እኮ ጭንቅ ነው
የትውልድ አእምሮ በስልት፣ አገር በሕብር የሚያምጠው::
መቼ ዋዛ የኛ ጉዞ
ቅድመ-ታሪክ ይዞታችን፣ አገር ዳግም ሳይቀረፍ
ምድራችን ሳይቸረቸፍ
ኢትዮጵያዊነታችንን፣ ክብራችንን ሳንገፈፍ
ለአዲስ ትውልድ አስረክበን እንደምን በክብር እንለፍ
እኛስ ለእኛ እንዴት እንትረፍ
ምንስ ሥልጣኔ እናስቀር
ከባላንጣ ጋራ በብስለት፣ እንዴትስ እንደራደር?!...
ዲፕሎማሲ እሚሉትንም፣ ምኒልክ ትልሙን አልፈራም
ግን አልፈራም በሚል እልክ፣ አርነቴን አላስገፋም::...
መቼ ዋዛ!...›

‹‹የጀግናው ወንድምህ ግጥም ባያልቅም ይበቃኻል:: አየኸው፡ - ይህ ግጥም ነፍስ ያስቋጥራል:: ብዙ ያስተምራል፤ አያሌ ጥያቄዎችን ይጠይቃል፤ ንቃተ-ኅሊናን ያጎለምሳል::››

‹‹ከጨለማ ውስጥ ብርሃንን መፈንጠቅ እንዲቻል ያህል፣ ከባላንጣ ጋራ ስትጓዝ ስልታዊ ጉዞ መሰነቅህን እንዳትዘነጋ ይመክርሃል:: ጉዞህ በደንበርባራው ከሆነ ግን፣ አውሮጳውያኑና አሜሪካውያኑ የፈለጉትን አረም እያነሱ እየጫኑብህ ያዳፍኑሃል፤ መልሰው መላልሰው ያፌዙብሃል::

‹‹ቀለሙን የቀየረው ወረቀት ወይም ብር የሚሉት ነገር ከመገልገያነት አልፎ ለመመለክ እስኪበቃ አጉነውታል:: ከራስህ ጋራ ሳትግባባ እንዲሁ ስትቅበዘበዝ እንድትኖር በገንዘብ ጦር ሰቅዘው ይዘውኻል፤ ስለገንዘብ ብቻ በመጨነቅ ‹ቢዚ› እንድትሆን፣ ከቤት እስከ አደባባይ ስለ ‹ቢዝነስ› ይወራል:: (ቢዚ የሚለው ቃል- ‹ቢዝነስ› ከሚለው ቃል የተደቀለ ዲቃላ ሳይሆን አይቀርም) ስቃይና ድንቁርና ያዘሉና ለቁጥር የሚያታክቱ አስደሳችና ምቹ ነገሮች እየፈጠሩ በቁም ማቃዠት ተክነውበታል::››

‹‹ይህ ነው የ'ነሱ እውነተኛ ማንነት:: ጥቅማቸውንና በጥንቃቄ የተሞላ ዲያብሎሳዊ ማንነታቸውን ለማስረፅ ብሎም ለማስጠበቅ ሲሉ፣ ይህን ምሥጢረዊ ደባቸውን እንዳታውቅባቸው አንተን በውሸት ሸማ ጋርደው ለመኖር፣ ‹ቴሌቪዥን› የተባለ ማደንዘዣ ቁስ አስቀመጡልህ:: ውሸትን ሰገነት ላይ አውጥተውና እውነትን መቃብር ውስጥ ቀብረው ቀስ በቀስ ያዝጉሃል:: በማዛጊያና በማደንዘዣ ቁስ:: ቁሱ በግልጽ ከሚወራለት ዓላማው በታቃራኒ እንዲውል በመደረጉ ‹ማደንዘዣ› የሚል ተቀጥያ ቃል እንዲከናነብ ተገዷል›› አለኝ- ስለ ቴሌቪዥን ያለኝን ስሜት ለማወቅ በጥያቄ እይታ እየተከታተለኝ::

‹‹ቆላ - ደጋ እየረገጥኽ አስቸገርኸኝ እኮ፤ እዚህ - እዚያ እያዛበርኸኝ የቱን ልጨብጠው? አንዴ ስለተፈጥሮ፤ እንደገና ስለ አውረጳውያኑ፤ አሁንም ስለ'ኛው መሪ... እንደገና ደግሞ ስለ ኢትዮጵያዊነትና ማንነት... ይህ ሁሉ በዚህ ቅጽበት ያስፈልገኛል?›› አልኹ - ተማርሬ::

‹‹አንተ ስልቹ! አያት ቅድመ-አያቶችህ ሁልቆ-መሳፍርት የሌላቸው ሥራዎችን ሠርተውልህ-ጽፈውልህ ያለፉት ብርቱ ስለነበሩ ነው፤ የማያንቀላፉ ትጉኃን ስለነበሩ ነው:: አየህ፣ አንተ ግን በዚች ቀላልና አጭር ጉዳይ ተሰላቸህ፤ ለዚህ ነው ‹አልዘሩ-በቀል!› የምልህ:: የምትደሰትበት ሳይኖርህ የምትጠላው ነገር ቢኖር ምን ምርኩዝ ይኖርሃል? ልትጠላው የሚገባህን ጠልተህና ጥለህ፤ ነገር ግን መሠረትህን እንዳጸናህ የምትኖረው እኮ የሚያስደስት ነገር እንዳለህ ስታውቅና ስትጠቀምበት ነው::››

‹‹የግእዝ ቋንቋ ሀጋራዊ ፋይዳው ሳይታይህ የአንድ ሃይማኖትና የቄሶች ብቻ እንደሆነ አድርገህ ስታስብ ስንት ዘመን ተረማመደብህ?! ይህን ቁንፅል ሥነ-ልቦናዊ ዐስተሳሰብ መሪዎችህ ይጭኑብሃል፤ (እነርሱም በመደንቆራቸው ስልማይገባቸው) አንተም እነርሱን እየተከተልህ በተከፋፈለ ቋንቋህ ሳትግባባ ተግባብተህ ትኖራለህ:: ግእዝ ግን የትኛውንም ብሔር፣ ክልል ምናምን ብቻ አያካልልም፤ መላ ኢትዮጵያን እንጂ:: የሁሉም ኢትዮጵያዊ እኩል ሀብት ነዋ! ይህ ዐስተሳሰብ ቢገዝፍ፣ የመከፋፈል ሴራ ያዘለው ‹የብሔር ብሔረ-ሰቦች› ቀን ሳይሆን የሚከበረው ‹የኢትዮጵያ ቀን› እየተባለ በየዕለቱ ይከበር ነበር:: ቋንቋው ...ኛ፣ ምንኛ እያለ በክልል አይከፋፍልም:: ብሔራዊ ቋንቋ ብታደርገው እንዳባቶችህ ከምትቀስመው ዕውቀት ባሻገር አንድነትህ እንዴት ይፈረጥም ነበር መሰለህ:: ከዚህም ሌላ ስንት ዕውቀቶችንና ምሥጢር አዘል ጥበቦችን እንደተሸከመ ብታውቅ፣ የገብስ ገብስ ሕይወት ከሚያንፏቅቅህ እንግሊዝኛ ይልቅ ከግእዝ ጋራ እንደተጣበቅህ ከሕይወት ዘመንህ ትጨልፍ ነበር:: አውሮጳውያኑና ደናቁርት መሪዎችህ ግን ይህን መሰል ጉዳይ እንድታውቅ አይፈልጉም:: ካልደነቆርህ እንደፈለጉ አይጠመዝዙህማ!››

‹‹በል እግዲህ፣ ከዚህ በላይ ሳትሰለችብኝ ይብቃኝና፣ ከተነጠፍኽበት ጆንዲ ላይ ንቃ!›› ሲል አዘዘኝና ቀይ ምልክት አሳይቶኝ ከመኝታዬ ነጠለኝ::

ይህ ሁሉ እየሆነ ያለው፣ በመሪዎቿ እየነፈረች ያለችውን ዐዲስ አበባን ለቅቄ ወደ አንዷ የኢትዮጵያችን የገጠር ክፍል በመሔድኹበት ወቅት ነው:: ተንፈስ ለማለት፤ እውነተኛይቱን ኢትዮጵያን ለማወያየት፤ የዕውቀት ጎተራ ላይ ዕውቀት ለማከማቸት፤ የኢትዮጵያዊነት ማገርን ለማጠንከር፤ ከነገረ-ኃጢአት ለመንጻት፤ ከራስ ጋራ ለመግባባት፤ የተናጋ ማንነትን ለማደስና ለማነፅ፤ የድንቅ ተፈጥሮ ባለቤትነታችንን አውቆ ለማድነቅ፣ ለመመሰጥ፣ ለማጣጣም፣ ኢትዮጵያ ውስጥ መፈጠር ልዩ ዕድለኛ መሆንን ያለመጠራጠር ለመቀበል፤ የኢትዮጵያዊነት ማኅተምን በልብ ውስጥ የማተም ኃይልን ለመጎናጸፍ...በላይኛው ደራሲ ድንቅ ሆነው ወደተጠበቡት የገጠሪቱ ክፍሎች መጓዝ መታደል መሆኑን ብመሰክር ከኢሕአዴግ ውጭ የሚቃወም ያለ አይመስለኝም፤ ቅር የሚለው ካለም በኢህአዴግ ሽንት የተጠመቀ ቅራሪ መሆን አለበት::

አልዘሩ-በቀል!

**ስደተኛ ብዕር** (በዚህ አምድ ስር ባህር ማዶ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊ ምሁራን በተለያየ አጋጣሚ ከሚያቀርቧቸውን ፅሁፎች ውስጥ ሚዛናዊ እና አስተማሪ ያልናቸውን መርጠን እናቀርባለን)

# የአሉላ፣ የዮሐንስ፣ የጎበና እና የምኒሊክ ትውልድ!

በግርማ ሞ.

የዚህ ጽሑፍ ግብ በመንግስት ስልጣን ሽሚያ የተነሳ በአንድ ወገን በዮሐንስ እና በአሉላ ትውልድ በሌላ ወገን በምኒልክ እና በጎበና ትውልድ መካከል የነበረውን የፖለቲካ ባላንጣነት፣ ለስልጣን ሲሉ የተደራረጉትን እና የፈጸሙትን ስህተት መተረክ አይደለም። በመካከላቸው የነበረው ጸብ ዙፋኑ ለእኔ ይገባ ነበር የሚል ጸብ ነበር። የስልጣን ጸብ ነበር። በእርስ በርስ ጦርነት የሚፈጸመው ስርዓት አልባው የመንግስት ሽግግር ባህላችን የፈጠረው ጸብ ነበር። ይህ የቀድሞ አባቶቻችን የፖለቲካ ባህል ችግር ዛሬም አብሮን አለ። ያን ችግር ለማስወገድ ሰላማዊ ትግል ጀምረናል። የኢትዮጵያን ህዝብ የመንግስት ስልጣን ባለቤት ለማድረግ ጉዞ ላይ ነን። ወደ ዴሞክራሲ ለመሸጋጋር በቁርጠኛነት ተነስተናል።

የአሉላ፣ የዮሐንስ፣ የጎበና እና የምኒልክ ትውልድን የፖለቲካ አሰራር ስንመረምር እና ስንመዝን በ19ኛው ክፍለ ዘመን በነበራቸው እውቀት እና የፖለቲካ ባህል ደረጃ መሆን አለበት። ዴሞክራሲያዊ መሆን ነበረባቸው ማለት አንችልም። እኛ ዛሬ በ21ኛው ክፍለ ዘመን ብዙ እውቀት አግኝተንም ገና ዴሞክራሲ አልሆንም። በየደረ ገጹ እና በኢቲቪ እንደታየው እኛ ዛሬ የሰው ልጅ ከነህይወቱ ጉድጓድ ውስጥ እንጥል የለም እንዴ? እኛ ያልደረስንበትን ስልጣኔ እነሱ ለምን አልደረሰቡትም ብሎ መውቀስ ትክክል አይደለም። እንዲያውም እነሱ ፈሪሃ እግዚአብሐር ነበራቸው። የአልቤኒያው ደብተራ መለስ ዜናዊ እና ተከታዮች ግን ፈሪሐ እግዚአብሔር የላቸውም።

የአሉላ፣ የዮሐንስ፣ የጎበና እና የምኒልክ ትውልድን በ21ኛው ክፍለ ዘመን ባገኘነው እውቀት እና ባህል ደረጃ እንስፈራቸው ካልን አንድም ብስለት የለንም አሊያም የጥላቻ እና የክፍፍል ፖለቲካ ሆን ብለን መርጨት ላይ ነን። በጎ ስራ ሰርቶ የህዝብ ድጋፍ ማግኘት እና የስልጣን እድሜ ማራዘም ይቻላል። ያን ማድረግ ሲሳንህ ግን ሌላውን እንዲጠላ በማድረግ መወደድን አገኛለሁ ብለህ የምታስብ ከሆነ ተሳስተሃል። በዚህ አይነት የስልጣን እድሜ ለማራዘም እችላለሁ ብለህ ከሆነ ቆም ብለህ አስብ! ህዝብን አንዴ እና ሁለቴ ማታለል ትችል ይሆናል። ሁሌ ማታለል ግን አትችልም።

ስለዚህ የዚህ ጽሑፍ ግብ ዙፋን ለእኔ ይገባል ከሚል ይነሳ የነበረውን የፖለቲካ ባላንጣነታቸውን መተንተን ሳይሆን የአሉላ፣ የዮሐንስ፣ የጎበና እና የምኒልክ ትውልድ እንደ ኢትዮጵያዊ ለኢትዮጵያ እና ለቀጣይ ትውልድ ሰርቶ እና አውርሶ የሄደውን መመርመር ነው። የአሉላ፣ የዮሐንስ፣ የጎበና እና የምኒልክ ትውልድ የሚጠበቅበትን ሰርቶ ሄዷል ወይ? ሊመሰገን እና ሊወደስ ይገባል ወይ? ልናከብረው ይገባል ወይ? በአልቤኒያው ደብተራ መለስ ዜናዊ እና ተከታዮቹ ሊወቀስ ይገባል ወይ? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ መስጠት ነው። ለእነዚህ ጥያቄዎች በቀላሉ መልስ መስጠት እንድንችል የአሉላ፣ የዮሐንስ፣ የጎበና እና የምኒልክ ትውልድ የመጣበትን ዘመን በአጭሩ በመጎብኘት እንጀምራለን። ለረጅም ዘመን የአባይ ወንዝ ባለቤትነት ምኞት የነበራት ግብጽ ኢትዮጵያን በወታደራዊ ኃይል ከሱዳን ቀላቅላ በመግዛት የጣና ሐይቅና የአባይ ወንዝ ሸለቆ ባለቤት ለመሆን እንደ አውሮፓ አቆጣጠር 1875 (እ.ኢ.አ. 1863) ዓ.ም. ግድም (1) በሰሜን ከመረብ ወዲያ ያለውን ደጋማውን ግዛት ተሻግራ እስከ አድዋ፣ (2) በምዕራብ ከቋራ አልፋ ቤጌምድርን፣ (3) ከቶጆራ ጅቡቲ ተነስታ አውሳንና ሸዋን እንዲሁም (4) ከዜይላ ተነስታ ሐረርጌን ለመውረር ጎንበስ ቀና ማለት ላይ በነበረችበት ሰዓት ነበር የአሉላ፣ የዮሐንስ፣ የጎበና እና የምኒልክ ትውልድ የፖለቲካ ኃይል ከምድር የተነሳው።

የቴዎድሮስ ትውልድ የቅኝ አገዛዝ ዋዜማ ትውልድ ነው። አሰብን በመግዛት ረገድ ሁነኛ ሚና የተጫወተው ጣሊያናዊ በቴድሮስ ዘመን በሚስዮናዊነት በሰሜን ኢትዮጵያ ሲንቀሳቀስ የነበረ ሰው ነው። በቅኝ አገዛዝ ዋዜማ የአውሮፓ ኃያላን መንግስታት በአፍሪካ ውስጥ ባሰራጨዋቸው በዘመናዊ ትምህርት (ፖለቲካ፣ ስለላ፣ ኢኮኖሚክስ፣ ህክምና፣ የመንገድ ስራ፣ የህንጻ እና ድልድይ ስራ፣ የአናጺነት ሙያ ወ.ዘ.ተ.) የሰለጠኑ ሚስዮናውያን፣ ተመራማሪዎችና ቆንሲሎቻቸው አማካኝነት አፍሪካን መውጫዋን፣ መግቢያዋን፣ የተፈጥሮ ሃብቷን፣ የህዝቧን በስልጣኔ ወደ ኋላ መቅረት፣ የዘርና የፖለቲካ ክፍፍሏ ሳይቀር በዝርዝር እየተጠና በሪፖርት እና በመጽሐፍ መልክ ይላክላቸው ነበር። እነዚህ ሪፖርቶች እና መጽሐፍቶች በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቢሮዎች በተቀመጡ እውቅ የፖለቲካ አቀንቃኞች ከልብ እየተጠኑ ለአዲስ መልዕክተኞች ስልጠና ይሰጥ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ በስብሰባም፣ በመልዕክትም፣ በቃልም፣ በፅህፈትም አፍሪካን እንዴት እርስ በርስ ሳይጋጩ በሰላም መከፋፈል እንደሚችሉ አሳብ ለአሳብ ሲለዋወጡ ነበር። በዚህ አይነት አውሮፓውያን እርስ በርስ ሳይጣሉና ሳይዋጉ አፍሪካን የሚይዙበትን፣ ንግዳቸው የሚስፋፉበትን፣ በቀይ ባህር የመርከቦቻቸው ዝውውር በሰላም የሚከናወንበትን ስምምነት ሊዋዋሉ ዝግጅት ላይ ሳሉ ነበር የአሉላ፣ የዮሐንስ፣ የጎበና እና የምኒልክ ትውልድ በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ ብቅ ያለው።

በቀይ ባህር የመርከቦቻቸውን ዝውውር ለማሳካት አውሮፓውያን በቀይ ባህር ዳርቻ ባሉ አገሮች ባህር በሮች እግራቸውን ማስገባት ጀመሩ። በዚህ ረገድ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር 1885 ዓ.ም. ግብጾች ሐረርጌን ሲለቁ ቀደም ብለው ይዘውት የነበረውን የዜይላ እና የበርበራ (ሰሜን ሶማሊያ) ባህር በሮች እንግሊዝ ያዘች። እንግሊዝ ሐረርም ዲፕሎማቶች ትልክ ነበር። ተመራማሪዎች በሚል ሽፋን ፈረንሳይ እና ጣሊያንም ሰላዮቻቸውን ወደ ሐረር ይልኩ ነበር። በመጨረሻ ግብጽ፣ ሱዳን እና ኬኒያም የእንግሊዝ ቅኝ ገዢዎች ሆኑ። እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1862 ግድም ፈረንሳይ ከኦቦክ ባላባቶች የኦቦክን የመርከብ ማቆሚያ ከገዛች በኋላ በወታደራዊ ኃይል ወደ ቶጆራና ጅቡቲ ገባች። እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1882 ዓ.ም. ጣሊያን እግሩን በአሰብ አስገብቶ የቅኝ ገዢ ባንዲራውን ማውለብለብ ከጀመረ ወዲህ ወደ ውስጥ እስከ ሸዋ ድረስ ዘልቆ ልዑካን በመላክ በቀን ስለንግድና ፍቅር እያወራ በለሊት ከአሰብ ወደ ምጽዋ መንፏቀቅ ጀምሮ ነበር። ከዚያ ጣሊያን በወታደራዊ ኃይል እግሩን ምጽዋ አስገባ። በመቅድሾም ተተከለ። ኢትዮጵያ በዚህ አይነት በቅኝ ገዢዎች በተከበበችበት ወቅት ነበር የአሉላ፣ የዮሐንስ፣ የጎበና እና የምኒልክ ትውልድ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ህይወት የገባው።

ስለዚህ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር 1884 (እ.ኢ.አ 1877) ዓ.ም. የአውሮፓ ኃያላን አገሮች በጀርመን (በርሊን) ተገናኝተው አፍሪካን በሰላም እንደ ቅርጫ ለመቀራመት በአሳብ ደረጃ የነበራቸውን ስምምነት በፊርማቸው ሲያጸድቁ የአሉላ እና የዮሐንስ ትውልድ በሰሜን ኢትዮጵያ የጎበና እና የምንሊክ ትውልድ በደቡብ እና በምስራቅ ኢትዮጵያ አገር የመጠበቅ እና የመገንባት ዘመቻዎች በማድረግ ላይ ነበር። ለጥቀን ለናሙና ያህል በአጭር በአጭሩ የአሉላ እና የዮሐንስ ትውልድ በሰሜን ኢትዮጵያ የጎበና እና የምኒልክ ትውልድ በደቡብ እና በምስራቅ ኢትዮጵያ የፈጸሙትን እንጎብኝ።

በሰሜን ኢትዮጵያ የአሉላ እና የዮሐንስ ትውልድ በ1875/6 በጉንደት እና በጉራ የግብጽን ወረራ አከሸፈ። ምጽዋን ለማስመለስ እንዲሁም ከሰላን የኢትዮጵያ ለማድረግ እንግሊዝን ብዙ ታግሏል። እንግሊዝ በፈጸመችው ተደጋጋሚ ክህደት ሳይሳካ ቀረ። በዶጋሊ ወራሪውን የኢጣሊያን ጦር መታ። በዚህን ጊዜ እነ አሉላ ደማቸውን እየጠረጉ ነበር ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነት የተዋጉት። ዮሐንስ ወደ ሰሐጢ ለመዝመት ዝግጅት ላይ ሳሉ ነበር መኳንቶቻቸውን ሰብስበው ለኢትዮጵያ መሞት እንደሚፈልጉ የገለጹት። ዮሐንስ ወዲህ ወዲያ አያውቁም። የሚያደርጉትን የሚነገሩ ሰው ነበሩ። የደርቡሾች በጎንደር እና በጎጃም ህዝብ ላይ የፈጸሙትን ለመበቀል ዘምተው ደማቸውን አፈሰሱ። እንደፈለጉት ለኢትዮጵያ ሞቱ ድንበር ጥበቃ ላይ ሳሉ። አሉላ በአድዋ ዘምተዋል። በደቡብ እና በምስራቅ ኢትዮጵያ ደግሞ የጎበና እና የምኒልክ ትውልድ ባደረገው የመስፋፋት እና የያውን ግዛት የመጠበቅ ዘመቻዎች በሱዳን፣ በኬኒያ እና በበርበራ በተተከለው እንግሊዝ፣ በጅቡቲ በተተከለው ፈረንሳይ፣ በአሰብ እና በመቅድሾ እግሩን ባስገባው ጣሊያን የዛሬው ምስራቃዊ፣ ደቡብ እና ደቡብ ምዕራባዊ የኢትዮጵያ ግዛት እንዳይገዛ አድርገዋል። ዮሐንስ እንደሞቱ ደርቡሽ ከሱዳን እየተነሳ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የጥቃት ዘመቻዎች ጀምሮ ነበር። ጎበና ለአንዴም ለሁሌም አቆመው። የአድዋም ድል ቢሆን እንደ ዶጋሊ ድል አገርን ከቅኝ ገዢ የመጠበቅ ድል ነበር። እስቲ ስለሐረጌ ጨመር አድርገን እንመልከት።

ግብጾች ከሐረርጌ እንደወጡ እንግሊዝ እና ፈረንሳይ ሐረርጌ ላይ አይናቸው አረፈ። ሁለቱ የረጅም ጊዜ የጥቅም ባላንጣዎች ስለነበሩ ብዙ ጊዜ ተዋግተዋል። በዚህን ጊዜ ግን ሁለታችንም ሐረርጌን አንይዝም የሚል ውል በመፈራረም ውጊያን አስወገዱ። ይሁን እንጂ ኢንግሊዝ ሐረርጌን ከዜይላ ቀላቅሎ የመግዛት ስውር ምኞት ነበራት። ፈረንሳይም ከእንግሊዝ ጋር የተፈራረመችውን ውል ክዳ ሐረርጌን ከቶጆራንና ጅቡቲ ለመቀላቀል የምትችልበትን አመቺ ጊዜ እየጠበቀች ነበር። ጣሊያንም በበኩሏ እንግሊዝ እና ፈረንሳይን ሸውዳ ሐረርጌን ከአሰብ ለመቀላቀል ትልቅ ምኞት ነበራት። ስለዚህ ሁሉም በየበኩላቸው አድብተው በአገር ጂኦግራፊ ምርምር ሽፋን ሰዎቻቸውን ወደ ሐረርጌ እየላኩ መንገዱን፣ ወንዛ ወንዙን፣ መውጫ መግቢያውን፣ ተራራውን ሲያስመረምሩ ነበር። እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1886 ዓ.ም. ግድም ጣሊያናዊ አገር መርማሪዎች (ወይንም አንድ መርማሪ) በሐረር ሲዘዋወሩ ሐርቲ የተባለ ቦታ ሲደርሱ የሐርረ አሚር አብዱላሂ ሰዎች ገደሉዋቸው። ጣሊያን "የዜጋዬን መገደል መበቀል ህጋዊ መብቴ ነው አለች።" ሐረርጌን ለመያዝ በቂ ሽፋን አገኘች። ጣሊያን በወታደራዊ ወረራ ሐረርጌን ለመያዝ ፕላንና ጊዜ በማማረጥ ላይ ባለችበት ጊዜ ነበር የጎበናና እና የምኒልክ ትውልድ ሐረርጌን ከኢትዮጵያ የቀላቀለው። ምኒልክ ሲዘምት ጎበና በሸዋ ሆኖ አገር ያስተዳድራል። ጎበና ሲዘምት ምኒልክም በሸዋ ሆኖ አገር ያስተዳድራል። በዚህን ጊዜ ምኒሊክ ወደ ሐረርጌ ዘመተ። ጣይቱ የዛሬዋን አዲስ አበባ ከተማ የቆረቆረችው ምኒልክ ከሐረርጌ ሳይመለስ ነበር።

ስለዚህ እንደ ኢጣሊያ ምኞት ቢሆን ኖሮ ምናልባት ዛሬ ሐረርጌ ከአሰብና ከምፅዋ ጋር ተቀላቅላ በኤርትራ ግዛት ውስጥ ልትሆን ትችል ነበር። እንዲሁም እንግሊዝ እንደ አሰበችው ቀንቷት ቢሆን ኖሮ ዛሬ ሐረርጌ ከዜይላ ጋር ተቀላቅላ የሰሜን ሶማሊያ አካል ትሆን ነበር። አሊያም የጅቡቲ አካል ትሆን ነበር ፈረንሳይ ያሰበቸው ቢሳካላት ኖሮ። ሐረርጌ በምኒልክ መያዙን እንግሊዞችንም፣ ፈረንሳዮችንም፣ ጣሊያኖችም በጣም ቆጭቷቸዋል።

ኢትዮጵያን ከቅኝ ገዥዎች በመጠበቅ እና ለቀጣይ ትውልድ በማስረከብ ረገድ የአሉላ፣ የዮሐንስ፣ የጎበና እና የምኒሊክ ስራዎች ተጋጋዥ ነበሩ። ግብጽ በጉንደት እና በጉራ መሸነፏ ያደረሰባት የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ድቀት ሐረርን ማስተዳደር እንዳትችል አደረጋት። የዶጋሊ ድል የአድዋ ቅድመ-ድል ነበር። ይህ ትውልድ በአላማ አንድ ነበር። አገር ጠብቆ አውርሶ ሄዷል።

ስለዚህ በየዘመኑ የመጡት የቀድሞ አባቶቻችን በዘመናቸው የሚያውቁትን አሰራር ተጠቅመው አገር ገንብተው እና ጠብቀው በማውረሳቸው ሊመሰገኑ እንጂ ሊኮነኑ አይገባም። ከስህተታቸው መማር በሚል ሽፋን የአልቤኒያው ደብተራ መለስ ዜናዊ እና ተከታዮቹ ከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ መቆም አለበት። ከስህተት መማር ማለት ቀደም ብለው የተፈጸሙ ስህተቶች እንዳይደገሙ ህዝብን ማስተማር ማለት እንጂ ህዝብ መካከል ጥላቻ መትከል ማለት አይደለም። የቀድሞ አባቶቻችንን ስህተቶች ብቻ እያባዙ እና እያሳበጡ (እየፈጠሩም) አገር አውርሰውን የሄዱትን ዛሬ በህይወት የሌሉ የቀድሞ አባቶች በቋሚነት መክሰስ ስህተት ነው። በህይወት ቢኖሩ ኖሮ የሚቀርቡባቸውን ክሶች መከላከል ይችሉ ነበር። በዚህ አይነት ዛሬን እና ነገን የትናንት እስረኛ ማድረግም ከጥቅሙ ጉዳቱ ይበልጣል። ያን የሚያደርጉ ሰዎች አንድም ስለ አለም ህዝብ እና ህብረተሰብ እድገት ታሪክ እውቀት የላቸውም አሊያም ሆን ብለው ከፋፍሎ የመግዛት ፖለቲካ በማራመድ የስልጣን ዘመናቸውን ለማራዘም ጥረት ማድረግ ላይ ናቸው። ይህን የሚያደርጉ ሰዎች ከፋፍሎ መግዛት ፖሊሲያቸው ነው። ለጥቀን የአልቤኒያው ደብተራ መለስ ዜናዊ እና ተከታዮቹ የመጡበትን ዘመን፣ የፈጸሙትን እና ለቀጣይ ትውልድ ያወረሱትን በአጭር በአጭሩ በመመልከት አጭር ንፅፅር እናድርግ፥

(1) የመጡበት ዘመን የኢትዮጵያ ሉዓላዊነት መከበር ባለበት ዘመን ሲሆን ያደረጉት ግን ለስልጣናቸው

እድሜ ማራዘሚያ ሲሉ ኢትዮጵያን ቅኝ ገዥ በማድረግ አገር ማፍረስ እና ኢትዮጵያን ባህር በር አልባ ማድረግ። የሱዳን፣ የጅቡቲ እና የሌሎች ጎረቤት አገሮች ወደቦች ጥገኛ (ፖለቲካዊ፣ ንግድ፣ ወታደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ጥገኝነት) ማድረግ። የሚከፈለውን ክፍያ ሳናነሳ። የምዕራቡን የኢትዮጵያ ለም መሬት ለደርቡሾች (ለሱዳን) መስጠት ነው። የዮሐንስ ደም የፈሰሰበት መሬት ሳይቀር ለደርቡሽ መስጠት። ለመጪው ትውልድ የሚያወርሱትም ይህንን ነው። አሳፋሪ ውርስ ነው።

(2) የመጡበት ዘመን ኢትዮጵያ ወደ ዴሞክራሲ መሸጋገር በምትሻበት ጊዜ ነው። ያደረጉት ግን የከፋፍለህ

ግዛ ፖለቲካ ማሰራጨት። ታሪክን መነሻው ያደረገ ከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ። የቀድሞ አባቶችን ስራ መሰረት ያደረገ ከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ። ጎሳን መስፈንጠሪያው ያደረገ ከፋፍለህ ግዛ ፖለቲካ። ዛሬም ዴሞክራሲ የለም። ለመጪው ትውልድ የሚያወርሱትም ይህንን ነው። አሳፋሪ ውርስ።

(3) የመጡበት ዘመን ቀድም ብለው በታሪካችን የነበሩ ሚዛናዊ ያልነበሩ ግንኙነቶች በአግባብ እየተጠኑ

ህዝብን ባሳተፈ መልኩ መፍትሄ መስጠት በሚያስፈልግበት ጊዜ ነው። ያደረጉት ግን ሚዛናዊ ያልነበሩ

ግንኙነቶችን እያነሱ ለራሳቸው ስልጣን ላይ መቆየት በሚጠቅም መንገድ ማወሳሰብ ነው። ለቀጣይ ትውልድ የሚያወርሱትም ይህንኑ ነው።

ስለዚህ የአልቤኒያው ደብተራ መለስ ዜናዊ እና ተከታዮቹ ከአሉላ፣ ከዮሐንስ፣ ከጎበና እና ከምኒሊክ ትውልድ ጋር ፍጹም ሊነጻጸሩ አይችሉም። ቢነጻጸሩም የአልቤኒያው ደብተራ መለስ ዜናዊ እና ተከታዮቹ በታሪካችን እጅግ ዝቅተኛ ቦታ ይይዛሉ። የአሉላ፣ የዮሐንስ፣ የጎበና እና የምኒሊክ ትውልድ ያን የቅኝ አገዛዝ ዘመን በመሃይም አዕምሮዋቸው ሁለት እና ሶስት የኮሌጅ ድግሪ የያዙ ቅኝ ገዢዎችን ተቋቁሞ ከሞላ ጎደል አገር ጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ በማውረሱ ዛሬ በቅኝ ገዢዎች ያልተገዛች አገር አለን። ስለዚህ እንደእኔ ከሆነ ትውልዱን የሚወክል አራቱ ሰዎች በተርታ ያሉበት ሐውልት መትከል አለብን። ባለውለታዎች መሆናችንን የሚገልጽ ሐውልት።



በ
ገ
ብ
ያ
ላ
ይ

